# የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ማጣቀሻ ሰነድ



Funded by European Union Humanitarian Aid
Global Protection Cluster
NEAR Network for Empowered Aid Response
OXFAM
HPG Humanitarian Policy Group
ODI

# ይዘት

## የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ማጣቀሻ ሰነድ 05

1. የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ዓላማዎች ምንነት 08
2. የባለድርሻ አካላት ልየታ፣ የሐይል ሚዛን ትንተና እና የለውጥ ፅንሰ-ሃሳብ 16
3. የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት አቀራረቦች እና ዘዴዎች 27
4. የሙግት ውጤቶችን ክትትልና ልኬት 37
5. የተጋላጮች ጥበቃ አድቮኬሲ ስጋት ቁጥጥር 44
6. ተጨማሪ አጋዦችን፣ ምንጮችንና መመሪያዎችን ማመሳከር 48

## የተጠናቀሩ የሁነት ጥናቶች 50

በሰሜን-ምዕራብ ሶሪያ የሚገኙ የሴት መምህራንን መብት ማጠናከር 50

በደቡብ ሱዳን ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች መፍትሄ ማስቀመጥ 55

በተወረሩ የፍልስጤም ግዛቶች የሚኖሩ ሴቶችን መብት ማስጠበቅ 60

## አጋዦች እና መመሪያዎች 64

አጋዥ **#1:** የተጋላጮች ጥበቃ የሙግት 'ችግሮች' እና ግቦችን መለየት 65

አጋዥ **#2:** የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት አላማዎች ምንነት 70

**አጋዥ #3:** የባለድርሻ አካላት ልየታ 72

አጋዥ **#4:** የሃይልና የባለድርሻ አካላት ትንተና ለስትራቴጂ ያለው አንድምታ 73

**አጋዥ #5:** የመረጃ አሰባሰብ እቅድ ማሳያ 75

**አጋዥ #6:** ከሙግት መድረኮች በኋላ አጭር መግለጫ አዘገጃጀት መመሪያ 76

**አጋዥ #7:** ወሳኝ የፖሊሲ ክንውንን መመዝገብ 78

**አጋዥ #8:** ለለውጥ ያለውን አስተዋፅዖ መገምገም 83

**አጋዥ #9:** የፔስትል መመሪያ 87

**አጋዥ #10:** ፈጣን እና ቀላል የአደጋ ስጋት ማትሪክስ 89

**አጋዥ #11:** የትራፊክ መብራት ሲስተም ምሳሌ 92

**አጋዥ #12:** የአደጋ ስጋት አጠቃላይ እይታ 94

**አጋዥ #13:** የአደጋ ስጋት ማትሪክስ (matrix) - መለኪያዎች: ዕድል / ተጽዕኖ 95

**ማስታወሻዎች......................................................................................................100**

# የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት

# ማጣቀሻ ሰነድ





*ሁለት ሴቶች በዳር አግ የተፈናቃዮች ጣቢያ (Dar Agg IDP camp) ፎቶ ፓብሎ ቶስኮ(Pablo Tosco)*

# መግቢያ

የዓለማቀፍ የሰብዓዊ ድጋፍና ጥበቃ ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ በመጨመር ላይ ይገኛል። ይህ ሰነድ እየተዘጋጀ ባለበት እኤአ በ2023 ሶስት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ሚሊዮን (339 ሚሊዮን) ሰዎች ማለትም በአለማችን ላይ ካሉ ከ23 ሰዎች አንዱ በህይወት ለመኖር ግዴታ አስቸኳይ የሰብዓዊ እርዳታ ያስፈልገዋል ተብሎ ይገመታል። ግጭት የእንደዚህ አይነት የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎቶች ቁልፍ ምክንያት በመሆኑ፣ የተጋላጮች ጥበቃ በግጭት እና ቀውስ የተጎዱ ሰዎችን መብት ማስከበር እንደ ወሳኝ እና ሕይወት አድን ተግባር አካል ሆኖ የቀጠለ ቢሆንም አዳዲስ እና ረዘም ላለ ጊዜ የቆዩ ግጭቶች፣ ለሰብዓዊ መብቶች እና ለሰው ህይወት መጥፋት ግድየለሽነት መስፋፋት ዋና አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

የተጋላጮችን ጥበቃን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት በአብዛኛው ኃላፊነታቸውን ሲወጡ አይታዩም፣ ወይም ሀላፊነታቸውን ለመወጣት ፈቃደኞች አይደሉም። በግጭት እና ቀውስ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን መብት ለማረጋገጥ ሃላፊነት ያለባቸው አካላት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ እና ግዴታቸውን እንዲወጡ ግፊት ማድረግ አንዱ የተጋላጮች ጥበቃ ሥራ ወሳኝ አካል ነው። ይህ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት (Protection Advocacy) ብዙ መልክ ያለው እና በተለያዩ አወቃቀሮች እና አደረጃጀቶች የሚካሄድ ሲሆን፣ ይህም የአካባቢ ባለስልጣናት ግፊት ማድረግ ከሚችሉ ማህበረሰቦች አባላት እስከ አገር አቀፍ ባለድርሻ አካላት ብሎም ዓለማቀፍ ደረጃ ሊሰራ ይችላል።እነዚህ የሙግት ስራዎ የሚኖራችውን ተጽዕኖ ለመጨመር በተለያዩ መንገዶች እና ቦታዎች ላይ ስለ ተጋላጮች ጥበቃ የሚሟገቱትን ሁሉ በጋራ ማስተባበርና ማጣመር የሚያስፈልግ ሲሆን ይህም የባለድርሻ አካላት ቅንጅት ሁሉም የየራሳቸውን ችሎታ፣ አቅም፣ ክህሎት እና የግንኙነት መረባቸውን ተጠቅመው የራሳችውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያስችላል፡፡

ይህ ሰነድ (toolkit) የተጋላጮችን ጥበቃ ውጤታማ እንዲሆን ለሚሞግቱ/ግፊት ለሚያደርጉ ግለሰቦች፣ ድርጅቶች እና መዋቅሮች አጋዥ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው። ሰነዱ አምስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የተጋላጮችን ጥበቃ ሙግት የዑደት ደረጃዎችን የሚገልጽ እና እያንዳንዱን ደረጃ ለመቃኘት የሚያስፈልጉ ቁልፍ አጋዥ መመሪያዎችን ወይም መሳሪያዎችን የያዘ ነው፡፡ በዚህ ሰነድ የተካተቱት ሞጁሎች አቀማመጥ የግዴታ ቅደም ተከተላዊ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡ ይልቁንም ሙግት እንደየሁኔታው የሚለዋወጥ፣ የራሱ የሆነ አካሄድ፣ የአደጋ ስጋት ትንታኔ፣ እንዲሁም ስልቶች ያሉት እና ተለዋዋጭ እውነታን ያማከለ ተደጋጋሚ ሂደት ነው፡፡

የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት (Protection Advocacy) አድካሚ ስራ ቢመስልም፣ ይህ ሰነድ (toolkit) የሙግት ስራን በቀላሉ ለማስረዳት የተለያዩ ግለሰቦች እና ኤጀንሲዎች በጋራ እንዲሰሩ በማበረታታት እና ከተጋላጮች ጥበቃ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስጋቶችን ለመቀነስ እንዲሁም የቀውስ ሰለባ ለሆኑ ሁሉ መፍትሄ የሚሆኑ ውጤቶችን ለማጠናከር የተለዩ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን አካታችነት ያበረታታል ተብሎ ይታሰባል።

ይህ ሰነድ የኔትወርክ ፎር ኢምፓወርድ ኤይድ ሪስፖንስ (Network for Empowered Aid Response (NEAR)) ፣ የአለማቀፍ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት እና የሙግት ስራ ቡድን (The Global Protection Cluster and its Advocacy Task Team) ፣ የኦክስፋም አለማቀፍ የሰብዓዊ ድጋፍ ቡድን (Oxfam’s Global Humanitarian Team)፥ እና የኦድአይ የሰብዓዊ ድጋፍ ፖሊሲ ቡድን (the Humanitarian Policy Group (HPG) at ODI) ባደረጉት አስተዋጽኦ የተዘጋጀ ነው።ሰነዱ የተዘጋጀው ከአውሮፓ ህብረት የሰብዓዊ ድጋፍ በኦክስፋም በኩል እና ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር (UNHCR) በኔትወርክ ፎር ኢምፓወርድ ኤይድ ሪስፖንስ (NEAR) በኩል ባደረጉት የፋይናንስ ድጋፍ ነው። በተጨማሪም የሁራስ ኔትወርክ (Hurras Network) እና የፍልስጤም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህብረት (Palestinian NGO Network) እጅግ ዋጋ ያላቸው ጥናቶችን (case studies) አበርክተዋል።

ሞጁል

# 1 የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ዓላማዎች ምንነት

የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት (Protection Advocacy) በዓለም ዙሪያ ያሉ የተለያዩ ማህበረሰቦች የሚያጋጥሟቸውን በርካታ የአደጋ ስጋቶች ተደራሽ የሚያደርግ የሰብዓዊ ድጋፍ ተግባር ወሳኝ አካል ነው። አብዛሀኛውን ጊዜ ሙግትን የሚሹ ጉዳዮች የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ዙሪያ ለተሰማሩ ባለድርሻ አካላት አዳጋች ቢሆንም፣ ግልጽ የሆኑ የሙግት ጉዳዮችን ለይቶ መጀመር ጠቃሚ ይሆናል። እነዚህ የሙግት ጉዳዮች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በሙግት ጥረቶች ሊለዩ ይችላሉ። በዋናነት በሙግት ስራ ላይ ትልቁ ተፅዕኖ መምጣት የሚችለው ከሌሎች ስራዎች (interventions) ጋር በማጣመር ከትንሹ ጅማሮ ('move the needle') ተነስቶ በማቀድ ልዩ ስጋቶችን ተጋላጭነቶችን እና አቅሞችን ያማከሉ ሙግት ተኮር ተግባራትን እና ፕሮግራሞችን መስራት ሲቻል ነው፡፡[2]

የሙግት ጥረቶች መቼ እና እንዴት ውጤታማ እንደሚሆኑ ለመረዳት ብሎም በሂደት ቅርጽ ለማስያዝ የተጋላጮች ጥበቃ ሁኔታ ትንተና ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል። ይህ ሞጁል ከተለየ የተጋላጭነት አደጋ ስጋትና ግልጽ የሆነ የሙግት ግብና ዓላማ ለማስቀመጥ የተጋላጭነት ትንታኔ እንደ መሰረታዊ የሙግት ስልት ይጠቀማል።

**ምስል 1.1 የተለያዩ የተጋላጮች ጥበቃ አጋሮችንና ወዳጆችን ትብብርና ቅንጅታዊ አካሄድን ታሳቢ በማድረግ የተጋላጭነት ሙግት ስልት አዘገጃጀት ቁልፍ የሂደት ደረጃዎችን ያሳያል፡፡**

## የተጋላጭነት ትንታኔ የስኬታማ ሙግት መሰረት ነው፡፡

እንደ ኢንተር ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ (Inter-Agency Standing Committee (IASC)) የተጋላጭ ጥበቃ በሰዓዊ ድጋፍ ፖሊሲ (Policy on Protection in Humanitarian Action (2016))[3] መሰረት የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና ባህሪና ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ በመፍጠር ምቹ የጥበቃ አውድ እንዲኖር ለማስቻል በማስረጃ የተመሰረተ ፕሮግራም፣ ሙግትና ውይይትን መፍጠር ይኖርበታል።



**የተቀናጀ የተጋላጭ ጥበቃ ትንተና ለተቀናጀ የተጋላጮች የጥበቃ ሙግት ዋና መሰረት ነው።**

የተጋላጮች የጥበቃ ትንተና ለተቀናጀ የሙግት አቀራረብ መሰረት ይጥላል። ይህም የሚሆነው የጥበቃ ስጋቶችንና ተያያዥ ሁኔታዎችን (እንደ ስጋቶች፣ ተጋላጭነት፣ አቅም እና መሰረታዊ መንስኤዎቻቸው) የጋራ መግባባት በመፍጠር፣ በተለያዩና ታማኝ የመረጃ ምንጮች ላይ በመመስረት፣ የተለያዩ አጋር አካላት በተቀናጀ መልኩ ስጋትን የሚቆጣጠሩበትና ተመጋጋቢ የሙግት አካሄዶችና ስልቶችን በመጠቀም የጋራ ድምጽ ማሰማት የሚያስችል አካሄድ ይፈጥራል።

**ምስል 1.1፡ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ስትራቴጂ ሂደት**




ከProCap's '*Advocacy for Protection Outcomes*' የወርክሾፕ ሰነዶች፣ እ.ኤ.አ 2021 የተወሰደ

## በተጽዕኖ ማሳደር ሂደት የስርዓተ-ጾታ ትንተናና የፌሚኒዝም አካሄድ

የሴቶችን መብት ተሚጋችነትን የተከተለ ሙግት የስርዓተ-ጾታ ትንተናን የስልታዊ እቅዱ ዋና ትኩረት በማድረግ የተጋላጭነት ጥበቃ ጉዳዮችን በሴቶች መብትና እነዚህን መብቶች ለማስከበር በተቀመጡ አለም አቀፍ የህግ ማእቀፎች ላይ በመመርኮዝ ያስቀምጣል።

የስርዓተ-ጾታ ትንተና የማህበረሰቡን ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚለዋወጥ ወቅታዊ የተጋላጭነት ጥበቃ ግንዛቤን ያስጨብጣል። የስርዓተ-ጾታ ትንተና ስለ ሴቶችና ልጃገረዶች ብቻ አይደለም። ይህም የሴቶችንና ወንዶችን፣ የልጃገረዶችንና ታዳጊ ወንዶችን ልዩ ልዩ ፍላጎቶችንና የህይወት ተሞክሯቸውን በጥልቀት መዳሰስን ይመለከታል።

የስርዓተ-ጾታ ትንተና የሰዎች የተዛመዱ/ የተሳሰሩ ማንነቶች ማለትም መደብ፣ ጾታ፣ ዘር ወዘተ እንዴት ሃይልና ልዩ ጥቅም እንደሚወዳጁና ለተለያዩ ስጋቶችና መገለሎች ተጋላጭ እንደሚያደርጋቸው ያጠናል።

የስርዓተ-ጾታ ትንተና ሴቶች፣ ወንዶች፣ ልጃገረዶችና ታዳጊ ወንዶች የሚያጋጥሟቸው የተለያዩ ተሞክሮዎች፣ አቅም፣ ስጋቶች ግንዛቤ ውስጥ እንደገቡና ተገቢ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ለማድረግ ያስችላል። በመሆኑም ጠንካራ የስርዓተ=ጾታ ትንተና የተጋላጮች ጥበቃ የትንተና ማእቀፍ አካል ተደርጎ እና የተቀመጠ የትንተና መሳሪያ በማድረግ ወይም ራሱን የቻለ የትንተና ሰነድ ተደርጎ ሊዘጋጅ ይችላል።[4]

የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና ሂደትና ውጤቶች በቀጥታ የሙግት ስትራቴጂውን የመወሰን አቅም ያላችው መሆን አለባቸው። የተጋላጮች ጥበቃ ትንተናና ምክረ ሃሳቦችን በመለየት ሂደት ውስጥ የሚከትሉትን ልናገኝ እንችላለን።

- ስለ ተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች፣ ውጤት፣ እና ህዝብና ማህበረሰብ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከት ግልጽ መረዳትን።
- ተለይተው በታወቁ የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች እና የትኞቹ ባለድርሻ አካላት በሚፈለገው ለውጥ ላይ ተጽእኖ የማሳደር አቅም እንዳላቸው
  በተፈጠረ ግንዛቤ መሰረት ኢላማዎች ሊለዩ ይችላሉ።
- የተለዩ የሙግት አካላት ፍላጎትና እሴትን ያማከለ ምክረ ሃሳብና መልዕክት ለማዘጋጀት የሚያግዝ የተደራጀ ማስረጃ መኖር።
- የተለዩ አካላትን ሊያነሳሱ የሚችሉ እነዚህን መልእክቶች ማስቀጠል የሚያስችሉ አካሄዶችንና ስልቶችን ላይ መነሻ ሃሳብ ማግኘት


ሳፊያ በኢሲዮሳ፥ ኬንያ፥ ፎቶ ሎሊ ዌ ፊሪ/ኦክስፋም

እነዚህ የተለያዩ ጉዳዮች ከአጋሮችና ወዳጆች ጋር ቢጋራ በመሆን የተቀናጀ የስትራቴጂ ዝግጅት ሂደት አካል ተደርገው የበለጠ መተንተንና መደራጀት አለባቸው።

የተጋላጮች ጥበቃ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የስጋት ምንጮችን ተደራሽ ለማድረግና ስጋትን በመቀነስ የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ከሌሎች አካላትና ወዳጆች ጋር በመተባበር የወደፊት መንገዶችንና ወሳኝ ምእራፎችን ለመለየት ትንታኔውን መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ይህን የመሰለ ጠንካራ መሰረት ያለው የጋራ ሃሳብ መያዝ ወደፊት ለመጓዝ ጥሩ እድል ይፈጥራል፡፡ ትንታኔው ወደፊት ለሚመጣው መሰረት ይሆናል ማለት ነው። ይህም የሚሆነው የተለዩ የተጋላጮች ጥበቃ ስጋትን ተደራሽ ለማድረግና የሙግት አላማዎችን ለማሳካት መልእክቶችን መቅረጽ፣ ትረካዎችና የሙግት ተግባራትን መከወን አስፈላጊ ስለሆነ ነው[6]።

### ለሙግት የሚጠቅሙ የተጋላጮች ጥበቃ ትንተናዊ ማዕቀፍ ግብዓቶች

የተጋላጮች ጥበቃ ትንታናዊ ማዕቀፍ (Protection Analytical Framework (PAF)) የተጠናከረና አውድን ያገናዘቤ የጥበቃ ትንታኔ እንድኖር ያግዛል።

ይህም የተጋላጮች ጥበቃ ስጋትን ለመቀነስ የሚረዱ ስትራተጂዎችን በማጎልበት ትንታኔያዊ መደምደሚያዎችን ይደግፋል። ቀጣይነት ያለው ትንታኔ እንዲኖር ለማረጋገጥና አስፈላጊ የማላመድ እርምጃች እንድወሰዱ ለማድረግ ቀውስ በተቀሰቀሰበት ጊዜና በቀውስ ውሰጥ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሰረት የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ ማዕቀፍ (PAF) አካል የሆኑ ልዩ ግብዓቶች በተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ስትራቴጂ ሂደት ወቅት አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ።

**አባሪ 2፡ የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ ማዕቀፍ (PAF) ትንታኔ ሂደት ሲገለፅ**

ይህ አባሪ የተደራጀ የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና ሂደትን በሚደግፉ የትንታኔ ጥያቄዎች ላይ መመሪያ ይሰጣል። ተዛማጅ ጥያቄዎችን እና ሂደቱን በተሻለ ሁኔታ ለማብራራት የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ችግርን እና ሊኖሩ የሚችሉ የእውቀት ክፍተቶችን ለይቶ የሙግት ስትራተጂን በማዳበር ረገድ አጋዥ ሊሆኑ ይችላሉ።

**የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ ማዕቀፍ (PAF) መሳሪያዎች፡ የጽንሰ-ሐሳብ መገናኛ መሰረታዊ ነጥብ (The Concept Matrix)**

ይህ መሳሪያ ቁልፍ የሆኑ የጥበቃ ችግሮችን ግልጽ በሆነ የግንኙነት መረብ ያቀርባል፡ ሀ) የጥሰት አይነቶች፣ ለ) የአለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ግንዛቤዎች፣ እና ሐ) ሰብዓዊ መብቶች

## የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ግብ እና ዓላማዎችን ማስቀመጥ


ቀጣዩ ሂደት የሙግት ስትራቴጂውን ማዘጋጀት ይሆናል። በተጠናቀሩ የሙግት ትንታኔዎች፣ የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔዎች እና ሌሎች ጠንካራ ማስረጃዎች ላይ በመመርኮዝ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በሙግት እና በዋና ግብነት ሊፈቱ የሚገባቸውን ልዩ የተጋላጭነት ጥበቃ ስጋቶችን መለየት እንችላለን።

የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና የችግሩን መንስዔዎች፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የተጋላጮች የአደጋ ስጋት፣ የችግሩ ሰለባዎች ማንነትን እና ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎችን፣ ተለይተው የታወቁ አግባብነት ያላቸው የአለም አቀፍ ህግ ጥሰቶች[7] እና ሌሎች ጉዳዮች ላይ አጠቃላይ ግንዛቤ እንዲኖር ያስችላል።



የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና ቅድሚያ የሚሰጣቸው የተጋላጭነት አደጋ ስጋቶችን ለመለየት እና ሙግትን ጨምሮ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ ስትራቴጅዎችን ለመንደፍ ይጠቅማል፡፡ እያንዳንዱ የትንተና ሂደቱ ውጤት (በምስል1.2 ላይ የቀረበውን የተጋላጮች ጥበቃ ትንተናዊ ማዕቀፍ ተከትሎ) ለሙግት ግብና ዓላማዎች የሚረዱ ማስረጃዎችንና ታሪኮችን ለማግኘት ይጠቅማል፡፡

**ምስል 1.2: የተጋላጮች ጥበቃ ትንተናዊ ማዕቀፍ (PAF) ትንተናዊ ድምዳሜዎች ቅደም ተከተል**




የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ግብና ዓላማዎች የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሹ የትኩረት ጉዳዮችን (ማለትም ትኩረት የሚሹ የተጋላጭነት ጥበቃ ስጋት አደጋዎች)፣ የመተግበር እድላቸው ከፍ ያሉትን ጉዳዮች የመለየት (ባለን አቅምና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት) እና የድርጅታችንን ልዩ ጥንካሬዎች ላይ መሰረት ያደርጋሉ። ይህም የሚከተሉትን ሊያሳይ ይችላል[8]:

| | |
|---|---|
| የሚለኩና ሊታዩ የሚችሉ ዓላማዎች | አገራዊ ፖሊሲዎችና ህጎች ላይ የተደረጉ ለውጦች |
| የሚለኩና አልፎ አልፎ ሊታዩ የሚችሉ ዓላማዎች | ተቋማዊ አቅም፣ ፍልስፍና ወይም አሰራሮች |
| ለመለካት የሚያዳግቱ፣ ለመታየት አዳጋች የሆኑ ዓላማዎች | አመካከትና እምነት እና/ወይም ተቋማዊ ባህል |

ከተጋላጮች ጥበቃ የአደጋ ስጋት አንጻር በሙግት ሊሳኩ ለሚፈለጉ ጉዳዮች የሙግት ግብና ዓላማዎችን ለማስቀመጥ ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።

| የተጋላጮች ጥበቃ አደጋዎች ምሳሌዎች | የሙግት ግብ እና ዓላማዎች |
| --- | --- |
| **ማፈናቀል እና/ወይም የግል ንብረት ውድመት**<br><br>*ከድርቅ ጋር በተያያዘ በሶማሊያ የሚኖሩ ዜጎችን በግዳጅ ማፈናቀል ሁለተኛ ደረጃ መፈናቀልን እየፈጠረ እና በአረጋውያን፣ ሴቶች እና ህጻናት ላይ ተመጣጣኝ ያልሆነ ተጽእኖ እያደረሰ ነው።.* | **ግብ** በአንድ የከተማ አካባቢ ተጨማሪ የግዳጅ መፈናቀልን ለማስቆም እና ለተጎዱ ማህበረሰቦች የእርዳታ እና የመብት አቅርቦትን ማጠናከር።<br><br>**አላማዎች**<br><br>➤ በተጨማሪ በማናቸውም ማፈናቀል ላይ ከንቲባው አፋጣኝ እገዳ እንዲሰጥ ማድረግ።<br>➤ የተከራዮችን እና መደበኛ ያልሆኑ ሰፋሪዎችን መብት የሚያጠናክር የፖሊሲ ለውጥ ለማራመድ።<br>➤ የሰብአዊ ድርጅቶች የተጎዱ አረጋውያንን፣ ሴቶችን እና ህጻናትን በሰብአዊ ርዳታ ውስጥ ማካተቱን ለማረጋገጥ።<br>➤ ከመባረር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመከታተል እና ለመመዝገብ ለቀጣይ የጥብቅና ማስረጃ መሰረት። |
| **የመንቀሳቀስ ነፃነትን የሚነኩ ህገ-ወጥ እንቅፋቶች ወይም ገደቦች እና የግዳጅ መፈናቀል**<br><br>*በብሔራዊ ባለስልጣናት የሚመራ የውስጥ ተፈናቃዮች (IDPs) ካምፕ የመዘጋቱ ሂደት የተፈናቀሉ ማህበረሰቦችን መብት አይቀበልም ወይም ዘላቂ መፍትሄዎችን አይደግፍም።* | **ግብ** ማንኛውም የካምፕ የመዘጋት ሂደት በተጎዱ ማህበረሰቦች መብቶች ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማረጋገጥ<br><br>**አላማዎች**<br><br>➤ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥን ለመደገፍ ከተጎዱ ማህበረሰቦች ጋር ትርጉም ያለው ምክክር ለማድረግ ከባለሥልጣናት መተማመኛ።<br>➤ የካምፕ መዘጋት ብሔራዊ እቅድ የመመሪያ መርሆችን ዋና ዋና ጉዳዮችን ያካተተ ለውጦችን ለማራመድ።<br>➤ በመብቶች ላይ የተመሰረቱ አካሄዶች ዘላቂ መፍትሄዎችን እና ኢኮኖሚያዊ ማገገምን እንዴት እንደሚደግፉ በአካባቢ እና በብሔራዊ ባለስልጣናት ውስጥ ግንዛቤን ማሳደግ። |
| **በጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት (GBV) እና የሀብት፣ እድሎች ወይም አገልግሎቶች ገደብ**<br><br>*የሴቶች የተጋላጮች ጥበቃ ሰራተኞች ከወንዶች ‘ጠባቂዎች’ ጋር መጎዳኘት ስለሚጠበቅባቸው የGBV አገልግሎቶችን በተናጥል ለማቅረብ አይችሉም፣ ይህም የሴቶች እና ልጃገረዶች ጥበቃን ይገድባል።* | **ግብ** የሴቶች ሰራተኞች ሙሉ እና ያልተገደበ ተሳትፎ የሚፈቅደውን ፖሊሲ በዲስትሪክት ደረጃ መከበራቸውን ለማረጋገጥ የማዕከላዊ ባለስልጣናት ቁርጠኝነትን ለማጠናከር።<br><br>**አላማዎች**<br><br>➤ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ያልተደናቀፈ የእርዳታ እና የተረፉ ሰዎች ጥበቃ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ የተጣሉ ገደቦችን በተመለከተ የፖሊሲ ለውጥን ለማራመድ።<br>➤ ተግባራትን በሚያከናወኑበት ጊዜ የሴት ሰራተኞችን ተሳትፎ የማረጋገጥ አስፈላጊነትን በተመለከተ ከዲስትሪክት ደረጃ ባለስልጣናት ጋር ግንዛቤን እና ድጋፍን ማዳበር።<br>➤ የሰብአዊነት ሰራተኞችን ጨምሮ የሴት ሰራተኞችን በነፃነት እንዲዘዋወሩ ለማድረግ ማህበራትን እና የሙያ ማህበራትን ማነቃቃት እና ማሰባሰብ። |

# የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ግቦችን እና ተዛማጅ ዓላማዎችን ማስቀመጥ

**የተጋላጮች ጥበቃ ግቦች እና ተዛማጅ ዓላማዎች** የተቀመጡት የነባር ስልቶችን እና/ወይም የማህበረሰብ ስትራቴጂዎችን፣ ማምጣት የተፈለገውን የተጋላጮች ጥበቃ ውጤት ትንተና ምላሽ፣ ተዛማጅ የህግ ማዕቀፎችን እና ስጋቶችን የመሳሰሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።

እነዚህ ዓላማና ግቦች ማምጣት በተፈለገው ለውጥ መሰረት የፖሊሲ (መቅረፅ፣ ማፅደቅ፣ ትግበራ እና/ወይም ክትትል)፣ ልማዶች፤ አመለካከቶች፤ ባህሪያት እንዲሁም ለውጡ በምን ደረጃ(ዎች)(ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ አገራዊ ወይም አለማቀፍ[9]) መካሄድ እንዳለበት የሚወስን መሆን አለበት።

**የሙግት ስትራቴጂ አጠቃላይ ዓላማ ወይም 'ግብ'** አጭር፣ አሳማኝ እና አበረታች መሆን አለበት። እኛ የምንፈጥረው ተጽዕኖ ውጤቱ በሰዎች ሕይወት ወይም በአካባቢያቸው መሻሻል ላይ ማተኮር አለበት።

ግቡ በተፅዕኖ እና በዘመቻ ስትራቴጂ የሚፈለገው ለውጥ ላይ አጠቃላይ አርዕስተ መግለጫ መስጠት አለበት።

የሙግት ስትራቴጂ መኖሩ ብቻ ሳይሆን - ለምሳሌ ሁሉንም የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች ከሚሸፍን የብዙ አመት ስትራቴጂ - አጠር ያለ ልዩ የሙግት ስትራቴጂ እና እቅዶች፤ የተጋላጮች ጥበቃ አጋሮች ጥረታቸው ላይ እንዲያተኩሩ እና ተግባሮቻቸውን እንዲያበዙ የሚያስችላቸው ሆኖ መቀረጹ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ የሙግት ስትራቴጂ በአንድ ቁልፍ 'አደጋ' ወይም ስጋት ላይ ብቻ ሊያተኩር እና የአጭር የጊዜ ገደብ ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌ የተጋላጮች ጥበቃ ስትራቴጂ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በሰሜን ኢትዮጵያ በአንድ የተወሰነ ግዛት ውስጥ በሚገኙ ካምፖች ውስጥ ታስረው የሚገኙ ተፈናቃዮችን እንዲፈቱ ባለስልጣናት ላይ ተጽእኖ ማሳደር ላይ ሊያተኩር ይችላል ወይም ስትራቴጂው በዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ምሥራቃዊ ግዛቶች ውስጥ ያሉትን የተፈናቃዮች ካምፖች በተመለከተ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ለውጥ ማምጣት ላይ ሊያተኩር ይችላል።

አንድ ስትራቴጂ በሁለት ወይም በሦስት ዓላማዎች ብቻ የተገደበ መሆን አለበት፡፡

| የሙግት ዓላማዎች የሚከተሉትን መሆን አለባቸው | | | |
|---|---|---|---|
| ግልጽ | ለክትትል ምቹ | ሊሳካ የሚችል | በጊዜ የተገደበ |
| በግልጽ የተቀመጠ፣ አሻሚ ያልሆነ፣ ውጤት ላይ ለማተኮር የሚያግዝ | የተሳካ መሆን አለመሆኑን ለመለየት የሚመች | በግልጽ በተቀመጠ የለውጥ ጽንሰ ሀሳብ[10] መሰረት፣ ባለው ሃብትና ጊዜ ውስጥ የታሰበውን ውጤትና ተጽዕኖ ለማምጣት የሚያግዝ | በተመጠነ ጊዜ ሊሰራ የመሚችል፣ ስትራጂው እየተፈጸመ ባለበት እንደየሁኔታው ሊሻሻል የሚችል |

## የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ዓላማ ምሳሌዎች

- የተጎዱትን ሰዎች ቅድሚያ መስጠት እና መብቶችን ለማንፀባረቅ መንግስት አዲስ የተፈናቃዮች ካምፕ መዝጊያ ፖሊሲ።
- መንግስት ከመጪው ምርጫ በፊት በካምፓላ ስምምነት መሰረት የተፈናቃዮችን ጥበቃ እና ድጋፍ የሚያበረታታ ረቂቅ ህግ እንዲያፀድቅ።
- እኤአ 2023 ለጋሾች ለአገራዊ የተጋላጮች ጥበቃ አካላት ተጨማሪ 15% ቀጥተኛ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጡ።
- አገር ውስጥ ላሉ የሰብዓዊ አድን ቡድኖች አዲስ የጥበቃ ስትራቴጂ ግቦችን፣ ኢላማዎችን እና ከግጭት ጋር ተያያዘው የሚመጡ ወሲባዊ ጥቃቶችን ለመቀነስ የተሰጡ ግብዓቶችን ማካተት።
- በተፈናቃዮች መካከል የሚከሰትን ያለ እድሜ ጋብቻን ለመለየት፣ መንግስት በማስረጃ የተደገፈ መረጃ እንዲሰበስብ እና ክስተቱንም ለመመዝገብ የሚያስችል ዘዴ እንዲዘረጋ።
- ከካምፓላ ስምምነት ጋር በተጣጣመ መልኩ ቢያንስ አስር አገራት የተፈናቀሉ ዜጎችን ጥበቃ እና እርዳታ የሚያበረታቱ ህጎችን እና ፖሊሲዎችን አውጥተው ተግባራዊ እንዲያደርጉ።
- የጥበቃ ስትራቴጂ ለሴቶች የተሻለ ጥበቃ ላይ ግልጽ ትኩረት ያደረጉ/ያካተቱ ግቦችን እና ኢላማዎችን ያካትታል፣ በተለይም በአገሪቱ ውስጥ ከግጭት ጋር ተያይዞ የሚመጡ ወሲባዊ ጥቃቶችን ለመቀነስ የተለየ አላማ/ግብ አለው።



*ሻፈቃ በፍልስጤም በሚገኝ መንደር የሴቶች ቡድን መሪ ናት። ፎቶ ኪራን ዶህረቲ (Kieran Doherty)*

ሞጁል 2

# የባለድርሻ አካላት ልዩታ፣ የሐይል ሚዛን ትንተና እና የለውጥ ፅንሰ-ሃሳብ (Theory of Change)

ከተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ችግሮች ከተለዩ እና ግብ እና አላማ ከተዘረዘረ ቀጣዩ ተግባር በጉዳዩ ድርሻ ያላቸውንና ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉ ባለድርሻ አካላትን መለየት ነው። በጉዳዩ ላይ ያላቸው ፍላጎትና ተፅዕኖም ሊተነተን ይገባል። እነዚህን እርምጃዎች በመከተል የሙብት ሙግት ዋና ዋና አላማዎችን መለየትና ማዘጋጀት ያላቸውን ተጽዕኖም በጥልቀት ለመመርመር ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ ውስብስብ የሆነ ችግርን በመፍታት ሂደት ለውጥ እንዴት ሊመጣ እንደሚችል ንድፈ ሐሳቡን መገንዘብ ይቻላል።

በእነዚህ እርምጃዎች የተጋላጮች ጥበቃ ዘመቻ ቁልፍ ኢላማዎች ሊመሰረቱ ይችላሉ። በተጨማሪም ከተጋላጮች ጥበቃ ጋር ተያይዞ የሚመጡ ስጋቶችን በተመለከተ እነዚህ ኢላማዎች ስላላቸው ተጽዕኖ እና ፍላጎት በጥልቀት ለመመርመር ያስችላል፡፡ እንዲሁም በዚህ ሂደት ውስጥ ውስብስብ ችግሮችን በመፍታት ሂደት ለውጥ እንዴት ሊመጣ ይችላል የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ በመመዝገብ ያስችላል።

የሙግት ጥረቶች በለውጥ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር፣ ጉዳትን መቀነስ እና በቀውስ ለተጎዱ ሰዎች ለውጥ ለማምጣት ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ። ይሁን እንጂ የለውጥ ሂደት በአብዛኛው ውስብስብና ያልተጠበቁ ውጤቶች የሚመጡበት ሂደት ነው። ስለሆነም ምን ማድረግ እና እንዴት ማድረግ እንደሚቻል በትክክል መወሰን አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ባለድርሻ አካላትን መለየት የሃይል ሚዛን ትንተና እና የለውጥ ፅንሰ-ሃሳብ የሙግት ጥረቶች ስትራቴጂያዊ ትኩረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ያግዛሉ፡፡

የለውጥ ፅንሰ-ሃሳብ በተለይ በታቀዱት ተግባራት እና በተቀመጡ ግቦችና ዓላማዎች መካከል ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል። እንደስትራቴጂ ልማት ሂደት መሰረታዊ አካላት ጥምረት ወይም የአጋሮችን ትስስር መፍጠር በጣም ፍሬያማ ተግባር ነው። ይህ ሁሉም አባላት በማን ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እንደሚሞክሩ፣ ማን እንደሚነካቸው እና ከጥበቃ አላማ ጋር በተያያዘ 'ለውጥ እንዴት እንደሚመጣ' የጋራ ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛል።

## የባለድርሻ አካላት ልዬታ እና የሃይል ሚዛን ትንተና

በአብዛኛው የባለድርሻ አካላት ልዬታ የሚካሄደው የሙብት ተማጋች ድርጅቶች ለማስተካከል የሚፈልጉትን 'ችግር ተመርኩዞ ነው። ይህ እንቅስቃሴ በችግሩ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ እና መፍትሄ መፈለግ የሚችሉ ባለድርሻ አካላት በጋራ እንዲሰሩ እድሎችን ይፈጥራል። የባለድርሻ አካላት ልየታ አብዛኛውን ጊዜ ከሃይል ጋር አብሮ የሚካሄድ ሲሆን እነዚህ ባለድርሻ አካላት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ የሚይዟቸው የተለያዩ ፍላጎት ወይም ተሳትፎ እና አርከን ይመረምራል። የባለድርሻ አካላት ልዬታ ለማካሄድ የመጀመሪያው እርምጃ ከሙግት ጋር በተያያዘ በሆነ መንገድ የሚዛመዱ ባለድርሻ አካላትን መዘርዘር ነው። እነዚህን ባለድርሻ አካላት እንዴት መለየት እና መገምገም እንደሚቻል ይገልጣል።

ባለድርሻ አካላትን በተዛማጅ ደረጃዎች ለመለየት (ማለትም በአካባቢያዊ፣ ብሄራዊ እና ዓለም አቀፋዊ) እና ተያያዥ የሀይል ሚዛን ትንተና ለማካሄድ የመጀመሪያው እርምጃ በተወሰነ መልኩ ከጥበቃ 'ችግር' ጋር የተያያዙትን ባለድርሻ አካላት መዘርዘር ነው፡፡ እነዚህን ባለድርሻ አካላት እንዴት እንደሚለዩ እና እንደሚተነተኑ እባክዎን በገጽ 72 ላይ ያለውን ኢጋዥ ቁጥር 3 ይመልከቱ።


ዝርዝሩ ከተሰናዳ በኋላ የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል የሚጫወተው ሚና ላይ ማብራሪያ ለመስጠት የተወሰነ ምርምር ማድረግ ያስፈልጋል። ይህ የሚደረገው እያንዳንዳቸው አቅም እና ፍላጎት ባላቸው ድርጅቶች፤ በተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ላይ በሚሠሩ ሰዎች እና ተባባሪዎች ጥምረት ነው። ባለድርሻ አካላት አቋማቸውን ሊቀይሩ ስለሚችሉ፣ መረጃ ሊወጣና ሌሎች ሲወጡ አዳዲስ ድርጅቶች ወደ መድረኩ ሊመጡ ስለሚችሉ የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል መረጃ በየጊዜው መገምገም ይኖርበታል።

የባለድርሻ አካላትን መረጃ በመመርመር ሂደት የእያንዳንዱን ባለድርሻ ግብ ወይም ዓላማዎች ለማሳካት እንዴት ሊረዳው እንደሚችል መጠየቅ ያስፈልጋል። በጉዳዩ ላይ ለመሳተፍ ምን ዓይነት ሀብት ወይም መረጃ ያስፈልጋቸዋል? እርምጃ እንዲወስዱ የሚገፋፋቸው ምንድን ነው? መልዕክታችንን ለምን ያዳምጣሉ? ይህን መረጃ ለመጠቀም አጋጣሚ የሚኖራቸው መቼ ነው? የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል።

| ማን እና እንዴት? | ምን? | ለምን? | መቼ? |
| --- | --- | --- | --- |
| የትኞቹ ድርጅቶችና ግለሰቦች? የሚወስኑት እንዴት ነው ወይም ተጽዕኖ እንዴት ያሳድራሉ? | ግባቸው ምንድን ነው? የተሳትፎ ደረጃቸውስ እስከ ምን ድረስ ነው? | ፍላጎታቸው እና የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው? | ቁልፍ ውሳኔ ግፊት የሚያሳድሩት መቼ ነው? |
| ➤ የመወሰን ወይም ተጳዕኖ የማሳደር ወይም ወሳኝ አካላትን ግፊት ማድረግ አቅም አላቸው?<br>➤ ማን ላይ ተጽዕና ያሳድራሉ? ማንስ ተጳዕኖ ያሳድርባቸዋል?<br>➤ እንዴት ይወስናሉ? | ➤ መፍትሄ ስለተፈለገበት ጉዳይ ያውቃሉ?<br>➤ ፍላጎታቸው ወይም ተሳትፎአቸው ምንድን ነው?<br>➤ ስለ ጉዳዩ ወይም አደጋው ያላቸው የእውቅና ደረጃ ምን ያህል ነው? | ➤ ለምን ይሳተፋሉ ወይም አይሳተፉም?<br>➤ ምን ያነሳሳቸዋል? በጉዳዩ ላይ አሁናዊ ወይም የወደፊት ፍላጎታቸው ምንድነው?<br>➤ ለምን ጉዳይ ይጨነቃሉ እና ለእነርሱ ዋጋ ያላቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? | ➤ ለውሳኔ አሰጣጥ ወይም ለተሳትፎ ወሳኝ ጊዜያት የትኞቹ ናቸው?<br>➤ እነርሱን ለማሳተፍ ልዩ እድሎች አሉ? |

በዚህ ሂደት ውስጥ **ሁለተኛው** ሂደት የሀይል ሚዛን ትነተና ማካሄድ ነው። ይህ የልዩታ ስራ ልምምድ የሁሉንም ተዋናዮች ፍላጎት ደረጃዎች ግልጽ ለማድረግ ከማስቻል በተጨማሪ የተካተቱትን የሀይል ሚዛን ትንተና ያሳያል። እንዲሁም የሙግት ጥረቶች ኢላማዎችን መለየትን ያመቻቻል። እነዚህ ከፍተኛ ተጽዕኖ እና ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው አካላት የመሆን አዝማሚያ አላቸው፣ ነገር ግን ልምምዱ ለማንኛውም የተሳካ ለውጥ እንዲመጣ ለማሳመን ወይም ከዋና \ዋናዎቹ ኢላማዎች መካከል ሊሆኑ የሚችሉትን አጋሮች ወይም አጥፊዎችን ለመለየት ጠቃሚ እድል ይሰጣል።

ምስል 2.1: **የሀይል ሚዛን ትንተና ስዕል**[11]



የትኛውም የባለድርሻ አካላት ልዩታ እና የሀይል ሚዛን ትንተና ልምምድ በቡድን ውስጥ አለመግባባቶችን እና ብዙ ውይይትን ያስከትላል። ይሁን እንጂ የተለያዩ አጋሮችና ባለድርሻ አካላት ስልጣንና አቋማቸውን መሰረት በማድረግ ያ እይታዎቻቸውን ማምጣት ስለሚያስችል ይህ እጅግ ጠቃሚ ሂደት ነው።

የመጨረሻው ትንታኔ እነዚህን የተራራቁ አመለካከቶችን የሚያንፀባርቅ መሆን አለበት። የባለድርሻ አካላት ፍላጎት እና ስልጣን በጊዜ ሂደት ስለሚለዋወጥ ይህንን ተግባር በየጊዜው ማከናወን አስፈላጊ ነው። የመጨረሻው ጠቃሚ ምክር ይህንን ተግባር በተቻለ መጠን ግልጽ ማድረግ ነው። ለአብነት ያህል የመንግስት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ጥቅምና ተፅእኖ እንደ አንድ አድርጎ ከመተንተን ይልቅ በየሚኒስቴር መስሪያ ቤቶቹ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ የስራ ክፍሎች ወይም የውሳኔ ሰጪዎችን አቋም መፈተሽ እና መመልከት የበለጠ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ዒላማዎችን እና ድርጊቶችን በሚተነትኑበት ጊዜ ተሟጋችነት ሁልጊዜ በአውድ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ድርጊቶቹ እራሳቸው ከሌሎች ዘመቻዎች ሊደገሙ ቢችሉም እንኳ ሁልጊዜም ከአካባቢው አውድ እና ከዒላማዎች ጋር መጣጣም አለባቸው። ይህ የሙግት ጥምረት ጥንካሬ የሚሰማበት ቁልፍ እርምጃ ነው። በአቨርሲስ ደቨሎፕመንት ኢንስቲትዩት(Overseas Development Institute (ODI))[13] በሰብዓዊነት ፖሊሲ ቡድን ጥናት እንደተገለጸው ጥምረቱ ሀገራዊ ተዋናዮችን ጨምሮ የተለያዩ ተዋናዮችን የማሰባሰብ፣ የባለድርሻ አካላት ልየታ እና የሃይል ሚዛን ግምገማ፣ ባህል አገናዛቢ፣ የተለየ እና ተዛማጅነት ያለው የመሆን እድላቸው ሰፊ ነው።

## የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት የትኩረት ዒላማዎች

እያንዳንዱ የሙግት ስልት ልዩ እና የተስተካከለ መሆን ያለበት ቢሆንም የጥበቃ ሙግት አንዳንድ የተለመዱ አላማዎች በዚህ ክፍል ውስጥ ጠቅለል ተደርጎው ተገልፀዋል። የሙግት ዒላማ ከሚሆኑት አካላት መካከል አብዛኞቹ ከአካባቢ ባለ ሥልጣናት አንስቶ እስከ ማህበረሰብ የሃይማኖት መሪዎችና የታጠቁ ቡድኖች አባላት ድረስ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌሎች ደግሞ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ሀገራት አንስቶ እስከ ዓለም አቀፉ ሰብዓዊ እርዳታ ሥርዓት መሪዎች ድረስ ዓለም አቀፋዊ ሊካተቱ ይችላሉ።
ከሁሉም በላይ በግጭት የተጎዱ ግለሠቦች፣ ማህበረሰቦች፣ እና የሲቪል ማህበረሰብ ተወካዮች ከሙግት ጋር በተያያዘ የሚጫወቱት ሚና እውቅና ሊሰጠው እና የባለድርሻ አካላትን ልየታ ለማውጣት እና ተዛማጅ የመግቢያ ነጥቦችን እና የተፅዕኖ ሰንሰለቶችን ለመረዳት በሚደረገው ጥረት ግንባር እና ማእከል መሆን አለበት።

ከለጋሾች፣ ከሰብዓዊ ድጋፍ ቡድን (humanitarian country team (HCTs)) እና አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት አያያዝ ዘዴዎች ጋር ግንኙነት ማድረግ በተመለከት ለበለጠ መረጃ የተለያዩ ግብአቶች በማመሳከሪያው ክፍል ውስጥ ተካትተዋል።

በአካባቢም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉ ሃላፊዎችና ባለስልጣናት ጋር መተባበር ለአብዛሀኛው የሙግት ጥረት ወሳኝ ግብዓት ነው። ይህም በዓለም አቀፍ ሕግ በተደነገገው መሠረት ሰላማዊ ሰዎችን ከጦር መሣሪያ ግጭት የመጠበቅ ዋነኛ ኃላፊነት የሚሸከመው መንግሥት መሆኑን ያሳያል። በአካባቢም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ ካሉ ሃላፊዎችና ባለስልጣናት ጋር መተባበር ለአብዛሀኛው የሙግት ጥረት ወሳኝ ነገር ነው። ይህም በዓለም አቀፍ ሕግ በተደነገገው መሠረት ሰላማዊ ሰዎችን ከጦር መሣሪያ ግጭት የመጠበቅ ዋነኛ ኃላፊነት የሚሸከመው መንግሥት መሆኑን ያሳያል።

ከዓለም አቀፍ የሕግ ግዴታዎች ጎን ለጎን፣ ባለስልጣናት የራሳቸውን ዜጎች እንዲጠብቁ አስፈላጊ የሆኑ ግዴታዎችና ኃላፊነቶች እንዲሁም የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሞራል ግዴታዎችም አሉ።

የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የህግ ማዕቀፎችን መመርመር መንግስታት ስለህጋዊ ግዴታዎቻቸው እና ቃል ኪዳናቸው ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያስችላል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ውሳኔዎች እንዴት እንደሚተገበሩ ምክረ ሃሳብ ለማምጣት የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን፣ በተለያየ ደረጃ የተመረጡ ተወካዮችን፣ ወይም የተወሰኑ ሚኒስትሮችን፣ መሥሪያ ቤቶችን እና የመንግሥት ሰራተኞችን ዒላማ ማድረግን ሊጨምር ይችላል።

የአካባቢ ፖሊስ መኮንኖች ወይም የመንግሥት ሠራተኞች በአንድ በኩል የመንግሥት ተወካዮች በተመሳሳይ ጊዜም የማኅበረሰቡ አባላት ሊሆኑ ይችላሉ። የአካባቢ እና የማህበረሰብ ጥበቃ ቡድኖች እና ኮሚቴዎች በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ማድረግ ከሚችሉ ግለሰቦች ጋር የማህበረሰብ እና የቤተሰብ አካላት ጋር ግንኙነት አላቸው። ከባለስልጣናት እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ግልጽ የሆኑ መርሆች እና የአደጋ መከላከያ እቅዶችም መዘጋጀትም አለባቸው[14]።

እንደ ሀገራዎ የስራ ሃላፊዎች ሁሉ የታጠቁ ቡድኖችም በማኅበረሰብና በግለሰብ ላይ፤ ፖሊሲዎች ላይ ቀጥተኛ ተጽዕኖ ያላቸው በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ ቁልፍ ዒላማ ናቸው። ከታጠቁ ቡድኖች ጋር ድርድር በማድረግ ልዩ ልዩ ልምድ ያላቸው ድርጅቶች ጠቃሚ ማስተዋልና ሃሳብ ሊሰጡ ይችላሉ።ኦቨርሲስ ድቨሎፐመንት ኢንስቲትዩት (Overseas Development Institute (ODI በቅርቡ ዓለም አቀፉን የቀይ መስቀል ኮሚቴ (ICRC) ምርምርና አቀራረብ ከታጠቁ ቡድኖች ጋር በመገምገም ዓለም አቀፍ ሰብዓዊነት ሕግ (IHL) እንዲከበር ለማበረታታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ከመረመረ በኋላ በማህበራዊ ደንቦች እና እሴቶች ላይ በተመሰረቱ ሰፋፊ ክርክሮች ህጉን ማሟያ የማድረግን አስፈላጊነት አሳይቷ።[15]

በተጨማሪም ግኝቶቹ የመንግሥትም ሆነመንግሥት ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች እንዴት እንደሚደራጁ፣ እንዴት እንደተደራጁ እና እንዴት በተሻለ ሁኔታ ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚችሉ የመመርመርን አስፈላጊነት ጎላ አድርገው ጠቅሰዋል። በተጨማሪም ጄኔቫ ኮል (Geneva Call) ከታጠቁ ቡድኖች ጋር መተባበርን ለመምራት የሚረዱ የተለያዩ አጋዦች አሉት።[16] በአንዳንድ ሁኔታዎች የተወሰኑትመንግሥታዊ ያልሆኑ ታጣቂ ቡድኖች ከአሸባሪ ድርጅቶች ጎራ የተመደቡበት ሁኔታ ያለ ሲሆን ይህም የሚያስከትለውን አደጋ (በተዘዋዋሪም ቢሆን) እና እነዚህን አደጋዎች ለመቆጣጠር የሚያስችሉትን መንገዶች ለይቶ ለማወቅ እና ምን ዓይነት ተጽዕኖ ማሳደር እንደሚቻል ለመገምገም የተሟላ የአደጋ ምርመራ መደረግ ይኖርበታል።

ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል አገሮች ጋር የ ሙግት (አድቮካሲ) ስራ መስራት ከብዙዎቹ የሙግት ስልቶች አንዱ ወሳኝ ነገር ነው። ለጋሾች ጥብቅና በመቅረብ፣ ቁልፍ የሆኑ መንግሥታትን ስለ ጥበቃ ጉዳይ ፈታኝ ሁኔታዎች በቂ እውቀትና ትርጉም ያለው ውይይት ለማድረግ፣ ግልጽ ውይይቶችን ለማነሳሳት እና በጥረቶች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር ድጋፍ ለመስጠት ሊረዳ ይችላል። በተመሳሳይም ሌሎች መንግሥታት በተለያዩ ደረጃዎች ከመንግስት የስራ ሃላፊዎች ጋር ሊኖራቸው የሚችለው ልዩ ዝምድናና ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ከአባል ሀገራት ጋር የሚደረግ የጥብቅና ማሟያ ለአገርና ለአካባቢ ባለስልጣናት አስፈላጊ ማሟያ ነው። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ በተለይ የተባበሩት መንግሥታት የደኅንነት ምክር ቤት (UNSC) ቋሚና ቋሚ ካልሆኑ አባላት ጋር መተባበር በተለይ ከዚህ ምክር ቤት (UNSC) ውሳኔዎች፣ በሰላም ጥበቃ ድንጋጌዎች ወይም በቅጣት አገዛዞች ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር በሚሞክርበት ጊዜ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ለአብዛኞቹ የመብት ሙግት ድርጅቶች ከለጋሾች ጋር መተባበር ወሳኝ ነገር ነው። ለጋሾች የሙግት አላማዎችን ፖሊሲዎችንና ልማዶችን የመወሰን እና በውሳኔ ሰጪዎች ላይ በተወሰነ መጠን ተጽዕኖ የማሳደር ችሎታ አላቸው። የተሟጋች አጋሮች ብዙውን ጊዜ አንዳንድ ፖሊሲዎችንና ልማዶችን በተመለከተ የመወሰን ወይም በኃላፊነት ተሸካሚዎች ወይም በሌሎች ተያያዥነት ባላቸው ውሳኔ ሰጪዎች ላይ በተወሰነ መጠን ተጽዕኖ የማሳደር ችሎታ አላቸው። ስለዚህ በየጊዜው የተሰበሰቡ መረጃዎችን የመብት ሙግት ላይ ስለሚጋረጥ አደጋዎች የፕሮግራም ፍላጎቶች እና ስላለው የገንዘብ ክፍተት ለለጋሾች ማጋራት በጣም አስፈላጊ ነው። አንዳንድ አለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ሀገራት ላይ በዋና ከተሞች ውስጥ በሚገኙ ለጋሾች በኩል ተጽእኖ ማሳደር ቢችሉም፣ አብዛኛዎቹ የጥበቃ አካላት በኤምባሲዎች እና ለተልእኮ በመስክ ላይ ያሉ አካላትን ይጠቀማሉ፡፡

የበጀት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የፕሮግራም ጉዳዮችን ጨምሮ በለጋሽ ኤጀንሲዎች ውስጥ ውሳኔዎች እንዴት እንደሚደረጉ መረዳት የጥበቃ አካላት ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ተሟጋቾች ጥረታቸውን ማስተካከል ይችላሉ። የገንዘብ ድጋፍ ወይም ለጥበቃ ጉዳይ ፖለቲካዊ ድጋፍ ከጠፋ፣ ከሌሎች ችግሮች /ተግዳሮቶች መካከል የመጠባበቂያ ጊዜ እቅዶችን ማዘጋጀት ይችላሉ።

በሰብዓዊ መብት ላይ ያተኮሩ ስልቶች እና ድርጅቶች በአንድ ሀገር ውስጥ የመብት ሙግት (አድቮኬሲ) ተግባራትን ለመስራት እና የሰብዓዊ ድጋፍን ለማድረግ ወሳኝ አጋርነቶችን እና መንገዶችን ሊያመላክቱ ይችላሉ። በሰብዓዊ መብቶች ምክር ቤት (HRC) የተፈጠሩትን ልዩ ልዩ የአሰራር ሂደቶችን ጨምሮ የሰብዓዊ መብት ባለሙያዎች የሙግት ጉዳዮችን ለመፍታት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፤ የጥበቃ ተሟጋችነት ኢላማ ወይም አጋር ሊሆኑ ይችላሉ፥ እንዲሁም በሰብዓዊ ቀውሶች በተጎዱ ሰዎች ላይ በተለይም በጣም ተጋላጭ በሆኑ ቡድኖች ላይ ግንዛቤን ለማሳደግ እንደ ጠቃሚ ጣቢያ ሆነው ያገለግላሉ። እያንዳንዱ የጥበቃ ባለድርሻ አካላት የጥበቃ ኔትዎርኮችን በማስፋት በተለያዩ የግል እና ህዝባዊ መንገዶች በየአካባቢው፣ በሀገር አቀፍ እና በአለም አቀፍ ደረጃ የጥበቃ ቅስቀሳን ለማስፋፋት ከሰብዓዊ መብት ተዋናዮች ጋር ስትራቴጂያዊ በሆነ መንገድ መስራት አለባቸው።

የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ከሚያደርጋቸው መደበኛ ስብሰባዎች በአንዱ (በዓመት ሦስት ጊዜ የሚደረግ ነው) ሚስጢራዊነትን በጠበቀ መልኩ መሳተፍ፣ ወይም አስቸኳይ የሰብዓዊ መብት ጉዳዮች ልዩ ስብሰባ ላይ በግልጽ መሳተፍ፣ ድምጽን ለማሰማት ዕድሎችን ሊሰጥ ይችላል። ተሟጋቾች የመብት ጥሰት ጉዳዮችን በቀጥታ ከሚመለከታቸው አካላት እና ከየሶስተኛ ወገን  አባል ሀገራት ጋር እንዲያነሱ ያስችላል፥ እንዲሁም ሁሉን አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ግምገማ(Univresal Persiodic Review) ግልጽ በሆነ የህዝብ መድረክ ላይ የመብት ጥሰት ጉዳዮች ላይ ያሉ ችግሮችን ለማንሳት እድል ሊፈጥር ይችላል፣ እንዲሁም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ በቀጥታ ከሀገራት ጋር ለመነጋገር እድል ይሰጣል።

በተጨማሪም የሰብዓዊ መብት ስልቶች ከመንግስት ጋር ለሚደረጉ ሙግቶችን ለመደገፍ እና በሰብአዊ መብቶች ላይ ሕጎቻቸውን እና ፖሊሲዎቻቸውን በማዘጋጀት እና በመተግበር ላይ ያሉ የተፈናቃዮችን ጥበቃን በተመለከተ ለምሳሌ የሀገር ውስጥ መፈናቀል የአፍሪካ ህብረት የካምፓላ ስምምነትን እንደአስፈላጊነቱ) ወደ ሀገራዊ ህግ ማምጣት ላይ ሊያግዝ ይችላል።

በተጨማሪም የሰብዓዊ መብት ስልቶች ከመንግስት ጋር ለሚደረጉ ሙግቶችን ለመደገፍ እና በሰብዓዊ መብቶች ላይ ሕጎቻቸውን እና ፖሊሲዎቻቸውን በማዘጋጀት እና በመተግበር ላይ ያሉ የተፈናቃዮችን ጥበቃ በተመለከተ ለምሳሌ የሀገር ውስጥ መፈናቀል የአፍሪካ ህብረት የካምፓላ ስምምነትን እንደአስፈላጊነቱ ወደ ሀገራዊ ህግ ማምጣት ላይ ሊያግዝ ይችላል። የሙግት ጥረቶቹ የዜጎችን ጥበቃ ለማጠናከር እና በመርህ ላይ የተመሰረተ ሰብዓዊ እርዳታ ለተጎዱ ህዝቦች መድረሱን እና ለፍላጎታቸው ምላሽ መስጠትን ለማረጋገጥ ያለመ ነው።

በዋናነት ትኩረት ከሚደረግባቸው አካላት መካከል የአደጋ ጊዜ እርዳታ አስተባባሪ (ERC)፣ የድንገተኛ አደጋ ዳይሬክተሮች (EDG) የተወካዮች ቡድን፣ እና ዘ ኦፕሬሽናል ፖሊሲ ኤንድ ኣድቮኬሲ ግሩፕ (OPAG) ይካትታሉ። በሀገር አቀፍ ደረጃ በሰብዓዊ እርዳታአስተባባሪ ቡድን (Humanitarian Coordinator team (HCT) የተቋቋመውና የሚመራው ፣ በሙግት ላይ ለሚደረጉ ጥረቶች ስትራቴጂያዊ አጋር ሊሆን ይችላል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ቢሮ ሰብዓዊ መብት ላይ ለሚደረጉ የጥበቃ ጥረቶች፤ የጥበቃ አጀንዳዎች እና የ IASC ጥበቃ ፖሊሲን ለማስፈጸም ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ ተብሎ ይጠበቃል።[21]

*ምስል 2.2:* **የአካባቢ እና ሀገራዊ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ኢላማዎች**




**ሚኒስቴር መ/ቤቶች**

- የተጋላጮች ጥበቃ ፖሊሲዎችን፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች፣ የአቀራረብ ዘዴዎችን እና በጀቶችን እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ማዘጋጀት
- የትኩረት አካላት ሚንስትሮችን፣ወሳኔ ሰጪዎችን፣ኤክስፐርት የመንግስት ሰራተኞችን ያካትታ

**የተመረጡ የህዝብ ተወካዮች**

- በሚወጡ ህጎች፣ፖሊሲዎች፣ በጀቶች እና መንግስት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ላይ ድምፃቸ መስጠት/መቃወም ወዘተ
- የትኩረት አካላት የፓርላማ አባላትና ሰራተኞቻችቸው፣ የልዩ ህግጋት ስፖንሰሮች፣የኮሚቴ አባላት ወዘተ ያካትታሉ።

**የሲቪል ማህበረሰብ**

- ከሰብአዊ መብቶችና ማህበራዊ ፍትህ ጋር የተያያዙ ትረካዎችን፣ የሙግት ትኩረቶችንና ጥረቶች ላይ ጫና ማሳደር።
- የትኩረት አካላት አክቲቪስቶችን፣ ጥምረቶችን፣ የሰብአዊና ሴቶች መብት ተሟጋቾችን፣ የሃይማኖት ድርጅቶችን፣ የወጣት አደረጃጀቶችን፣ ማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ወዘተ ያካትታል።

**ኢ/መንግስታዊ የታጠቁ ቡድኖች**

- ሲቪሊያን የሚኖሩባቸው አካባቢዎችን የሚቆጣጠሩ ወይም ከፍተኛ ጫና የሚያሳድሩ፣ አንዳንዴም ፍትህና አገልግሎት የሚሰጡ።
- የትኩረት አካላት ትዕዛዝ ሰጪ የሆኑ አባላት፣ ጫና የሚፈጥሩ አካላት ማለትም የማህበረሰብ አካላትን እንደ መግቢያ በመጠቀም ጨምሮ።

**የአካባቢ ባለስልጣናት**

- ጸጥታ ማስከበርን ጨምሮ ፖሊሲዎችን ማስፈጸምና አገልግሎት መስጠት።
- የትኩረት አካላት ከንቲባዎችን፣ አማካሪዎችን፣ ዳኞችን፣ የጤና ባለሙያዎችንና የማህበራዊ ባለሙያዎችን ወዘተ ያካትታል።

*ምስል 2.3: አካባቢያዊና ሀገራዊ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት የትኩረት አካላት*




### የተመድ ጸጥታው ምክር ቤትና አባል ሀገራት

- የጸጥታው ም/ቤት ውሳኔዎች ላይ መወሰን ፣ የአለም ወንጀለኞች ፍ/ቤት ሪፈራሎች፣ የማዕቀብ ሥርዓቶች፣ የሰላም ማስከበር ግዴታዎች ወዘተ።
- የትኩረት አካላት በ ኒው ዮርክ ውስጥ የሚገኙ የአባል ሀገራት ቋሚ ተልእኮዎች፣ ቋሚ እና ተዘዋዋሪ የፀጥታው ምክር ቤት አባላት፣ ባለሀብቶች እና የኤክስፐርት ቡድኖች፣ ወዘተ ያካትታሉ።

### የኢንተር ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ (IASC)

- ለሰብአዊ እርዳታ ምላሽ የሚሆኑ ፖሊሲዎችን እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች ማዘጋጀት እና ግብአቶችን ማሰባሰብ
- የትኩረት አካላት ERC, የተወካዮች ቡድን፣ የአደጋ ጊዜ ዳይሬክተሮች ቡድን፣ እና የድርጊት ፖሊሲና የሙግት ቡድኖችን ያካትታል።

### የሰብአዊ መብት ጥበቃ መንገዶች

- ሰብአዊ መብቶችን መከታተል እና ሪፖርት ማድረግ፣ ልዩ ልዩ አሰራሮች፣ የሥልጣን ባለቤቶች፣ UPR እና HRC መድረኮችን ያጠቃልላል።
- የHRC ክፍለ-ጊዜያት እና የውሳኔ ሃሳቦች፣ የባለስልጣናት ሀገር ጉብኝት እና ዘገባዎች፣ የ UPR ሪፖርቶችን ወዘተ ወርቃማ እድሎች ናቸው።

### ረጂ ድርጅቶች

- ለልማት እና ለሰብአዊ ርዳታ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የገንዘብ ድጋፍ ማዘጋጀት እና መተግበር።
- የትኩረት አካላት በሀገር አቀፍ እና በካፒታል ደረጃ የአለም አቀፍ ለጋሾች ተወካዮች እና ለጋሽ ፈንዶችን ያካትታሉ።

### አህጉራዊ አካላት

- የኢኮኖሚ ውህደትን እና ልማትን፣ ሰላምን እና ደህንነትን፣ሰብአዊ መብቶችን ወዘተ ለመደገፍ ያለመ።
- የትኩረት አካላት የአፍሪካ ህብረት፣ ASEAN፣ LAS፣ OAS፣ PIF ወዘተ ያጠቃልላል.።

### ከመገናኛ ብዙሃን ጋር በጋራ መስራት

የመገናኛ ብዙሀን የማንኛውም የባለድርሻ አካላት ልዩታ እና የስትራቴጂ ልማት ሂደት ውስጥ መካተት ያለባቸው ወሳኝ አጋሮች እና ባለድርሻ አካላት ናቸው፡፡ መገናኛ ብዙሀን ተፅዕኖ የመፍጠር አቅም በዋነኛነት የሙግት መልእክቶችን ለህዝብ እንዲደርሱ በማድረግ ወይም ውሳኔ ሰጪ አካላት ላይ ተጽእኖ መፍጠር እና በምርመራ ጋዜጠኝነትም ጭምር ውሳኔ ሰጪ አካላትን በህዝብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

ከቁልፍ ጋዜጠኞች ጋር መልካም ግንኙነት መገንባት በሰብዓዊ እና ጥበቃ ጉዳዮች ላይ በመገናኛ ብዙሃን አጋሮች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲኖርና የጥበቃ ዓላማዎችን ለመደገፍ ሚዲያን እንዴት እና መቼ ለመጠቀም እንደሚቻል የተሻለ የጋራ ግንዛቤን ለመፍጠር ይረዳል። የተለያዩ የሚዲያ አካላትን ያካተተ የባለድርሻ አካላት ልዩታ፤ የተለያዩ የኤዲቶሪያል መስመሮቻቸውን በመተንተን እና በጥበቃ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አቋም በመረዳት የትኛዎቹ የሚዲያ አካላት አጋር ሊሆኑ እንደሚችሉ ለመለየት ይረዳል።

ጋዜጠኞች እና የሚዲያ ተቋማት ሙያዊ የሥነ ምግባር ደንብን የሚያከብሩ ጠቃሚ አጋሮች ቢሆኑም ተሟጋቾች ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በአግባቡ በመገምገም እና  ማንም ላይ ጉዳት እንዳይደርስ መስራት (Do no harm) በሚለው መርህ ላይ በመመስረት የሚዲያ ተሳትፎን የተስተካከለ አካሄድ ማረጋገጥ አለባቸው።

ከሚዲያ ተሳትፎ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተግዳሮቶችን ከግምት ውስጥ ስናስገባ፣ የተጋላጮች ጥበቃ ባለድርሻ አካላትም በጣም ሚስጥራዊነት ባላቸው ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን ሊሳተፉባቸው የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች አሉ። ከነዚህም መካከል፡

- ስለ ቁልፍ የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች እና በሰዎች ላይ ስለሚኖረው ተፅዕኖ በተመለከተ ከመዝገብ ውጪ'ተጨማሪ መግለጫ እና ትንታኔ 'ለሚታመኑ ጋዜጠኞች መስጠት ያስፈልጋል። ይህ በተለይ ጋዜጠኞች ወደ አንድ የተወሰነ አካባቢ መድረስ በማይችሉበት ጊዜ እና የተጋላጮች ጥበቃ አካላት ስለ አንድ ጉዳይ የተለየ ሃሳብን ለማራመድ በሚሞክሩበት ጊዜ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።
- አሳሳቢ ሁኔታ ሲከሰት የዚህን መረጃ ምንጭ እንዴት እንደሚጠቅስ ግልጽ በሆነ ስምምነት ላይ በመመስረት ስም-አልባ (anonymous) ጥቅስ ለጋዜጠኛው ማቅረብ ይቻላል። ይህ ሊቀረጽ የሚችለው "አንድ የሰብዓዊ ድጋፍ ሰራተኛ እንደተናገረው ተፈናቃዮች በነፃነት መንቀሳቀስ እና የአካባቢ ገበያ እና መሰረታዊ አገልግሎቶችን ማግኘት አልቻሉም። ይህም የምግብ አቅርቦት እጦት እየጨመረ እና ሊታከም የማይችል በሽታን እያስከተለ ነው"። በሚል ኢሆን ይችላላ። ማንኛውም አመላካች የሚሆኑ ገላጭ ቃላትን በማስወገድ ጥንቃቄ ማድረግ።
- በሀገር ውስጥ፣ በክፍለ አህጉር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ በህዝብ ተቀባይነት ያላቸውን (የቀድሞ የመንግስት ተወካዮችን፣ ምሁራንን እና የፖሊሲ ተመራማሪዎችን ሊያካትት ይችላል) አጋሮችን መለየት እና በመገናኛ ብዙሃን ቁልፍ መልዕክቶች እና ምክሮችን እንዲጽፉ መደገፍ፡፡
- ስለ አንድ ሁኔታ በቀጥታ ከተጎዱ ሰዎች መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ፕሮጀክት ጣቢያዎች ወይም ለመድረስ አስቸጋሪ አካባቢዎች የሚዲያ ጉብኝቶችን ማመቻቸት።

በመጨረሻም ከተለመዱ አሰራሮች ውጭ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም ለተለምዷዊ ታዳሚዎች ለሙግት ጥረቶች የበለጠ አስቸጋሪ ሊሆኑ ቢችሉም ፈጠራ በተሞላባቸው አካሄዶች እና ከተለያዩ ተዋናዮች ጋር በመተባበር ተጽዕኖን ለመፍጠር ይቻላል። የሶስተኛ ወገን ሃገራት ጨምሮ አማላጆችን ወይም ሶስተኛ ወገኖችን መጠቀም ትኩረት ማድረግ በተፈለገው ዒላማ ላይ ተጽዕኖ ለማድረግ አዳዲስ እድሎችን ሊፈጥር እና እንዲሁም አደጋዎችን ለመቀነስ ይረዳል።

እንደዚሁም እንደ የሃይማኖት መሪዎች፣ አርቲስቶች እና የማህበራዊ ሚዲያ ተጽእኖ ፈጣሪዎች ወይም የግሉ ሴክተር ባለድርሻ አካላት ጋር መገናኘት የጥበቃ ውጤቶችን ለመደገፍ እና የተለያዩ 'የመግቢያ ነጥቦችን' ሊያመጣ ይችላል።

# የለውጥ ጽንሰ-ሀሳብ (theory of change) የማዳበር አስፈላጊነት

የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብባለድርሻ አካላት ሊከተሉት የሚፈልጉትን የለውጥ መንገድ በሰፊው የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ ነው። አብዛኛዎቹ የፕሮጀክት ንድፎች (ፕሮፖዛሎች)፣ የመንግስት ፖሊሲዎች እና የሙግት (አድቮኬሲ) ስትራቴጂዎች የለውጥ ንድፈ ሃሳቦችን ይይዛሉ።

ይህ ጠቃሚ መሳሪያ (tool) የሚወሰዱ እርምጃዎችን ዝርዝር እቅድ ለማውጣት እና የእንቅስቃሴ አጋሮች ለማሳወቅ፣ የሙግት እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እና ግምገማ ለማድረግ (M&E) ግልፅ መሰረት እንዲኖራቸው ያስችላል። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ የማጎልበት ልምድ ከጥበቃ ጥምረት አባላት ጋር የጋራ ተነሳሽነት ለመፍጠር እና የጋራ ባለቤትነትን ለመፍጠር አስተዋፅኦ ያበረክታል።

የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብን ለማሳየት በመደበኛነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ብዙ ንድፈ ሃሳቦች አሉ። ንድፈ ሃሳቡ ምንም ይሁን ምን የማንኛውም የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ በጣም አስፈላጊ ገጽታዎች ግልጽ እና ወጥ የሆኑ ናቸው።

የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብን በተሻለ መልኩ ለማቅረብ ከሁሉ የተሻለው መንገድ ሁሉንም ባለድርሻ አካል (ከውስጥ እና ከውጪ) ማማከር እንዲሁም ለተለያዩ ተመልካቾች የተለያዩ ስሪቶችን ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## የለውጥ ጽንሰ-ሐሳብ ቀረጻ ደረጃ በደረጃ

**አማራጭ 1**

የለውጥ ጽንሰ-ሐሳብ ንድፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሾችን ማሰባሰል እና መጻፍን ያካትታል።

1. አጠቃላይ ለማምጣት የሚፈለገው ለውጥ ምንድን ነው?
2. የአውድ ቅድመ-ሁኔታዎች ምንድን ናቸው?
3. ተፅዕኖ ለመፍጠር ያደረጋችሁት አስተዋፅኦ ምንድን ነው?
4. ያልተጠበቁ ውጤቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
5. ያለው እድገት ምን ይመስላል?
6. ግኝቶቹ እንዴት ይቀጥላሉ?

**አማራጭ 2**

- በዚህ የዝግጅት ሂደት ላይ በቀኝ በኩል ባለው ወረቀት ላይ ያሉትን አላማዎች እና በግራ በኩል ያሉትን ተዋናዮች/ባለድርሻ አካላት ዝርዝር ይፃፉ።
- እያንዳንዱ አላማ ባሻገር ቀስት በመሳል በግራ በኩል ማን ለዓላማው መሳካት ምን ማድረግ እንዳለበት ያመልክቱ።
- ተጨባጭ ወይም ተግባራዊ ያልሆኑ ድርጊቶችን አስወግዱ። አንድ በአንድ በግራ በኩል በተዘረዘሩት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ይፃፉ, በመቀጠልም በተጽእኖው ድርጊት እና በስሙ መካከል ያለውን ቀስት ይሳሉ.
- ትርጉም የሚሰጥ ካርታ እስኪታይ ድረስ ሂደቱን በተለያዩ መንገዶች ይቀጥሉ።
- ከዚያ በመነሳት ሊወስዷቸው የሚገቡትን እርምጃዎች መወሰን ይችላሉ።

ጥሩ የሚባል የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ እንደ የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና፣ ምርምር፣ ግምገማዎች፣ የጥበቃ ጣልቃገብነትን የሚደግፉ ነባር ሰነዶች፣ ተዛማጅ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞች እና ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ ነው። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ ረቂቅ ላይ የሚሳተፉትን ቁልፍ ባለድርሻ አካላት መለየት አስፈላጊ ሲሆን፣ መቼና እንደት በተሻለ ሁኔታ መሳተፍ እንዳለባቸው መወሰን (ለምሳሌ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብን በጋራ መንድፍ፣ ከመጀመሪያው ረቂቅ በኋላ ምክክር ማድረግ) የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችን፣ የተገለሉ ቡድኖችን፣ የአገሬው ተወላጆችን፣ በሴቶች የሚመሩ እና በወጣቶች የሚመሩ ድርጅቶችን፣ እና የሀገር ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ማካተት ጠቃሚ እና ተፅዕኖ ያለው የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ ለመቅረጽ ያግዛል።

የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ የተለያዩ አመክንዮአዊ ማዕቀፍ (logframe) በመፍጠር ሊሻሻል ይችላል። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ በስትራቴጂክ ደረጃ ትልቁን ምስል ሲሰጥ፣ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ አመክንዮአዊ ማዕቀፍ የተጋላጮች ጥበቃ ሂደትን በፕሮግራማዊ መንገድ ለመረዳት መንገድ ይከፍታል። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ  የተወሰኑ መንገዶች በለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ አመክንዮአዊ ማዕቀፍ ሊብራሩ ይችላሉ። ይህም ማለት ዓላማዎች፣ ግቦች፣ ተፅዕኖዎች፣ ውጤቶች ፣ እና እንቅስቃሴዎች በዝርዝር መገለጥ አለባቸው። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ በራሱ እንደ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ተቋማዊ ሂደቶችን የመሳሰሉ መሰረታዊ ሁነቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሲሆን እነዚህም  ለሚፈለገው ለውጥ ግብዓት ሊሆኑ ይችላሉ። የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ  በሌሎች ባለድርሻ አካላት ሊደረጉ የሚገቡ ድርጊቶችን ሊጠቁም ይችላል።

ከዚህ ቀደም የነበሩ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳቦች ለእያንዳንዱ እርምጃ አሳማኝ ማስረጃዎችን ያካተቱ ሲሆን የሂደቱን 'ለምን' እና 'እንዴት' ግልጽ በሆነ ምክንያት ያሳያሉ። ወደ አመክንዮአዊ ማዕቀፍ (logframe) አን ከተላመደ ግን ለተጋላጮች ጥበቃ ተዋናዮች ከታቀዱት የተወሰኑ እርምጃዎች ጋር የተያያዙ አካላት ብቻ ይካተታሉ። ተግባራት በአመክንዮ እና በቅደም ተከተል ይቀርባሉ። እሱም 'ሀ ወደ ለ' ይመራል በሚለው መልኩ ይሆናል። ሰንጠረዦች እና ኤክሴል (excel) ፋይሎች በብዛት ለአመክንዮአዊ ማዕቀፍ ያገለግላሉ።[22]

አግባብነት ያላቸውን ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለም አቀፋዊ ጊዜዎችን መለየት ለተጋላጮች ጥበቃ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ እና የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ አመክንዮአዊ ማዕቀፍ (logframe) በሚፈጠርበት ጊዜ ቁልፍ ምዕራፎችን ለማዘጋጀት ይረዳል። የታቀዱት የተጋላጮች ጥበቃ ተግባራት የሚቀረፁት ቁልፍ ባለድርሻ አካላት ከዚህ በፊት የትና መቼ እንደተሰማሩ እና ወደፊትም የት እንደሚሰማሩ በመረዳት ነው። ወደዚህ ግንዛቤ ለመድረስ ባለፉት ጊዜያት ቁልፍ ውሳኔዎች የትና መቼ ተደርገዋል? መጪዎቹ ጠቃሚ ክንውኖች ምንድን ናቸው? አግባብነት ያላቸው ዓለም አቀፍ ቀናት የቶቹ ናቸው? የሚመለከታቸው የክልል ስብሰባዎች ምን ምን ናቸው? ጉዳዩን ለመጠቀም ወይም ግንዛቤን ለማሳደግ ምን ጥሩ አጋጣሚዎች አሉ?


አንሀድ ላይ አሳ የምታጠምድ ሴት (Woman fishing in Anhad). ምስል: አሊ ናጀብ-ኤደን / ኦክስፋም

ሞጁል ፫

# የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት አቀራረብ እና ዘዴዎች

አሁን የተጋላጮች ጥበቃ ተሚጋችነት 'ችግር' ተለይቶ፤ የሚፈለገው ውጤት ወይም ዓላማዎች ተገልጸዋል። የባለድርሻ አካላት ልዬታ/ክለላ ስራ ከሀይል ሚዛን ትንተና/power analysis/ ጋር ተዳምሮ ዋና ዋና የሙግት ኢላማዎችን የለየ ሲሆን፥ የለውጥ ንድፈ ሃሳብ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት የሙግት ኢላማዎች የሚፈልጓቸውን ሁነቶች እና ውሳኔዎች ይዘረዝራል። ከዚህ በኋላ የሚቀረው ጉዳይ እርምጃ መውሰድ ይሆናል።

የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ (protection analysis) እና የሙግት ስትራቴጂ ዕቅድ ጨምሮ በሂደቱ ውስጥ ያሉት እያንዳንዱ ደረጃ በተሻለ ሁኔታ የሚከናወኑት ከተለያዩ ባለሙያዎች እና ድርጅቶች ግብዓት ሲያገኙ ነው። የሙግት ጥምረት እስካሁን ካልተቋቋመ ለሙግት ዘመቻው አጋር ሊሆኑ የሚችሉ አካላትን ለመለየትና ለማግኘት ጊዜው አሁን ነው። የትብብር አካሄድ የድጋፍ እርምጃዎችን ህጋዊነት እና ለጥረቱ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ስለሚያሳድግ የትብብር አካሄድ ይበልጥ ይመከራል። ይህ ሞጁል ቅንጂታዊ አካሄድ ለምን እና እንዴት የሚለውን ይዳስሳል። የቅንጂት አካሄድ አቀራረብን እና ዘዴዎችን በመከተል ቅንጂታዊ አካሄዱ የሚሳካ መሆኑን ከማረጋገጥ በተጨማሪ የሙግት ጥምረቱ ውሳኔ ሰጪዎች በተሳካ ሁኔታ በሚመለከት፤ የሚተገበርበት መንገድንና የሙግት እድል ዓይነቶች ማለትም የሙግት አቀራረብና ስልቶች ላይ መስማማት ይኖርበታል።

## በቅንጅት የመሥራት ጥቅሞች

የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ መፍትሄ ለማፈላለግ ተነሳሽነት ያላቸው ሌሎች ተዋናዮች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ የሙግት ጥምረትን ለመመስረት ጠቃሚ እድልን ይፈጥራል። እንዲሁም በአጋር አካላት መካከል ያለው ትብብር የሙግት ቅቡልነት እና ውጤታማነት ሊያሳድግ ይችላል። የአጋር አካላት ስብስብ የተለያዩ ማስረጃዎችን፣ ትንተናዎችን፣ የተደራሽነት አቅምን እና ውሳኔ ሰጪዎችን ማግኘት የሚችሉ አካላትን ለማቀናጀት ይረዳል።

የተጋላጮች ጥበቃ ተዋናዮች/ባለድርሻ አካላት አላማቸውን እና አካሄዳቸውን በአግባቡ ለማቀናጀት እንዳልቻሉ ጥናቶች ያሳያሉ።[23] የገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው ውድድር ወይም ኤጀንሲዎች በራሳቸው ቅድሚያ መስጠትን ተከትሎ በመካከላቸው አለመናበብ ለቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ምክንያት ሊሆን ይችላል። ይህም ድጋፍና ጥበቃ የሚሹ ሰዎችን ሁኔታ ለማሻሻል በተቀናጀ መልኩ የመስራት እድሎችን ያሳጣል።

*ምስል 3.1: ከማን ጋር ነው አጋርነት የምንፈጥረው?*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አገር በቀል ሲቪል ማህበራት | አለም አቀፍ ሲቪክ ማህበራት | የማህበረሰብ ድረጅቶች | ማህበራዊ እንቅስቃሰዎች | የሴቶች መብት ተሚጋች ድርጅቶች |
| ማህበረሰብ | የሃሳብ ማንሸራሸሪያ መድረኮች | ዩኒቨርሲቲዎች | መንግስት | የንግድ ተቋማት |
| ሚዲያ | የገበያ ኤጀንሲዎች | ፊልም ሰሪዎች/ የፎቶግራፍ ባለሙያዎች | አርቲስቶች | የተመድ ኤጀንሲዎች |
| የሀይማኖት አባቶች | የፖለቲካ ፓርቲዎች | ሊጋሾች | ተፅዕኖ ፈጣሪዎች | ሌላማን? |


ከ*Influencing for Impact Guide*, *ኦክስፋም* የተወሰደ

በሙግት እንቅስቃሴ ውስጥ የእያንዳንዱን አጋር ፍላጎት መረዳትና ማጣጣም በጣም አስፈላጊ ነው። በጊዜ ሂደት የአጋር አካላት ቁርጠኝነት አስፈላጊ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ ሊሳካ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ አጋሮች በጥምረት ውስጥ ጥቅሞቻቸውን እንደሚያስከብሩ እና ሁሉም እንደ አቻ አጋር ሲተያዩ እንዲሁም ጅማሮው ስኬታማ ሆኖ ከተገኘ ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ሲሰማቸው ነው። በጥምረቱ ውስጥ ያሉ አንዳንድ አጋሮች እንደ የቋንቋ መሰናክሎች፣ የቦታ ርቀት ወይም የገንዘብ አቅም ያሉ በእኩልነት ለመሳተፍ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ መሰናክሎች ሊያጋጥማቸው ይችላል። ሆኖም አጋሮች መጀመሪያ ላይ ማናቸውንም መሰናክሎች ለመለየት እና መፍትሄ ለመፈለግ ቁርጠኛ መሆን አለባቸው።

አጋር አካላትን ወደ ፊት ስናመጣ ስልታዊ በሆነ መንገድ ማሰብም ይመከራል። አንዳንድ አጋር አካላት ከሌሎች በተሻለ መልኩ መልዕክቶችን ለማድረስ በተሻለ ሁኔታ ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ሁሉም አጋሮች በተመሳሳይ ጊዜ ሁነኛ ቦታ መያዝ የለባቸውም። በሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች እና በሰብዓዊ እርዳታ ባለሙያዎች  መካከል መተባበር መኖር እንዳለበት ጥናቶችም ይመክራሉ።[24]

የተባበሩት መንግስታት ክላስተር ስርዓት የአለም አቀፍ የተጋላጮች ጥበቃ ክላስተርን ጨምሮ ያሉትን ውህደቶች ለመጠቀም እና የተሻለ የትብብር መነሳሳትን ለመፍጠር የሚያስችል መድረክ ይሰጣል። በአገር አቀፍ ደረጃ ከስድስት ዋና ዋና የክላስተር ተግባራት አንዱ ጠንካራ ሙግትን በተለያየ መንገድ፤ ማለትም 1) አሳሳቢ ጉዳዮችን በመለየት ቁልፍ መረጃዎችን እና መልዕክቶችን ለሰብዓዊ እርዳታ አስተባባሪ እና ለአገር አቀፍ ሰብዓዊ ድጋፍ ቡድን የመልእክት ልውውጥ እና ተግባር በማበርከት እና 2) ክላስተሩን፤ የክላስተር አባላትን እና የተጎዱ ሰዎችን በመወከል መሟገት መደገፍ ነው።[25]

***ምስል 3.2: ሰብዓዊና የአደጋ ግዜ እፎይታ አስተባባሪ***




ከIASC ለአስተባባሪ ክላስተር በተዘጋጀ ማጣቀሻ ሞጁል የተወሰደ

ክላስተሮች በሰብዓዊ ድጋፍ ባለሙያዎች እና በሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች መካከል ያለውን ትስስር ስርዓታዊ አቅምን ለመገንባት የድርጊት መርሃ ግብሮችን መፍጠር ይችላሉ።

የተጋላጮች ጥበቃ ተሟጋችነት ለተለያዩ ተዋናዮች የተለያዩ አደጋዎችን ሊያስከትል ስለሚችል፣ ሁሉም አጋሮች አደጋዎችን በጋራ መለየት፣ ማስማሚያ እቅዶች ላይ መስማማት እና የተሻሉ የተሳትፎ መንገዶችን መወሰን አስፈላጊ ነው። ያስታውሱ! የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች (WROs) ስለ ማህበረሰቡ የተጋላጮች ጥበቃ ደረጃ የተለያዩ ግንዛቤ የሚሰጡ የሥርዓተ-ፆታ ትንታኔዎችን በማበርከት ጠቃሚ አጋሮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ማስታወስ ያስፈልጋል።

ከተሟላ አጋርነት በተጨማሪ በባለድርሻ አካላት መካከል ምን አሸናፊዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ግምት ውስጥ ያስገቡ። ቅቡልነት ያላቸው (champions) ግለሰቦች እና ቡድኖች ስልጣንን እና ተፅእኖን የሚይዙ፣ ለዓላማው ህጋዊነትን ለመገንባት እና ጠንካራ ድጋፍ ለመስጠት የሚረዱ ናቸው። ቅቡልነት ያላቸው (champions) ብዙውን ጊዜ በጉዳዩ ላይ የግል ታሪኮች ወይም አመለካከቶች አሏቸው, በይፋ ለመናገር ፈቃደኛ ናቸው። ሰውነታቸው ለውሳኔ ሰጭዎች በሮችን ሊከፍት ይችላል።

# ከማህበረሰብ ጋር የመሥራት አስፈላጊነት

በእያንዳንዱ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ሂደት ውስጥ ዋነኛ መርህ የመብት ባለቤት የሆነውን ማህበረሰብ ማሳተፍ እና ማብቃት ነው። የማህበረሰቡ አባላት በተቻለ መጠን እና ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለራሳቸው እንዲናገሩ ማበረታታት በጉዳዩ ላይ በጣም የተጎዱ ሰዎች የባለቤትነት ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋል። ይህ ውክልናን ከማረጋገጥ በተጨማሪ የሙግት ስልቱ በጉዳዩ ለተጎዱ ወገኖች አስፈላጊ መሆኑን ያረጋግጣል።

የሙግት ዓላማዎችን እውን ለማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ መስራት በጣም አስፈላጊ ነው። የመብት ባለቤቶች ያልተሳተፉበት ሂደት የሚፈለገውን የፖሊሲና የህግ ለውጥ ማምጣት ቢቻልም የህግና ፖሊሲዎችን ውጤታማ እና ትርጉም ያለው ትግበራ ማረጋገጥ የሚቻለው በህብረተሰቡ ተሳትፎ ብቻ ነው።

ከማህበረሰብ አባላት ጋር መነጋገር፣ በስትራቴጂው፤ በአቀራረብ እና ስልቶቹ ላይ ግብአት እንዲያቀርቡ ማበረታታት እና ስለሚመቻቸው የተሳትፎ ዓይነቶች በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግ።

## የተጋላጮች ጥበቃ/ሙግት አቀራረብ መንገዶች

የሙግት ዘመቻዎች የህብረተሰቡን እና የሚዲያውን ቀልብ ለመሳብ የተነደፉ ጥቂት ዝግጅቶች ቢኖሩም በአብዛሀኛው የተጋላጮች ጥበቃ ተግባራት የሚከናወኑት በግል ነው።
ይህ ሁለቱንም የጥምረት አባላትን እና ሌሎች የተጋላጮች ጥበቃ አጋሮችን ሊመለከት ይችላል። ብዙሃኑ በአደጋዎች፣ ውስን የገንዘብ አቅም ወይም ሌሎች ምክንያቶች ማንነታቸው እንዳይታወቅ ይመርጣሉ። የተሻለ አቅም ያላቸው እና አደጋን የመቋቋም ችሎታ ያላቸው አካላት ለተጋላጮች ጥበቃ እንቅስቃሴ መሪ ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ።

የተጋላጮች ጥበቃን ለማረጋገጥ ከሚያስፈልጉት እርምጃዎች ጋር ውሳኔ ሰጪዎችን ወደ መድረክ ለማምጣት በተለምዶ ሶስት ዓይነት የአቀራረብ መንገዶች አሉ እነሱም፥ **ማሳመን፣ ማሰባሰብ እና ውግዘት ናቸው**። ሦስቱ ዘዴዎች የተቀናጁ ስልቶችን ለመንደፍ የሚደግፉ የጥበቃ ማእቀፍ አካል ናቸው።[26] ይህም ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዎችን ወዲያውኑ ለመግታት፣ ለመቅረፍ የታለሙ እርምጃዎችን አደጋው ከቀነሰ በኋላ የኑሮ ሁኔታውን ወደነበረበት መመለስ ወይም መብቶች የሚከበሩበት አካባቢ መፍጠርን ያካትታል።[26]

### የአጠቃቀም ዘዴ ምርጫ የሚወሰነውም:

- ውሳኔ ሰጪዎች እርምጃ ለመውሰድ ያላቸው ፍላጎት እና አቅም፣
- ተጎጂዎች እራሳቸው እንዲሰሩ የሚያስችል አቅም፣
- የጥምረቱ የድርጊት አቅም እና የሚጠበቀው የድርጊት ቆይታ፣
- ከቀደምት ድርጊቶች የተወሰዱ ትምህርቶች፣
- የተገመገሙና የተለዩ የአደጋ ስጋቶች

*Figure 3.3: ማሳመን፣ ማሰባሰብ እና ውግዘት*

| ማሣመን | ማሰባሰብ | ውግዘት |
|---|---|---|
| ➤ የለውጡን አስፈላጊነትና ለውጡን ለማድረግ የራሳቸውን እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ውሳኔ ሰጪዎችን ማሳመን።<br>➤ ማሳመን ከኃይል ክርክር ይልቅ የክርክርን ኃይል ይጠቀማል። | ➤ ማሰባሰብ ሰላማዊ ሰዎችን ለመጠበቅ የተለየ እርምጃ እንዲወስዱ ተገቢውን የኃያላን ውሳኔ ሰጪዎች መረብ የመገንባት፣ የማሳወቅ እና የማበረታታት ጥበብ ነው።<br>➤ ቅስቀሳ ከታች ወደላይ፣ ከላይ ወደ ታች ወይም ሁለቱም በአንድ ጊዜ ሊሆን ይችላል። | ➤ የውግዘቱ አመክንዮ ውሳኔ ሰጪዎችን በሕዝብ መጋለጥ፣ በግል ሕሊና ወይም ግልጽ በሆነ ፍላጎት የተለየ እርምጃ እንዲወስዱ ማሳፈር ነው።<br>➤ ውግዘት ጮክ ብሎ እና ይፋዊ መሆን አያስፈልገውም። እንዲሁም ግላዊ፣ ጸጥ ያለ እና በጥንቃቄ ያነጣጠረ ሊሆን ይችላል። |

ከ*Protection: An ALNAP Guide for Humanitarian Agencies*, ALNAP የተወሰዶ

➤ **ማሳመን፡** ክርክሩ ምክንያታዊ እና አሳማኝ በሆነ መልኩ ከውሳኔ ሰጪው የሞራል እይታ እና የግል ጥቅም ጋር ተጣጥሞ መቅረብ መቻል አለበት፡፡ ስብሰባዎች፣ ሪፖርቶች፣ ደብዳቤዎች እና መደበኛ ልውካንን መጠቀም ከማሳመኛ ስልቶች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

➤ **ማሰባሰብ፡**ባለድርሻ አካላት መረብ - ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች የተደራጁት - ለውሳኔ ሰጪው አንድ መልእክት ለማስተላለፍ ነው። በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ ፈጣን እርምጃ እንዲወሰድ በሚጠይቁ ተዋናዮች ብዛት ምክንያት ውሳኔ ሰጪው አካል ላይ የሚያርፈው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። ከእነዚህ የንቅናቄ ስልቶች መካከል ሰላማዊ ሰልፎችን፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ተፅዕኖዎችን ደብዳቤ የመጻፍ ዘመቻዎችን እና አቤቱታዎችን ያካትታል።

➤ **ለማውገዝ፡** ይህ በድርጊት ወይም በድርጊት አለመኖር ላይ ጠንከር ያለ መግለጫ መስጠት እንዲሁም የውሳኔ ሰጪውን ፍርድ ማውገዝን ያካትታል። ለአደጋ አፋጣኝ ምላሽ፣ ወይም የበለጠ አንጸባራቂ፣ የረጅም ጊዜ እይታ ሊሆን ይችላል። ውግዘት ይፋዊ ሊሆን ይችላል፣ነገር ግን በተዘጉ ቦታዎችም ሊከሰት ይችላል። የውግዘት ዘዴዎች የሚዲያ መግለጫዎች፣ በክስተቶች ላይ የተደረጉ ንግግሮች፣ ቀጥታ ስብሰባዎች እና ደብዳቤዎች ያካትታሉ።

የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት/አዲቮኬሲ ቅስቀሳ ዘመቻዎች የማሳመን፣ የመሰብሰብ እና የውግዘት መንገድን አንድ ላይ ሊያካትቱ ይችላሉ። ነገር ግን ህዝባዊ ውግዘት ከጥቅም ውጭ መሆን አለመሆኑን በጥንቃቄ ማሰብ ያስፈልጋል።[27] የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ለደረሰባቸው ነቀፋ ምላሽ ሲሉ ከተሟጋቾች ጋር ለመገናኘት ፈቃደኛ ላይሆኑ ይችላሉ።

ምስል 3.4 እንደ ውግዘት ያሉ ተቃራኒ አካሄዶችን ከሚጠቀሙ የህዝብ እና የግል የጥብቅና ዘዴዎች ጋር ተጨማሪ ልዩነቶችን ያሳያል ወይም የበለጠ በማሳመን አዎንታዊ አቀራረቦች ላይ ያተኮሩ። አብዛኛዎቹ የጥብቅና ስልቶች በመጨረሻ ብዙ ጊዜ እንደዚህ ያሉትን በርካታ 'የድርጊት ስልቶች' በተለያዩ ጊዜያት እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ያዋህዳሉ። ይህም የጥበቃ ስጋቱን ባህሪ፣ የባለድርሻ አካላትን ትንተና፣ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ እና ተዛማጅ አጋሮችን የአደጋ ስጋት መቻቻልን ያሳያል።

*ምስል 3.4: የሙግት መንገዶች*[28]

| | |
|---|---|
| **ይፋዊ ተቃዋሚ**<br>በፖሊሲ ወይም በተግባር ላይ ለውጦችን የሚጠይቅ ይፋዊ ሪፖርት | **ህዝባዊ አዎንታዊ**<br>ለጋራ ስጋቶች መፍትሄዎችን ለመለየት ከመንግስት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ እና ከማህበረሰቦች ጋር የተደረገ ህዝባዊ ዝግጅት |
| **የግል ተቃዋሚ**<br>ወታደራዊ አሠራርን በሚቆጣጠር ሕግ ላይ ለመወያየት ከፓርላማ ኮሚቴ ጋር የተደረገ ከመዝገብ ውጪ ስብሰባ | **የግል አዎንታዊ**<br>የሲቪል ተጎጂ ፖሊሲን ለማዘጋጀት ከሠራዊቱ ጋር የተደረገ ተከታታይ ከመዝገብ ውጪ ስብሰባዎች |

ከሴንተር ፎር ሲቪሊያንስ ኢን ኮንፍሊክት፥ *Protecting Together: Preventing, Mitigating, and Addressing Civilian Harm, Advocacy Guide*, 2022,ገጽ 21 የተወሰደ

በአንዳንድ ሁኔታዎች ለሙግት የሚሆን ቦታና እድል አነስተኛ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አሁንም ከመንግስት ጋር መግባባት እና በፖሊሲ እና በተግባር ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይቻላል። የሙግት ጉዳዮችን በጥንቃቄ መምረጥ፣ በልዩ ልዩ ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ የበለጠ ፈቃደኛ የሆኑትን የመንግስት አካላት ኢላማ ማድረግ እና አደጋዎችን ለመቀነስ እና ኔትወርኩን ለማስፋት ከቅንጅት አካላት ጋር በጋራ መስራት መልካም ነው።

## የሙግት ስልቶች

የሙግት/አድቮኬሲ ስልቶች ግባችንን ለማሳካት የሚደረጉ ልዩ እርምጃዎች ናቸው።[29]

- **ጥናትና ምርምር፡-** ለምሳሌ በአንድ ጉዳይ ላይ ድርጅታዊ አቋምን ማዘጋጀት እና መግለጽ እና ችግሩን ለመፍታት ምን መደረግ እንዳለበት የምርምር ሪፖርቶችን እና ፖሊሲዎችን ማሳተም።
- **ውትወታ እና ቀጥተኛ ሙግት፡-** ለምሳሌ ሰላማዊ ግንኙነቶችን መገንባት፣ ማደራጀት እና በስብሰባ ላይ መገኘት፣ የሎቢ ደብዳቤዎችን መጻፍ ወይም ከውሳኔ ሰጪዎች እና ከመንግስት፣ ከንግድ እና ከሌሎች ተቋማት እና ድርጅቶች ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሆኑ ሰዎች ጋር በቀጥታ ግንኙነት ማድረግ።
- **ውይይቶችን እና ተሳትፎን ማመቻቸት፡-** ለምሳሌ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና ውሳኔ ሰጪዎች ጋር የውይይት ቦታዎች እና መድረኮች ማመቻቸት እና መሳተፍ።
- **ማህበረሰብ መር ተሚጋችነትን እና በጉዳዮች ላይ ተሳትፎን መደገፍ:** ለምሳሌ በወሳኝ የገንዘቤ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎች፣ አሳታፊ እና የጋራ መማሪያ ዝግጅቶችን ማዘጋጀት።
- **የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሴቶች እና ወንዶች እራሳቸውን ለውጥ ፈጣሪ እና ተፅእኖ ፈጣሪ እንዲሆኑ መደገፍ፡-** ለምሳሌ በአመራር ልማት ፕሮግራሞች።
- **ኮሙኒኬሽን እና ሚዲያ:** ለምሳሌ ከሀገር ውስጥ፣ ከሀገር አቀፍ እና ከአለም አቀፍ ሚዲያዎች እና የመገናኛ ዘዴዎች፣ ከማህበራዊ እና ዲጂታል ሚዲያዎች እና ከሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች ጋር መገናኘት እና መጠቀም።
- **ህብረት መፍጠር እና የአውታር መረብ ግንባታ:** ለምሳሌ የጋራ ግቦችን ለማሳካት የሲቪል ማህበረሰብ፤ የሴቶች ቅንጅቶችን እና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን ማስተባበር፣ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እና መሳተፍ።
- **ማህበራዊ ደንቦች እና የባህሪ ለውጥ:** ለምሳሌ ማህበራዊ ትምህርትን መደገፍ ወይም ተደማጭነት ያላቸውን መልእክት አድራሾች መጠቀም።
- **ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ድጋፍ መስጠት:** ለምሳሌ የገንዘብ ድጋፍ፣ የቴክኒክ ምክሮች እና ስልጠና በመስጠት።

ከሁኔታዎች አንጻር የተለያዩ አይነት ዘዴዎችን ወይም ስልቶችን ማሰብ ይገባል ለሙግት ክፍት የሆኑ ቦታዎች፣ የይገባኛል ጥያቄዎች በነዚህ ቦታዎች ውስጥ ምን የጥበቃ/ሙግት እድሎች አሉ? ምን እድሎችስ ሊፈጠሩ ይችላሉ?

**የሙግት አጋጣሚ እድሎች**

| የተሰጡ እድሎች | የተገኙ እድሎች | የተዘጉ እድሎች |
|---|---|---|
| ➤ በውሳኔ ሰጪዎች የተደራጁ ወይም የተገኙባቸው ዝግጅቶች ወይም መድረኮች። ለእንደዚህ አይነት ክስተት መጋበዝ የፖሊሲ ለውጥ አስፈላጊነትን "ከውስጥ በኩል" ለመናገር እና ግንኙነቶችን ለመመስረት ጠቃሚ እድል ይሰጣል። | ➤ ያለ ኦፊሴላዊ ድጋፍ የተደራጁ ዝግጅቶች ወይም መድረኮች። ከአጋሮች እና ከተፅእኖ ፈጣሪዎች ጋር ለመነጋገር ቦታ ይሰጣል፣ ነገር ግን ከውሳኔ ሰጪዎች ወሳኝ ነፃነትን ይጠብቃል።<br>➤ ህትመቶች: የመመሪያ ወረቀቶች፣ የምርምር ዘገባዎች፣ የማጠቃለያ ማስታወሻዎች።<br>➤ የሚዲያ እና የመገናኛ አውታሮች፣ ማህበራዊ እና ዲጂታል ሚዲያዎች።<br>➤ ቅስቀሳ እና ዘመቻ: ሰልፎች፣ የኢሜይል አቤቱታዎች፣ የብዙኃን ማህበራዊ ሚዲያ ድርጊቶች። | ➤ ከውሳኔ ሰጪዎች እና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ጋር ቀጥተኛ ስብሰባዎች.<br>➤ ለውሳኔ ሰጪዎች ቀጥተኛ፣ ይፋዊ ያልሆኑ ግንኙነቶች።<br>➤ በጉዳዩ ላይ ለውሳኔ ሰጪዎች መረጃን ለማስተላለፍ ከተፅእኖ ፈጣሪዎች ጋር ቁልፍ ግንኙነቶችን መጠቀም። |

በጥምረቱ ውስጥ አንዳንድ አጋሮች በተወሰኑ ዘዴዎች ላይ ለመምራት ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ሊቀመጡ ስለሚችሉ ማን ምን እንደሚያደርግ ስትራቴጂክ መሆን ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንድ ድርጅት በምርምር እና በፖሊሲ ልማት የላቀ ሊሆን ይችላል፣ ሌላው ደግሞ ሁነቶችን በማቀላጠፍ ረገድ ከፍተኛ ልምድ ያለው፣ ሌላኛው ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር ቀጥተኛ ስብሰባዎችን ለማድረግ በጥሩ ሁኔታ ሊመደብ ይችላል፣ ልሎች ደግሞ በማህበረሰቦች ውስጥ ግንዛቤን ለማሳደግ ይችል ይሆናል።

## መልዕክቶችን መቅረፅ እና መለየት


የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት/አዲቮኬሲ ስልት ሂደቶች ውስጥ ዋነኛ ገፅታ፤ በተለዩት ስልቶች፣ ቻናሎች እና እርምጃዎች ላይ የሚተላለፉትን መልዕክቶች፣ ምክሮች እና ትረካዎች ማዘጋጀት እና መቅረጽ ላይ ነው።

በሞጁል 1 ውስጥ የተዳሰሱት የተጋላጮች ጥበቃ ትንተናዎች የማንኛውንም የሙግት ስራ ተነሳሽነት ወይም ስትራቴጂ አካል የሆኑትን የትረካ እና ልዩ መልዕክቶችን ለመቅረጽ ቁልፍ እድልን ይፈጥራሉ። እንደ የአለምአቀፍ ጥበቃ ክላስተር የጥበቃ ትንተና ዝማኔ[30] ያሉ ማጠቃለያ ትንታኔዎች 'የተጋላጮች ጥበቃ ታሪኩን' ለማዘጋጀት ያግዛሉ። እንዲሁም የተጋላጮች ጥበቃ ችግሮችን ተደራሽ ለተለያዩ ኢላማዎች ወይም ውሳኔ ሰጪዎች አግባብነት ባላቸው ምክሮች ወይም 'የድርጊት ጥሪዎች' ላይ ያተኩራሉ።

ምስል 3.5 በትኩረት እና ድርጊት ተኮር የሆኑ ምክረ ሃሳቦችን በማዘጋጀት ግምት ውስጥ ያስገባል። በአጠቃላይ እንደዚህ ያሉ ምክሮች - የተፅእኖ ቦታን ወይም የተለያዩ ዒላማዎችን የመወሰን ኃይልን በማንፀባረቅ እና በእነዚህ የተለያዩ ኢላማዎች ምን ልዩ እርምጃዎች እንደሚያስፈልጉ፣ በየትኛው ቦታ፣ በየትኛው የጊዜ ገደብ ውስጥ እና ግልጽ ሀሳቦችን ማምጣት ይቻላል በማለት የበለጠ ልዩ ሊደረጉ ይችላሉ። እንዲሁም የበለጠ (በቀላሉ) ሊተገበሩ እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ይረዳል።

እንደዚህ ያሉ ምክሮች እና መልዕክቶች እንደ የፖሊሲ አጭር መግለጫ ወይም የሚጠየቁ ጥያቄዎች ሰነድ፣ ወይም በውትወታ ስብሰባዎች ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውሉ የውይይት መድረኮች፣ የቃል ገለጻዎች ወይም ሌሎች ተሳትፎዎች ውስጥ በሙግት መሳሪያዎች ውስጥ ሊዋሃዱ ይችላሉ። በእርግጥ መልእክቶች እና ምክሮች ብቻ በቂ አይደሉም። እውነተኛ እሴታቸው በተለያዩ ኢላማዎች እና በተለያዩ ቻናሎች የሙግት ስትራቴጂ አካል ተብለው በተለዩት አካሄዶች እና ስልቶች እንዴት እንደሚተላለፉ እና እንዴት እንደሚካፈሉ ነው።

**ምስል 3.5፡ የጥብቅና ምክረ ሃሳቦችን በማዘጋጀት ላይ ግንዛቤ መደረግ ያለባቸው**




መልዕክቶችን፣ ምክሮችን እና ሰፊውን ትረካ የምንቀርጽበት መንገድ ብዙውን ጊዜ አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወስዱ የሙግት ኢላማዎችን ከማነሳሳት አንጻር እንደትክክለኛው ይዘት አስፈላጊ ነው። ግንኙነቶችን በመቅረጽ እና የመልእክት መላላኪያዎችን ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ጉዳዮች እና የጥብቅና ዒላማዎች እሴቶችን በሚያገናኙ መንገዶች፣ ተጽዕኖ ለማድረግ የምንሞክረውን እና እንዲሰሩ ለማነሳሳት የምንሞክርባቸውን ሰዎች ለማነሳሳት የበለጠ እድል እንሰጣለን።

ይህ ለምሳሌ ከታጠቁ ሀይሎች ጋር ድርድር በሚያደርጉ የተጋላጮች ጥበቃ ተዋናዮች የሚታወቅ ነጥብ ነው። ከፍተኛ መጠን ያለው ጊዜ እና ጉልበት ከመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች አባላት ጋር ለመነጋገር በጣም ውጤታማ መንገዶችን ለማግኘት (ከስር እሴቶቻቸው እና ፍላጎቶቻቸው ጋር በማገናኘት) ስለ ሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽነት አስፈላጊነት ወይም የአለም አቀፍ የሰብዓዊ ህጎችን (IHL) ማክበር ይተገበራል።

በሁለቱም የህዝብ እና የግል ቦታዎች የተጋላጮች ጥበቃ ተሟጋች መልእክቶችን የመቅረጽ አስፈላጊነት የሚመጣው  በባህር ማዶ ልማት ኢንስቲትዩት (ኦዲአይ) በተካሄደው ለሰብዐዓዊነት መሟገትየምርምር ፕሮጀክት (2019) ላይ ጠንከር ብሎ የተገለጸ ነው። ይህ ጥናት የጥበቃ ጠበቆች ከአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር ጋር በመሳተፋቸው ከባለስልጣናት ጋር ሲወያዩ ከባህላዊ የህግ ቃላቶች ርቀው በምትኩ 'የሲቪል ጉዳት' ጽንሰ-ሀሳብ እና ቋንቋን ሲቀበሉ ከአሜሪካ የመከላከያ ሚኒስቴር ጋር በመሳተፋቸው ከፍተኛ ስኬት እንዳለው የሚያሳይ ማስረጃ አግኝቷል። [32]

ከተለያዩ መንግስታት ጋር አብረው የሚሰሩ ዲፕሎማቶች የታሪኮችን ውጤታማነት በተሟጋቾች የሚያስተላልፉት የጥበቃ መልእክት አካል እንዴት እንደሆነ እንዳስተዋሉ ጥናቱ አመልክቷል፣ እነዚህ ታሪኮች የIHL ጥሰቶችን አስከፊ የሰው ልጅ ተፅእኖ በግልፅ የሚያሳዩ እና አስፈላጊ እርምጃዎችን ለማነሳሳት የሚረዱ ናቸው።

የተለያዩ የጥበቃ ተዋናዮች ከሚያመጡት ልዩ ልዩ ግንዛቤ አንፃር ለመልእክቶች እና ለትረካዎች መቀረጽ ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ሌላው የትብብር አካሄድ ለጥብቅና ጥረቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። የአካባቢ እና የብሔራዊ ጥበቃ ተዋናዮች ከሚመለከታቸው ባለስልጣናት ጋር ምን ዓይነት መልእክት እንደሚለዋወጡ ልዩ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል ፣ ነገር ግን በኒውዮርክ የሚገኙ የጥብቅና ባልደረቦች ከአንድ የተወሰነ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት አባል ጋር ለመቀራረብ እውቀታቸውን ወደ ትኩረት ማምጣት ይችሉ ይሆናል።

በዋና ከተማ ውስጥ ያለ አጋር በመደበኛነት ለሚያገኟቸው የፓርላማ አባላት የሚተላለፉ መልዕክቶችን በጣም አስፈላጊ እና አስገዳጅ በሆነ መንገድ ጥረቱን ሊደግፍ ይችላል። እነዚህ የተለያዩ ተሟጋቾች የሚያራምዱዋቸው መልእክቶች በተመሳሳይ ትንተና እና ዋና ‘የድርጊት ጥሪዎች’ ላይ የተመሰረቱ መሆን አለባቸው ነገር ግን ለተፈለገው ለውጥ አስተዋጽዖ ሊያበረክቱ ለሚችሉ የተለያዩ ዒላማ ታዳሚዎች የተዘጋጀ መሆን አለበት።

## ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር ለመነጋገር የሚጠቅሙ ግንዛቤዎች

ውሳኔ ሰጪዎችም ሰው ናቸው። ግባቸውን እና ገደቦችን ለመረዳት ይሞክሩ።  ይህ ማለት ግን ከአካሄዳቸው ወይም ከተግባራቸው ጋር ምንም አይነት ስምምነት አለ ማለት አይደለም። በቀላሉ ውጤታማ የሆነ ሙግት የሚሰራው አንድን ዒላማ ምን እንደሚፈልግ በመረዳት አንድን ውሳኔ ለማድረግ እንዲችሉ እና ምን እንዲያደርጉ እንደሚያነሳሳቸው በመረዳት ነው።

ውሳኔ ሰጪው እርስዎ ለመፍታት እየሞከሩት ስላለው የሙግት ችግር ሁሉንም መረጃ ወይም ዝርዝሮች መረጃዎች አሉት ብለው አያስቡ። ችግሩ በሰዎች ህይወት ላይ እንዴት ተጽዕኖ እያሳደረ እንደሆነ ታሪኮችን እና ምሳሌዎችን ማጋራት የግድ በመደበኛ የመረጃ ቻናሎቻቸው ሊደርሱባቸው የማይችሉት አስፈላጊ አካል ሊሆን ይችላል።

ውሳኔ ሰጪው አስቀድሞ በጉዳዩ ላይ የተናገረውን ወይም ያደረገውን ለማወቅ፣ የትኛውን ቋንቋ እና ቃላቶች እንደሚጠቀሙም በመገምገም አንዳንድ የዳራ ጥናት ያድርጉ። ይህ መልእክቶች በትክክል የተስተካከሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል። ይህም የተከናወኑ እና ሊገነቡ የሚችሉ ትናንሽ አወንታዊ ድርጊቶችን ማወቅን ይጨምራል። እንዲሁም የሚጠቀሙባቸውን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን አንዳንድ ቋንቋዎች ከሰብአዊነት ቃላት በመራቅ በቀጥታ ማንጸባረቅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

በቀጣዮቹ ስብሰባዎች፣ መረጃዎችን እና ትንታኔዎችን በመደበኛነት በመለዋወጥ የግንኙነቶችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ ቀጣይነት ያለው ተሳትፎ እና እድገትን፣ ለአስፈላጊ ዝግጅቶች ግብዣዎችን እና ሌሎች እርምጃዎችን በአውድ ላይ በመመስረት ያረጋግ።

ሞጁል 4

# የሙግት ውጤቶችን ክትትልና ልኬት (MONITORING AND MEASURING ADVOCACY OUTCOMES)

የሙግት ተግባራቶችን የሚያስተባብር የሙግት እቅድ በተጨማሪ የሙገታ ጥረቶቻችን በአጭርና ረዥም ጊዜ ያመጣዉን ተጽእኖ ለመገምገም እቅድ ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው። ይህም በሚከተሉት ነገሮች ሊጠቅም ይችላል፣ 1) የሙገታ ጥረቶቻችን በጊዜ ሂደት ለለውጥ ያደረገውን አስተዋጽኦ ለመረዳትና ለመለካት 2) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የሙግት እቅዶቻችንን ለማስተካከል እና 3) ተጠቂ ማህበረሰቦችን ጨምሮ ከባለድርሻ አካላት፣ አጋሮች፣ አመረራሮች፣ ረጂ ድርጅቶች ጋር የሙግት ተግባራት ያመጣዉን ውጤት በማጋራት ተጠያቂነትን፣ ድጋፍንና መነቃቃትን ለማጠናከር ይረዳል።

## ለተጋላጮች ጥበቃ ሙግት የክትትል፣ ግምገማና ትምህርት (Monitoring, Evaluation, Learning) እቅድ ማዘጋጀት

በሴንተር ፎር ሲቪሊያን ኢን ኮንፍሊክት (Center for Civilians in Conflict (CIVIC)) የሙግት ማጣቀሻ[33] ላይ እንደተገለጸው ወደ ሙግት ስራ ከተገባ ጀምሮ የሙግት ስትራቴጂውን ስኬታማነት መከታተል ድርጅቱ ወይም ህብረቱ ያስቀመጠውን አላማና ተጠባቂ ውጤት በማሳካት ረገድ ውጤታማ መሆኑን ለመረዳት ብቻ ሳይሆን በታየው ለውጥ የድርጅቱ አስተዋጽኦ እስከ የት ድረስ እንደሆን እንዲሁም በድርጊት መርሃ ግብሩ ቆይታ ወቅት አካሄዱን ለመቀየርና ስልቶችን ለማስተካከል እድል ይፈጥራል።


ለድርጅቶች እና ህብረቶች የክትትል፣ ግምገማ እና መማር (MEL) ዕቅዶችን እና አካሄዶችን ለማዘጋጀት ብዙ መንገዶች አሉ ነገር ግን እያንዳንዱ እቅድ የሚከተሉትን ያካትታል[34]፡

- ትርጉም ያለው፣ ሊለካ የሚችል የለውጥ አመላካቾች ከተፈለገው ዓላማዎች እና ውጤቶች ጋር ያካተተ።
- ማስረጃን የተፅዕኖ መሠረት በማድረግና ለውጤት አመላካቾች መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብ እቅድ ማካተት።
- አድልኦዎችን፣ ለሚታዩ ክስተቶች አሳማኝ አማራጭ ማብራሪያዎች እና አሉታዊ ውጤቶችን መለየት።
- ለውጥን ለመገምገም፣ ሃሳብ ለመስጠት፣ ያማከለ የስትራቴጂና ስልት ለውጥ ለማድረግ የታቀዱ እና ጊዜያዊ እድሎችን ያካተተ።

በተጨማሪም የMEL እቅድ በሙግት ዘመቻው ውስጥ የቡድን ሞራልን በመጠበቅ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ለተገኘው የአጭር ጊዜና መካከለኛ ጊዜ አወንታዊ የለውጥ ስኬት እውቅና ይስጡ!

ምስል 4.1: **ሙግት እንደ ቀጣይ ዑደት**




ከINTRAC Toolkit for Small NGOs, ክፍል 7: የሙግት ስልት ክትትልና ግምገማ የተወሰደ

# ከመጀመሪያው ጀምሮ መለካት

የሙግት ተግባራትን ውጤትን ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ መገምገም ለስትራቴጂው ስኬት ትልቅ አስተዋፅኦ ይኖረዋል። ውጤቶችን መለካት ሃሳብ ለመስጠትና ከተግባራትና ክስተቶች ለመማር እድልን ይፈጥራል። ከዚህ የተገኙት ትምህርቶች የዕቅዱን ትክክለኛነት የሚያረጋግጡ ወይም በእቅዱ ውስጥ መወሰድ ያለባቸውን ማሻሻያዎች ሊያመለክቱ ይችላሉ[35]።

# ምን ይለካል (What to Measure)?

የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ውጤቶቹ ቀድሞውኑ በስትራቴጂው ሊገለጹ/ሊቀመጡ ይችላሉ። እነዚህ ለተጋላጮች ጥበቃ ተሟጋች ዓላማ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ወሳኝ ክንውኖች ናቸው። 'ውጤቶች' ከተወሰዱት እርምጃዎች ይልቅ የተፈለገውን ለውጥ ይገልፃሉ። የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ተግባራት ሂደት ውስጥ ወደ መጨረሻው አላማ የሚደረገውን የእድገት ደረጃ ለመረዳት ውጤቶች መለካት ይኖርባቸዋል።

በተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ላይ የተገኙ ውጤቶች ሙሉ በሙሉ በራሳችን ጥረት ላይሆኑ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ በውጤቱ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ብዙ ተጨማሪ ተዋናዮች ወይም ሁኔታዎች አሉ። በመሆኑም ውጤቶቹን በስራችን ብቻ የመጡ ልንለው የምንችለው ከስንት አንዴ ነው። የሙግት አስተዋጾን ሌሎች ባደረጉት ሰፊ አውድ መለካት እና የሙግት ስራ ሂደቱን እና ውጤቱን እንዴት እንደረዳ ማሳየት ይኖርብናል። አንዳንድ ውጤቶች ለመለካት እና ለመከታተል ቀላል ይሆናሉ። ሌሎች ደግሞ ለመለካት አስቸጋሪ እና ለመከታተል አስቸጋሪ ይሆናሉ። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች ለመከታተል ወይም ለመለካት አስቸጋሪ ሆኖ የተገኘው በጣም ትርጉም ያለው ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ህጎች፣ሀገራዊ ፖሊሲዎች እና የጸጥታ ተግባራት በቀላሉ የሚለኩ እና የሚታዮ ሲሆኑ አስተምህሮ፣አሰራር፣ስልጠና፣የሃብት ድልድል እና የተቋማት አቅም የሚለኩ እና አንዳንዴም የሚታዩ ብቻ ናቸው። ለመለካት አስቸጋሪ የሚሆኑት አመለካከት እና እምነት፣ ተቋማዊ ባህል እና ተጽዕኖን መቀበል ናቸው። ምንም እንኳን ውጤቶቹ እራሳቸው በተጨባጭ ሊለያዩ ቢችሉም የውጤቶቹን ስኬት ለመገምገም መረጃ ይሰበሰባል። ለሙግት ውጤቶች የተሰበሰበው መረጃ በጥራት እና በቁጥር ይሆናል።

*ምስል 4.2: **የአጭር ጊዜ ውጤቶች, ስኬት, ተጽዕኖ***



**የአጭር ጊዜ ውጤቶች (Output)**
በልማት ጣልቃገብነት ምክንያት የሚመጡ ምርቶች፣ የካፒታል እቃዎች እና አገልግሎቶች፣ በውጤቶች ስኬት የሚመጡ ለውጦችንም ሊያካትት ይችላል።

**ስኬት (Outcome)**
የአጭር-ጊዜ እና መካከለኛ-ጊዜ ጣልቃ-ገብነት ሊሳኩ የሚችሉ ወይም የተገኙ ውጤቶች

**ተጽእኖ (Impact)**
በልማት ጣልቃገብነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታሰበ ወይም ያልተፈለገ አወንታዊ እና አሉታዊ፣ የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የረጅም ጊዜ ውጤቶችን ያካትታል።

ከአክስፋም MEL of Enfluencing ክፍል 2.2 የተወሰደ

**የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት የውጤት ምሳሌዎች**

- በአንድ ጉዳይ ላይ የፖሊሲ ለውጥን ለመለካት የሚያገለግሉ ውጤቶች ለምሳሌ አዲስ ፕሮፖዛል ወይም መመሪያ መርሆች (የፖሊሲ ልማት)፣ በይፋ የወጡ ፖሊሲዎች (በፖሊሲ አጀንዳዎች ላይ ማስቀመጥ) ወይም በመደበኛነት የተቋቋሙ ፖሊሲዎች (የፖሊሲ ትውውቅ) ሊሆኑ ይችላሉ።
- በኮንፈረንስ ላይ የሚካፈሉ ሰዎች ብዛት ወይም የማህበራዊ ሚዲያ ልኡክ ጽሁፍ ማንበብ (የህዝብ መጋለጥ)፣ በሰርቶ ማሳያ ላይ የሚሳተፉ ወይም ለማህበራዊ ሚዲያ ልጥፍ ምላሽ የሰጡ ሰዎች ብዛት (የህዝብ ተሳትፎ) ወይም ፒቲሽን የሚፈርሙ ወይም

ትዊት የሚለጥፉ ሰዎች በመሳሰሉት በአንድ ጉዳይ ላይ ህዝባዊ ተሳትፎን ለመለካት ጥቅም ላይ የሚውሉ ውጤቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

∏ በአንድ ጉዳይ ላይ የባህሪ ለውጥን ለመለካት ጥቅም ላይ የሚውሉ ውጤቶች በተሰራጨው መረጃ ወይም በተሰጠው ድጋፍ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ብዛት (የግንዛቤ መጨመር)፣ ሰዎች በጉዳዩ ላይ እንዴት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ማወቅ (እውቀት መጨመር) እና አዎንታዊ ወይም አሉታዊነትን ሊያካትቱ ይችላሉ። ለጉዳዩ የተሰጠውን ትኩረት ወይም አስፈላጊነት ደረጃ (የአመለካከት ለውጥ) ያካትታሉ።

ከኦክስፋም *Influencing for Impact* መመሪያ የተወሰደ

## እንዴት ይለካል (How To Measure)?

የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብ (ቲዎሪ ኦፍ ቼንጅ) እና/ወይም የአድቮኬሲ ስልት እና የሚጠበቁ ውጤቶችን ይወስናሉ። አፈፃፀሙን ለመገምገም አግባብነት ያላቸውን አመልካቾችም ማካተት አለበት። ከዚህ በመነሳት የአድቮኬሲ ተፅእኖ መለኪያ እቅድ ሊዘጋጅ ይችላል (እባክዎ ማጣቀሻ ቁጥር 5 ይመልከቱ)። የአድቮኬሲ ተጽዕኖ መለኪያ እቅድ የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

- ክትትል የሚደረግባቸው ውጤቶች
- መሰብሰብ ያለበት የመረጃ አይነት
- መረጃ እንዴት እንደሚሰበሰብ
- የመረጃ አሰባሰብ ድግግሞሽ (ለምሳሌ በየሳምንቱ፣ በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ)
- መረጃ ለመሰብሰብ ኃላፊነት ያለባቸው ሰዎች
- የተሰበሰበው መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል

የአድቮኬሲ ተፅእኖ መለኪያ እቅድ ምን አይነት መረጃ መከታተል እንዳለበት የሙገታ ቡድኑን ይመራል። በሚደረጉ ሙግት ጥረቶች እድገትን በሚመለከት ምን አይነት መረጃ ጥሩ ግንዛቤ እንደሚሰጥ ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። በተመሳሳይ ጊዜ የሀብት እና የጊዜ ገደቦች እንደ ምክኒያት ከተቀመጡ በእውነቱ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉትን መረጃዎች ብቻ መሰብሰብ ይመከራል። የሚፈለገው ማንኛውም መረጃ አስቀድሞ በሌሎች ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች እየተሰበሰበ እንደሆነ ማጤን እና መረጃዉን መጋራት እንደሚቻል ቢታሰብበት ይመከራል።

የተጋላጮች ጥበቃ ትንተና እና ተዛማጅነት ያለው የመረጃ አሰባሰብ እና ትንተና እቅድ መልካም ተሞክሮዎችን ለመድገም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች ላይ ልዩ ክትትል ማድረግ የአድቮኬሲ ውጤቶችን ለመከታተል ከተለዩ ልዩ አመልካቾች ጋር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። መረጃዎችን በሚሰበስቡበት ጊዜ መረጃ የሚያበረክቱ አካላት በፈቃዳቸዉ ስለመሳተፋቸው ውሳኔ ለመስጠት ሙሉ በሙሉ እውቅና እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው። በመረጃ ላይ የተመሰረተ ስምምነት ላይ ካልደረሱ በስተቀር የመረጃ ግላዊነት መብትን ማረጋገጥ እና መረጃ የሚያቀርቡትን ሰዎች ማንነት መጠበቅ የማንኛውም ድርጅት ኃላፊነት ነው። በመረጃ አሰባሰብ ሂደት የትኛውንም ተሳታፊ ለማንኛውም የደህንነት ስጋት እንዳይጋለጥ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ሴቶችን ጨምሮ በተለምዶ ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች ሙሉ በሙሉ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ውስጥ እንዲወከሉ እና በተቻለ መጠን የተገኙት የመረጃ ስብስቦች በፆታ እና በሌሎች ተዛማጅ ምድቦች እንዲከፋፈሉ የተቻለውን ሁሉ ያድርጉ። በተለምዶ ከሚገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ተሳታፊዎች እንዲካተቱ ለማድረግ ሁሉንም ምክንያታዊ ጥረቶችን ማድረግዎን ያረጋግጡ።

የጥበቃ ተሟጋች የውጤት ምዘናዎች ከግምገማ ዳሰሳ ጥናቶች እና ከውስጥ ትንተና በተገኙ የጥራት መረጃዎች ላይ በእጅጉ ይመረኮዛሉ። እንደነዚህ ያሉት ዘዴዎች በዐውዱ ውስጥ ለውጥ እንዴት እየተፈጠረ እንደሆን፣ የአድቮኬሲ ጥረቶች ለዚህ ለውጥ በምን መልኩ አስተዋፅዖ እያበረከቱ እንደሆነ፣ አጠቃላይ ውጤታማነትን ለመገምገም እና የማስተካከያ ሂደቶችን ለመደገፍ ግንዛቤን ይሰጣሉ።

የጠራ መረጃን ለመሰብሰብ ሌላው አስፈላጊ ዘዴ ከሙግት ቡድኑ ጋር መወያየት ነው። አጋዥ#6 ለማብራራት መመሪያ ነው። ቡድኑ በአድቮኬሲ ጥረቱ ሂደት ውስጥ ጉልህ የሆነ የፖሊሲ ስኬት ሲገኝ መመዝገብ አለበት። አጋዥ #7 እንደዚህ አይነት ስኬቶችን እንዴት መያዝ እና ማጋራት እንደሚቻል ያሳያል።

በመጨረሻም የውጤት ስብሰባ (Outcome Harvesting) ለክትትል፣ ግምገማ እና ለመማር (MEL) እንዲሁም በመካሄድ ላይ ባሉ የተጋላጮች ጥበቃ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ውስጥ በጣም ጠቃሚ ዘዴ ነው። በዚህም የውጤት አሰባሰብ ሂደት ወቅት ለለውጡ ያለውን አስተዋጾ ለመገምገም ውጤቶች ተሰብስበው ወደ ኋላ በአመላካችነት ጥቅም ላይ ይውላሉ።


አንዳንዴ ለውጡ አሉታዊ እና/ወይንም ከራሳችን አስተዋጽዖ ጋር ሊያያዝ የማይችልበት ሁኔታ ይፈጠራል። ይልቁንም ከሌሎች የለዉጥ ተዋናዮች ጋር ሊገናኝ ይችላል። ይህ ሂደት የውጤት ካርታ ዘዴ (Outcome Mapping) ተብሎም ሊጠቀስ ይችላል። በውጤት አሰባሰብ ላይ ሙሉ አጋዥ ስልጠና በCIVICUS ድህረ ገጽ ላይ ይገኛል። ለተገኘው ለውጥ የድርጅቱን አስተዋፅዖ እንዴት መገምገም እንደሚቻል ላይ ተጨማሪ እገዛን ለማግኘት እባክዎን አጋዥ ቁጥር 7 እና 8ን ይመልከቱ።

# የጥበቃ ሙግት ውጤቶችን ለመለካት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች

የተጋላጮች ጥበቃ የሙግት እንቅስቃሴዎችን መለካት ልዩ ተግዳሮቶችን ይዞ ይመጣል። ለምሳሌ ተሚጋችነት ብዙውን ጊዜ ሕግን ለመለወጥ ወይም አዲስ ሕጎችን ለመፍጠር ያለመ ከሆነ እነዚህም የረጅም ጊዜ ዓላማዎች የሚኖራቸዉ በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜ ሊለኩ የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ - ምናልባትም አድቮኬሲ በተሰራበት ዘመን ውስጥ እንኳን የተፈለገዉ ለዉጥ እዉን ላይሆን ይችላል። የጥበቃ ተሚጋችነት እንደ ሰብአዊ መብቶች ያሉ ረቂቅ የጋራ ጥቅምን ሊያበረታታ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የአድቮኬሲ ዘመቻው ዓላማ መከላከል ወይም የድርጊት አለመኖር ሊሆንም ይችላል (ይህም ማለት 'አሉታዊ' ውጤት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል)። በመጨረሻም እንደ ቀጥታ ስብሰባዎች ያሉ ቦታዎች ላይ መሚገት ግልጽነት ሊጎለው ስለሚችል ዉጤቱን መከታተል አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።

በተጨባጭ እና በይበልጥ የሚታዩ እና በቀላሉ የሚለኩ የተጋላጮች ጥበቃ አድቮኬሲ ውጤቶችን አጽንኦት መስጠት የበለጠ ተመራጭ ሊያደርገዉ ይችላል። ነገር ግን እንደ የማህበራዊ ሚዲያ እንቅስቃሴ እና በስብሰባ ላይ ያሉ ታዳሚዎች የመሳሰሉ ውጤቶች በተወሰነ አውድ ውስጥ ብቻ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። በእነዚህ ስኬቶች ላይ ማተኮር እውነተኛ ለውጥን አይገመግምም። ተፅዕኖ (Impact) በቀላሉ ሊለካ ከሚችለው ነገር በታች የመከሰት አዝማሚያ አለው። ለዚህም ነው በአድቮኬሲው ሂደትም ሆነ መጨረሻ ላይ ለስኬት የሚዳርጉ አስተዋጾዎችን የሚገመግም ጥራት ያለው መረጃ መመዝገብ እና መተንተን በጣም አስፈላጊ የሚሆነው።

*ምስል 4.3፡* **የእሴት አይስበርግ**




ከሽላንገን፣ ርሆንዳና ጂም ኮይ(2014). The Value Iceberg: Weighing the benefits of advocacy and campaigning የተወሰደ

ብዙ ጊዜ አብዛኛው የጋራ ጥረቶችን አሰባስበን ጉልበተኛ የአድቮኬሲ ስልቶችን እና እቅዶችን በመንደፍ እና ወደ ተግባር እንገባለን። ለለውጥ የምናደርገውን አስተዋጾ ለመለካት የጋራ ክትትል፣ ግምገማ እና መማር (MEL) እቅድ ማውጣት ከብዙ ጊዜ በኋላ ወይም በጭራሽ አይደረግም። ይህ ማለት የተፅእኖአችን ፋይዳ እና ለጠንካራ የመከላከል ውጤቶች እንዴት እንደሚያበረክት ለማሳየት እንደ ተሚጋችነት ያመለጠ እድል ማለት ነው። ከመጀመሪያው ጀምሮ

ቀላል የMEL እቅድ ለማዘጋጀት በቂ ጊዜ እና ቦታ ማመቻቸት ተጠያቂነትን፣ ተአማኒነትን እና ተነሳሽነትን በረጅም ጊዜ ውስጥ ለማስቀጠል የሚያስፈልገንን ጥረት ከማጎልበት አንፃር ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

## የግምገማ እና የመማር (MEL) እቅድን በመተግበር ሂደት ውስጥ የሚነሱትን አነስተኛ ተጨባጭ የየተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ውጤቶችን እንዴት መለካት እንደሚቻል የሚነሱ ጥያቄዎችን ለመፍታት ጠቃሚ ምክሮች

**1. ተግዳሮት፡ ፖሊሲ/ህጉ ገና ካልተቀየረ ስኬትን እንዴት መለካት ይቻላል?**

***ጠቃሚ ምክር:*** *የፖሊሲ ዓላማዎችን ብቻ አይቆጣጠሩ። በአድቮኬሲ ስትራቴጂ ውስጥ የተቀመጡትን ውጤቶች ይመልከቱ።*

***2. ተግዳሮት ፡- በአድቮኬሲ ሂደት ውስጥ መሻሻልን ለመለካት አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም ውጤቶቹ ተጨባጭ አይደሉም።***

***ጠቃሚ ምክር፡*** *ተጨባጭነት ምንም ይሁን ምን ጠቃሚ የአድቮኬሲ ውጤቶችን ለማሳየት ማስረጃዎች ይኖራሉ። ለምሳሌ የሕዝብ አመለካከት ለውጥ ጠቋሚው በዋና ዋና የመገናኛ ብዙሃን የተሰራጩ አዎንታዊ ጽሑፎች ወይም የአስተያየት መሰብሰቢያ ሰርቬይ ሊሆን ይችላል።*

*ውጤቱ ጉዳዩን ወደ ፖለቲካ አጀንዳ እያደረሰው ከሆነ ይህን የሚያሳየው በፓርላማ ውይይቶች መጨመር ወይም መንግስት በጉዳዩ ላይ ባለድርሻ አካላትን በመጋበዝ ሲያወያይ ነው። ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር የጠነከረ ግንኙነት ስለመሆኑ ማስረጃዎች ተገናኝተው ለመወያየት ወይም ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ በመጋበዝ ሊሆኑ ይችላሉ።*

***3. ተግዳሮት ፡- አወንታዊ ለውጦች በአድቮኬሲው ወይም በሌሎች ምክንያቶች የተገኙ መሆናቸውን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው።***

***ጠቃሚ ምክር፡*** *ከባህሪው ይልቅ ድርሻዉን ይገምግሙ። ፖሊሲዎችን እና ህጎችን ለማውጣት ብዙ ምክንያቶች ይኖራሉ እንዲሁም አብዛኛው ሂደቱ ከእይታ በራቀ ሁኔታ ውስጥ ይከሰታል። በመሆኑም በመጨረሻው ውሳኔ፣ ፖሊሲ ወይም ህግ ውስጥ የአንድ ድርጅት ሚና ሙሉ በሙሉ ለመረዳት የማይቻል ሊሆን ይችላል።*

*በተደረገው ክትትል በተሰበሰቡ ማስረጃዎች ላይ በመመስረት ምን እና ለምን አስተዋጽኦ እንዳደረጉ እንደሚሰማዎት ወሳኝ ግምገማ ያድርጉ። ይህ እንደ ተገቢነቱ ሌሎች በግኝቶቹ ላይ እንዲወያዩ እና እንዲደግፉ ወይም ውድቅ እንዲያደርጉ እድል ይፈጥርላቸዋል።*

- *ስለአስተዋጽኦዎ ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት በመጠየቅ ምዘናውን ቅልቅል ያድርጉት። ከዚያ በአመለካከታቸው ውስጥ መመሳሰሎችን ይፈልጉ።*
- *አድቮኬሲዉ ያመጣዉን አስተዋጽኦ የሚያመላክቱ ከፖሊሲ አውጪዎች የተሰጡ ደብዳቤዎች እና መግለጫዎች በጥንቃቄ መዝግበው ያቆዩ።*
- *የድርጅትዎን ስም፣ ሪፖርት፣ ስራዎች የሚጠቅሱ ሁኔታዎችን የሚያሳዩ ጎግል ማንቂያዎችን ወይም ተመሳሳይ መፈለጊያ መሳሪያ ያዘጋጁ።*

***4. ተግዳሮት ፡ ስትራቴጂው በአፈጻጸም ወቅት መቀየር ሲገባው በተለዋዋጭ ለውጦች ምክንያት ለውጡን ለመከታተል አስቸጋሪ ነው።***

***ጠቃሚ ምክር፡*** *አድቮኬሲ ቀጥተኛ መንገድ ስላልሆነ በተጠቀመበት ስልት፣ አካሄድ ወይም ታክቲክ ላይ የተደረጉ ለውጦችን መመዝገብ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ከእያንዳንዱ ስብሰባ በኋላ የነበረን የተሳትፎ ሁኔታ ለመመዝገብ እና ከእያንዳንዱ ክስተት በኋላ አዲስ የተፈጠሩ ግንዛቤዎችን ለመቅረጽ መረጃን ይሰብስቡ። እነዚህ መዝገቦች አስተዋጽዖ ያደረጉ ምክንያቶችን ወደፊት ለመተንተን ይረዳሉ።*

***ከ*** *Advocacy: A toolkit for small NGOS, INTRAC*[41] ***የተወሰደ***

ሞጁል

5

# የተጋላጮች ጥበቃ አድቮኬሲ ስጋት ቁጥጥር (Protection Advocacy Risk Management)

የሰብአዊ ድጋፍ ተግባራት ብዙውን ጊዜ መረጋጋት በማይታይበት፣ ተለዋዋጭ በሆኑ አውዶች ውስጥ እና ሰዎች ከበርካታ ምንጮች ማለትም የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የግዳጅ መፈናቀል፣ የትጥቅ ግጭት፣ ብጥብጥ እና/ወይም የሰብአዊ መብት ረገጣ ጋር ተያይዘው በሚመጡ የየተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶችን በመጋፈጥ ሁኔታ ውስጥ ይከወናሉ። እነዚህ አውዶች በመረጃ ላይ የተመሰረተ የአደጋ ስጋት ቁጥጥርና አስተዳደርን አስቸጋሪ እንደሚያደርግ ነገር ግን ይበልጥ አስፈላጊ እንደሆነ ያሳያሉ። ከጥበቃ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ መሟገት ብዙውን ጊዜ ሚስጥራዊነት ያላቸው ወይም አወዛጋቢ ጉዳዮችን ያካትታል። ነገር ግን በድርጅቱ፣ በሰራተኞች፣ በአጋሮች እና በፕሮግራሞች ላይ ሊደርሱ ስለሚችሉ አደጋዎች መሟገትን ማስወገድ ሳይሆን ድርጅቶችን በመለየት፣ በመተንተን እና ምላሽ በመስጠት ተያያዥ አደጋዎች ላይ የተመረኮዙ የአድቮኬሲ ስልቶችን እና ዘዴዎችን በጋራ እንዲሰሩ ማነሳሳት አለባቸው። በስተመጨረሻ አደጋዎች እና ስጋት አስተዳደር ማለት አደጋዎችን መገምገም፣ ስለስጋቶች ያልተጨበጠ መላምት አለመስጠት እና በመቀጠልም ሊከሰቱ የሚችሉ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለመቀነስ በንቃት መቆጣጠር እና መቀነስ ነው።

### የአደጋ ስጋት አስተዳደር፡ የሲቪል ማህበረሰብ ጉዳት መከላከል እና ምላሽ ምን የተለየ ነገር አለው?

> ከጉዳት መከላከል እና ምላሽ ጋር በተገናኘ የሙግታ ስራዎችን ማካሄድ ከርዕሰ-ጉዳዩ አሳሳቢነት፣ የታጠቁ ሀይሎች ተሳትፎ፣ ለግጭት አካባቢዎች ካለው ቅርበት ወይም የመረጃ አይነቶች ጋር ተያይዘው በሚመጡ ሁኔታዎች ድርጅቶችን ወይም ተጠቃሚ ማህበረሰቦች ተጨማሪ አደጋዎችን ሊያስከትል ይችላል። [42] .

ከ*የሲቪክ የተሟጋችነት መመሪያ የተወሰደ*.

ስጋቶችን ወደፊት ሊከሰቱ ከሚችሉ ጎጂ ክስተቶች ወይም አደጋዎች እና ከሚያስከትሏቸው ተጽእኖዎች ጋር በተያያዘ መረዳት ይቻላል። ብዙ ኤጀንሲዎች (እና እንዲሁም ቢዝነሶች) በ2018 በአለም አቀፉ የደረጃ አሰጣጥ ድርጅት (አይኤስኦ) የቀረበውን የስጋት ትርጓሜ ቀብለዋል። ይህ ትርጉም ስጋትን በዓላማዎች ላይ እርግጠኛ ያለመሆን ውጤት እንደሆነ ይገልፃል። ውጤቱም አወንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆን እንደሚችል እና በጊዜ ሂደት ሊለወጥ እንደሚችል መረዳት አስፈላጊ ነው። አሁን ላይ ስለወደፊቱ ካለን ውስን እውቀት ጋር ስለሚዛመድ የጥርጣሬው መጠን በጊዜ ሂደት ይለወጣል። በተጨማሪም ስጋቶች ከዓላማዎች (ሰዎች፣ ነገሮች፣ ድርጅቶች፣ ወዘተ) ጋር የተገናኙ ናቸው። ይህም ስጋቶችን ከአጠቃላይ አለመረጋጋት ይለያቸዋል ምክንያቱም ሁሉም እርግጠኛ ያልተሆነባቸው ሁኔታዎች በሚመለከታቸው ድርጅቶች፣ ሰራተኞቻቸው፣ አጋሮቻቸው ወይም ፕሮግራሞች ላይ ተጽእኖ ስለማይኖራቸው። ስለዚህ በነዚህ አላማዎች ላይ ተጽእኖ በሚያሳድሩ የስጋት ክስተቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ስጋቶችን አጠቃለው ሲገልጹ በተለያዩ ኤጀንሲዎች ውስጥ የዓላማዎች፣ የእሴቶች፣ የአቀራረብ፣ የባለቤትነት ወዘተ ልዩነቶች እንዳሉ ያስታውሱ፣ ይህም ስጋቶች ወይም የአደጋ ክስተቶች በተለየ መልኩ ግንዛቤ እና አረዳድ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጓቸዋል።

የስጋት አስተዳደር የወደፊት ጉዳቶችን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚደረጉ ጥረቶችን ያመለክታል። በዚህ ጥረት ውስጥ የተለያዩ ሴክተሮችን የሚያግዙ ብዙ የተለያዩ አቀራረቦች እና ማዕቀፎች አሉ። ለምሳሌ የድርጅት ስጋት አስተዳደር (Enterprise Risk Management) ለአደጋ ስጋት አስተዳደር በአጠቃላይ ተቀባይነት ያለው ማዕቀፍ ነው። በተጨማሪም አደጋዎችን ለመቀነስ የሚረዱ ሌሎች አካሄዶችም አሉ ለምሳሌ የመከላከል አካታችነት፡ ይህም የጥበቃ መርሆዎችን በማካተት እና በሰብአዊ ርዳታ ውስጥ ትርጉም ያለው ተደራሽነትን፣ ደህንነትን እና ክብርን ማስተዋወቅ እንዲሁም አድልዎ፣ ጥቃት፣ ቸልተኝነት እና ብዝበዛን ለመከላከል ይረዳል። አንዳንድ ድርጅቶች ለምሳሌ ሴፍ ፕሮግራሚንግ (Safe Programming) 46 የሚባል አካሄድ ይጠቀማሉ። የዚህ ዓላማ የሰብአዊ ድጋፎች፣ ድርጊቶች እና ፕሮግራሞች ሳያውቁ በሰዎች ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ፣ ስራቸውን የሚደግፉ እሴቶችን፣ ደረጃዎችን እና ደንቦችን እንዳያበላሹ ለማድረግ ንቁ እርምጃዎችን ያካተተ ነው። .

የግጭት አገናዛቢነት (Conflict Sensitivity) እና ምንም ጉዳት ያለማድረስ መርህ (Do No Harm)47 ያልተጠበቁ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ለመቀነስ ሌሎች መንገዶች ናቸው። ይህ ሞጁል በተወሰነ ማዕቀፍ ወይም አቀራረብ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን የጋራ ጉዳዮችን እና የአደጋ

ስጋት አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት በተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ውስጥ መሳተፍ አደጋዎችን መቆጣጠር ቀጣይነት ያለው ሂደት መሆኑን ለማጉላት ይፈልጋል።

የአደጋ ስጋት ምዘና ሂደቶች የሙግት ስትራቴጂ እቅድ ሂደት ዋና አካል መሆን ያለባቸው ሲሆን የተለያዩ የአሰራር ልምዶችን እና እውቀቶችን የሚወክሉ የተለያዩ ግለሰቦችን እና ድርጅቶችን ማካተት አለባቸው። ጥሩ የአደጋ ስጋት ግምገማ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ጥረት ማድረግ አለበት:

- ምን ሊከሰት ይችላል?
- የመከሰት እድሉ ምን ያህል ነው?
- ሊያስከትል የሚችለው ተጽእኖ ምንድን ነው?
- ጉዳት ሊደርስባቸው የሚችሉ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው (ለምሳሌ ሰራተኞች፣ ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች፣ አክቲቪስቶች፣ ደጋፊዎች፣ አጋሮች)?
- ሊቃወሙ የሚችሉ አካላት (በሙግት ተግባር ውስጥ ለሚሳተፉ ሰዎች እና/ወይም አብረዉን የሚሰሩ ሰዎች ስጋት የሚፈጥሩ) እና በሙግት ሂደት ውስጥ አጋሮች እነማን ናቸው?
- የአደጋ ስጋቶችን እንዴት መከላከል፣ ማቃለል ወይም ማስተዳደር ይቻላል?
- ጥቅሞቹ ሊከሰቱ ከሚችሉ አደጋዎች ይበልጣሉ?
- አደጋዎችን ለመቀነስ ምን እርምጃዎች ሊወሰዱ ይችላሉ?

## አውዱን መረዳት (Understanding the Context)

በአደጋ ስጋት አስተዳደር ውስጥ ካሉት የመጀመሪያ እርምጃዎች አንዱ የሙግት ስልቱ የሚዘረጋበትን አውድ እና ስፋት መተንተን ነው። ይህ የዐውደ ትንተና ከዐውዱ ጋር የተያያዙ ብዙ ነገሮችን በመመርመር የመከላከል ትንተና፣ የባለድርሻ አካላት ካርታ እና የኃይል ሚዛን ትንተና ላይ ተመርኩዞ ይገነባል። እነዚህ ከሚከተሉት አንዳንድ ምክንያቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሊያካትቱ ይችላሉ። እነዚህም በተለያዩ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች፣ በከተማ እና በገጠር አውድ እና በመሳሰሉት መካከል ሊለያዩ ይችላሉ።

### በአዉድ ትንተና ውቅት ሊታሰብባቸው የሚገቡ ሁኔታዎች

- ወቅታዊ ጉዳዮች፣ ታሪክ፣ የህግ ማዕቀፎች፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ወጎች እና የስርዓተ-ፆታ ደንቦች
- ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ነጎሳ እና ሌሎች ጥምረቶች፣ እኩልነት እና ልዩነቶች
- የደህንነት ደረጃና አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሁኔታዎች
- ለተለያዩ ብሔረሰቦች እና አናሳ ቡድኖች፣ ጾታዎች፣ የሃይማኖት ቡድኖች እና የውጭ ዜጎች (ምዕራባዊ፣ ዲያስፖራ ወይም አካባቢያዊ) ያለው አመለካከት እና አስተሳሰብ
- ለሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች፣ የእርዳታ ኤጀንሲዎች ወዘተ የሚሰጠው አመለካከት እና አስተሳሰብ
- ሙስናን ጨምሮ ሌሎች የአስተዳደራዊ ጉዳዮች

በዚህ ሂደት ውስጥ ከተገለጸው በተጨማሪ የተለያዩ ተዋናይ አካላት ፍላጎቶች/ዓላማዎች አንድ ላይሆኑ እንደሚችሉ ማስተዋል እና በተዋንያን መካከል ያለውን ትስስር እና መስተጋብር ከኃይል ሚዛን ትንተና አንጻር መለየት እንዲሁም እነዚህ ግንኙነቶች በድርጅትዎ እና በአጋሮችዎ ላይ እንዴት እንደሚተሳሰሩ መገምገም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።
የዐውድ ትንተና በሚከውኑበት ጊዜ በዐውዱ ውስጥ በተለያዩ ምድቦችን መከፋፈል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ይህም ለምሳሌ የፔስትል (PESTLE) ትንተና አቀራረብን በመጠቀም ሊተገበር ይችላል። ፔስትል (PESTLE) የሚለው ምህፃረ ቃል ፖለቲካ፣ኢኮኖሚክስ፣ማህበራዊ፣ቴክኖሎጂ፣ህግን እና አካባቢን ያካትታል። ፔስትል ድርጅቶች ውጫዊ ሁኔታዎችን እንዲረዱ የሚያግዝ እና ስለ ሰፊው አውድ ስልታዊ ግንዛቤ የሚሰጥ የአስተዳደር ማዕቀፍ እና የምርመራ መሳሪያ ነው። ይህም ትንታኔ ሲያካሂዱ ለእያንዳንዱ ምድብ ችግሮችን፣ ተዋናዮችን፣ የግንኙነት ማእቀፎችን፣ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን፣ የሃይል ሚዛንን፣ ቁጥጥርን፣ አላማዎችን ወዘተ መለየት እና እነዚህ በተመረጡት አላማዎች ላይ ምን አይነት ተፅእኖ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ መለየት እጅግ ጠቃሚ ነው። እባክዎ በፔስትል (PESTLE) ላይ ተጨማሪ ለማግኘት አጋዥ ቁጥር 9 ይመልከቱ።

## የአደጋ ስጋቶች ትንተና (Risk Analysis)

በዐውዱ ትንታኔ ላይ በመመስረት ሂደቱን በሦስት ደረጃዎች በመከፋፈል ራሱን የቻለ የአደጋ ስጋት ትንተና ሊጀመር ይችላል። ይህም የአደጋ ስጋትን መለየት፣ የአደጋ ስጋት ግምገማ እና የአደጋ መቆጣጠር ስልቶችን ያካትታል።

የተሳታፊ ተዋናይ ካርታ፣ የሃይል አሰላለፍ ካርታ እና የአውድ ትንተናን ተከትሎ (ለምሳሌ የPESTLE አካሄድን በመጠቀም) አንዳንድ ስጋቶች እና አደጋዎች አስቀድመው ተለይተው ሊታወቁ ይቸላሉ። በመሆኑም ከአጋሮችና ደጋፊዎች ጋር በሚደረግ የጋራ ውይይት በማድረግ ትንተናዉን የበለጠ ተአማኒ ማድረግ ይቻላል፡ ለምሳሌ ቀላል የአደጋ ስጋት መዝገብ በመጠቀም ወይም በነጭ ሰሌዳ ላይ መሰረታዊ ዝርዝር መፃፍ ሁሉም አደጋዎች ግምት ውስጥ መግባታቸውን ለማረጋገጥ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ተፅእኖ ከመፍጠር ወይም ከሙግት ጋር የተያያዙ በጣም የተለመዱ የአደጋ ስጋት ዓይነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- **ቀጥተኛ የደህንነት ስጋቶች፡** እነዚህም የመገናኛ መሳሪያዎችን በመጠቀምና አካላዊ ክትትል፣ በቤትና ንብረት ላይ የሚደርስ ጉዳት፣ ዛቻ እና ማስፈራራ፣ የዘፈቀደ እስራት ወይም ክስ፣ አካላዊ ጥቃቶች፣ አፈና ወይም ግድያ ያካትታሉ።

- **ፖለቲካዊ ስጋቶች፡** እነዚህ በድርጅትዎ እና/ወይም በአጋሮችዎ እና ማህበረሰቦች ላይ በመንግስት በኩል የሚደርሱ ጫናዎችን፣ የስራ እንቅስቃሴ ገደቦችና ማስፈራሪያዎች ያካትታሉ።.

- **ከመልካም ስምና ዝና ጋር የተያያዙ ስጋቶች፡** እነዚህ መልካም ያልሆነ የሚዲያ ወይም የህዝብ አቀባበልን፣ የማህበረሰብ ወይም ተቋማዊ ገቢ ማጣትንና ከሌሎች የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች፣ ከሀገር አቀፍ እና ከአለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያለው ግንኙነት መበላሸትን ያካትታሉ።

- **ከህግ ጋር የተያያዙ ስጋቶች፡** እነዚህም ስም ማጥፋትን (የአንድን ሰው ስም የሚጎዳ ወይም ሊጎዳ የሚችል ማንኛውም ነገር)፣በድርጅትዎ ወይም በአጋሮችዎ ላይ ሊወሰድ የሚችል ህጋዊ እርምጃና የካሳ ጥያቄዎችን.ያጠቃልላል።

- **የተአማኒነት ስጋቶች፡** ተፅዕኖው ሊመለከቷቸው በሚፈልጓቸው ለውጦች ላይ ትንሽ ወይም ምንም ተጽእኖ ከሌለው በድርጅቱ ሰራተኞች፣ ለጋሾች፣ አጋሮች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት መካከል የትችት እና መልካም ስምን የመጉዳት አደጋ ስጋት ይኖራል።

*በአድቮኬሲ ዘመቻ ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የተሳተፈ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ አደጋ አይደርስበትም። እንደ አንድ ሰው ጾታ፣ ዕድሜ፣ ዘር፣ ዜግነት እና ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያሉ ምክንያቶች ጥቃትን እና እንግልትን ጨምሮ ምላሽ ሊገጥማቸው በሚችልበት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ።*

*በተለይም ሴት የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች እና ሴት አክቲቪስቶች እኩል ያልሆነ የስልጣን እና የሃብት ድልድልን ስለሚፈታተኑ እና ብዙ ሰዎች ሴቶች ድምፃቸውን እንዲያሰሙ እና ተሰሚነት እንዲያገኙ ሲጠይቁ ተቀባይነት እንደሌለው ስለሚቆጥሩ አጸፋ ይደርስባቸዋል። በእርግጥ የሴቶች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የሚያጋጥሟቸው ጥቃቶች ጉልህ ድርሻ ከቤተሰቦቻቸው እና ከማህበረሰቡ የሚመጣ ሲሆን በአብዛኛው ለውጭ ሰዎች የማይታይ ሊሆን ይችላል።*

*በአድቮኬሲ ስራዎች ወይም በአጠቃላይ የመካላከል ስራ ላይ ለሚሳተፉ ድርጅቶች ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። የመንግስታቱ ድርጅት ኤጀንሲዎች ከአለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይም የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የተለየ ሥጋት ሊጋፈጡ እንደሚችሉ ሁሉ ሃገራዊ ድርጅቶችም ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች የተለየ ሥጋት ይገጥማቸዋል።*

*ይህም የአደጋ ስጋትን የመቀነስ ስትራቴጂዎችን በመንደፍ እና በመተግበር ሂደት ላይ የተለያዩ የግለሰቦች፣ ማህበረሰቦች እና ድርጅቶች ማሳተፍ እንደሚያስፈልግ ያሳያል።*

እያንዳንዱ የተገለጸው አደጋ ከቦታ፣ ማን ወይም ምን አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል እና ምን ሊያስከትል እንደሚችል መገምገም ይኖርበታል። የአደጋ ስጋት መፈጠር ግዴታ አንድን ቡድን ወይም ድርጅት በተመሳሳይ ሁኔታ ተጽእኖ ያደርጋል ማለት አይደለም። የአደጋ ስጋት ምዘና ስርዓት አደጋ የመከሰቱ እድልን ለመገመት የሚረዳ እና ከተፈፀመ የችግሩን ክብደት ለመቀነስ የሚያስችል ታዋቂ አካሄድ ነው። ይህ አደጋ ስጋት ማትሪክስ (Risk Matrix) በመባልም ይታወቃል። በእነዚህ ሂደቶች ውስጥ ለማስተዳደር አመቺ ያልሆኑ ወይም በጣም ብዙ የሆኑ በርካታ የአደጋ ስጋቶች ሊገኙ ይችላሉ። ይህም

እንደ ልዩ አውድ እና በተካተቱ አካላት የስጋት ትኩረት ላይ በመመስረት ትኩረት ሊደረግባቸው በሚችሉት ክስተቶች ላይ በተለይ ከከባድ ተፅዕኖ ጋር የተያያዙ ስጋቶች ወይም የሁለቱም ጥምርነት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል፡ እነርሱም ከፍተኛ የመከሰት እድል እና ከፍተኛ ተፅዕኖ የማሳደር።

# የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስልቶች

ስጋቶቹ እና ማን ወይም ምን የስጋቱ ተጎጂዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ከተለዩ እና የትኞቹ አደጋዎች የትኩረት ዒላማ መሆን እንዳለባቸው ውሳኔዎች ከተላለፉ በኋላ የአደጋ ስጋት ስትራቴጂ መቀረጽ አለበት። በአጠቃላይ አራት የተለያዩ ስልቶች አሉ። እነርሱም መቀበል/መታገሥ፣ ማስወገድ/ማቋረጥ፣ ማስተላለፍ እና መቀነስ/ማሳሳት ናቸዉ።

*ስጋቱ እራሱን እንደ አወንታዊ እድል ሲያቀርብ ድርጅቶች የበለጠ በመጠቀም፣ በመሞከር፣ በማበልጸግ ወይም በመቀበል በተለየ መንገድ ሊያስተዳድሩት ይችላሉ።*

*ስጋትን መቀበል ተጽእኖዉን አይቀንስም። ይህ ማለት ግን በተመሳሳይ ጊዜ ችላ ማለት አለብን ማለት አይደለም። ሁሉም ስጋቶች ያለማቋረጥ ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል። ስጋትን ማስወገድ ወይም ማቋረጥ የመቀበል ተቃራኒ ነው። እዚህ ላይ ስልቱ ድርጊቶቹን (የአድቮኬሲ ስልቱን) ማቆም እና ተመሳሳይ አላማዎችን ለማሳካት አዳዲስ መንገዶችን መፈለግ ነው።*

*ስጋትን ማስተላለፍ ማለት ባለቤትነትን በሆነ መንገድ ለሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ ማለት ነው። የተለያዩ ድርጅቶች በጋራ በመሆን ሙግት ላይ ሲሰማሩ የአደጋ ስጋትን ማስተላለፍ በመካከላቸው ያለውን የአደጋ ስጋት መጋራት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል ምክንያቱም አንዳንድ ድርጅቶች የአድቮኬሲ ጥረቱን ከፊት ሁኖ ለመምራት የተሻሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ። እንዲሁም ሌሎች ደግሞ በሁለትዮሽ ስብሰባዎች እና ለስላሳ ዲፕሎማሲ ላይ እንዲያተኩሩ እና አንዳንዶቹ በመረጃ አሰባበሰብ እና ትንተና ላይ ለማተኮር ስለሚያስችላቸው።*

*ስጋትን መቀነስ ወይም ማስወገድ ማለት የአደጋውን የስጋት እድል እና/ወይም ተፅእኖ ተቀባይነት ወደሚያገኝ ደረጃ የመቀነስ ስልት ማለት ነው።*

ስጋቶችን የመፍታት ስትራቴጂ ከተነደፈ እና በመዝገብ ውስጥ ከተቀመጠ በኋላ ቀሪ ስጋቶች አሁንም ሳይለዩ ሊቀሩ ይችላሉ። ይህም እንደገና መፈተሽ እንዳለበት ይመከራል። በተጨማሪም የትኛውም የተመረጠ ወይም የተተገበረ ስትራቴጂ ሌሎች አደጋዎችን እንደሚጨምር ወይም አዳዲስ ችግሮችን ሊፈጥር እንደሚችል መቀበል አስፈላጊ በመሆኑ ቀሪዎቹን እና ተጨማሪ ስጋቶችን እንዲሁም የተወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነት ቀጣይነት ባለው መልኩ መከታተል አስፈላጊ እና ቀጣይነት ያለው የስጋት አስተዳደር ዑደት አካል ነው።

በአስቸጋሪ እና በተከለከሉ አውድ ውስጥና ስልጣንን የያዙትን ታሳቢ ያደረገ የአድቮኬሲ ዘመቻ ማካሄድ በተፈጥሮው አደገኛ ነው። እነዚህ ስጋቶች የተለያዩ ርምጃዎችን በመውሰድ ተያይዘው በሚመጡ ስጋቶች እንዲሁም ምንም ካለማድረግ እና ዝም በማለት ምክኒያት በድርጅት፣ በፕሮግራሞች፣ በአጋር አካላት እና ዜጎች ላይ ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎች እና ኢፍትሃዊነት እንዲከሰት ወይም እንዲቀጥል ከመፍቀድ አኳያ ለሚነሱ ስጋቶች ጋር መመዘን አለበት።

በአድቮኬሲ እና በተያያዥ ስጋቶች ዙሪያ ያሉ ውስብስብ ጉዳዮችን ማሰስ ወደ ተግባር ለመግባት ማበረታቻን ለመፍጠር እና በቅጡ ያልታዩ የአደጋ ግንዛቤዎችን ተቋቋሞ ለመስራት የአመራር ድጋፍን ይጠይቃል። ጥሩ የአደጋ ስጋት አስተዳደር በመረጃ የተደገፈ ዉሳኔ በፍጥነት፣ በብቃት እና ያለማቋረጥ በቀጣይነት እና ተደጋጋሚ የሚጠይቅ ቢሆንም የአደጋ ስጋቶችን ለመቆጣጠር እና ለመቀነስ ከሁሉም የአድቮኬሲ አጋሮች እና ተባባሪዎች ጋር በትብብር የተዘጋጀ ጠንካራ ትንታኔ እና እቅድ ይጠይቃል፣ ። በመጨረሻም በመከላከል አድቮኬሲ ውስጥ ሲሳተፉ የሚያጋጥሙትን ስጋቶች ለመቀነስ የሚያግዙ ሌሎች መሰረታዊ ሃሳቦች እና ድርጊቶች አሉ።

- **በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ማድረግ፡**- የመከላከል ጉዳዮችን ለአድቮኬሲ ስትመርጡ ምን ዓይነት የአደጋ ስጋት ደረጃ ተቀባይነት እንዳለው እና እንደሌለው በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ያድርጉ።

- **የአድቮኬሲ ስልትን በጥንቃቄ ያቅዱ፡** ጥልቅ እቅድ ማውጣት እና ጥሩ ትንተና ለአደጋ ስጋት አስተዳደር ወሳኝ ናቸው። ስለ ዐውዱ እና በውስጡ ስለሚንቀሳቀሱ ተዋናዮች፣ የአድቮኬሲ ኢላማዎችን ጨምሮ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረን ማድረግ ይኖርብናል። በእነዚህ ዒላማዎች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ውጫዊ እና ውስጣዊ ነባር ሁኔታዎችን ማወቅ አስፈላጊ ነው።
- **በማስረጃ ላይ የተመሰረተ ተሚጋችነት፡** ይህ የአድቮኬሲ ስጋት አስተዳደር መሰረቱ ነው። ተሚጋቹን የሚደግፉ የመረጃ እና የጥበቃ ስጋት ትንተናዎች በከፍተኛ ደረጃ መከናወን አለባቸው እንዲሁም ግምቶችን ወይም የግል መላምቶችን የለባቸውም።
- ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር **በትብብር መስራት** የአደጋ ስጋቶችን ለመቀነስ ይረዳል። በስትራቴጂካዊ ሂደቶች ውስጥ አብረን የምንሰራውን ሰዎች ማካተት ባለቤትነትን ለመፍጠር እና ማረጋገጫን ለመስጠት ይረዳል። እንዲሁም አድቮኬሲው የተጎዱትን ሰዎች ፍላጎት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥም ይረዳል።

**ምስል 5.1፡ የአደጋ ቅነሳ እቅድን በማዘጋጀት ሂደት ማስተዋል ያለብን ነገሮች**[50]

ምንም እንኳ የተሟላ ዝርዝር ባይሆንም ድርጅቶች የአደጋ ቅነሳ ዕቅድ ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸው ይሆናል።

**የመልእክት የማስተላለፊያ መንገድ ምርጫ፡** በተቃራሚ መልእክት ላይ የተመሰረቱ ስልቶች በተወሰኑ ሁኔታዎች በተለይም ደኅንነት እንደ ህዝባዊ ጥቅም በሚታይበት ጊዜ ለህዝብ ቁጥጥር እና ለምርመራ ተገቢነት በሚታይበት እና መንግስት ለትክክለኛ ትችቶች ትኩረት የሚሰጥ እና ምላሽ በሚሰጥበት ሁኔታ በጣም ውጤታማ ሊሆን ይችላል።

በሌላ ሁኔታ የሲቪል ማህበራት ወይም ጥምረት የመንግስት በቀል ወይም አሉታዊ የህዝብ ምላሽ ሊደርስባቸው ይችላል። በእነዚህ አጋጣሚዎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በባህሪ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ከሚችሉ ማህበረሰባዊ ወይም ተቋማዊ እሴቶች ጋር ለማጣጣም መልእክቶችን ማስተካከል፣ በራስ መተማመን እና መተማመንን ለማዳበር በግል መንገዶች መሳተፍ፣ አዎንታዊ እና መፍትሄዎች ላይ የተመሰረቱ መልዕክቶች ላይ ማተኮር፣ እና የፈጠራ፣ የጥበብ ዓይነቶችን ወይም መልቲሚዲያን መጠቀምን ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።

**የደህንነት እቅድ ማውጣት፡** የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች አግባብነት ያላቸውን ስጋቶች ማለትም የዲጂታል ስጋት አስተዳደርን (ኃላፊነት የሚሰማው የመረጃ አያያዝ እና ምስጠራ (encryption)፣ ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ቴክኖሎጂ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የግንኙነት ፕሮቶኮሎችን ጨምሮ) እና አካላዊ አደጋዎች (ተቋሞች፣ የሰራተኞች ጉዞ እና ደህንነት ክስተቶች ወይም እንቅስቃሴዎች) በበቂ ሁኔታ የሚሸፍን የደህንነት እቅድ ሊኖራቸው ይገባል።

ሰራተኞች በፀጥታ እቅድ እና በማንኛውም የአደጋ ጊዜ ምላሽ ሂደቶች ላይ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል, እና ድርጅቱ ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ የግንኙነት ስልት ሊኖረው ይገባል።

**የውስጥ ቁጥጥር፣ ግልጽነት እና አስተዳደር፡** በአንዳንድ ሁኔታዎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በጥብቅና እንቅስቃሴዎች ምክንያት ህጋዊ በቀል ወይም ስማቸው ላይ ጥቃት ሊደርስባቸው ይችላል።

የምርምር ዘዴዎችን እና ተግባራትን ጥራት እና ግልጽነት ማረጋገጥ እና ድርጅታዊ አስተዳደርን መከተል እና ህጋዊ ደንቦችን ማክበር ድርጅቱን ከዘፈቀደ ጥቃቶችን ሊከላከል ይችላል።

**ህብረትና የውጭ ድጋፍ፡** በአንዳንድ አካባቢዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስራቸውን ከአቻ ድርጅቶች ወይም ካልተጠበቁ አጋሮች (እንደ የንግድ ድርጅቶች ወይም የንግድ ቡድኖች) ጋር ማጣጣም ወይም ስራቸውን ከተወሰኑ አደጋዎች ለመከላከል የአለም አቀፍ ደጋፊዎችን ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ።

ከ*Civic Advocacy Guide የተወሰደ ምስል*.

ሞጁል

6

# ተጨማሪ አጋዥችን፣ ምንጮችንና መመሪያዎችን ማመሳከር

## ሞጁል አንድ


- CARE. *Emergency Toolkit: Developing an Advocacy Strategy and Taking Action.* https://www.careemergencytoolkit.org/topics-issues/2-advocacy/9-developing-an-advocacy-strategy-and-taking-action/
- CARE. (2014). *The CARE International Advocacy Handbook.* https://www.care-international.org/files/files/Care%20International%20Advocacy%20Handbook.pdf
- Global Protection Cluster. *Protection Analytical Framework.* https://globalprotectioncluster.org/field-support/Protection-Analytical-Framework
- Norwegian Refugee Council. *NRC Protection Resource Pack: Legal and Normative Frameworks*
- Oxfam. *Guide to Feminist Influencing*, Section 2 on Gender Analysis. https://oi-files-d8-prod.s3.eu-west-2.amazonaws.com/s3fs-public/file_attachments/oxfams_guide_to_feminist_influencing_english.pdf
- Oxfam. (2020). *Influencing for Impact Guide.* https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/handle/10546/621048/gd-influencing-for-impact-guide-150920-en.pdf?sequence=1
- IRC-DRC. *Protection Analysis Roadmap.* https://rescue.app.box.com/s/trfxly0dgspfp8msqwl1vufggzil22ff/file/896292800720
- IRC-DRC. *Problem Solving Approach Canvas.* https://rescue.app.box.com/s/trfxly0dgspfp8msqwl1vufggzil22ff/file/896279702440


## ሞጁል ሁለት


- BOND. *Theory of Change for Advocacy and Campaigns.* https://www.bond.org.uk/resources/theory-of-change-for-advocacy-and-campaigns
- CARE. (2014). *The CARE International Advocacy Handbook.* https://www.care-international.org/files/files/Care%20International%20Advocacy%20Handbook.pdf
- Global Protection Cluster. (2020). *GPC Collective Advocacy for Strategic Impact - 22 September 2020.* https://www.globalprotectioncluster.org/2020/07/22/gpc-collective-advocacy-for-strategic-impact/
- INTRAC. *Advocacy: A Toolkit for Small NGOs.* https://www.intrac.org/wpcms/wp-content/uploads/2022/06/BA-Advocacy-Toolkit.pdf
- Oxfam. (2019). *Oxfam's Guide to Feminist Influencing.* https://www.oxfam.org/en/research/oxfams-guide-feminist-influencing
- Oxfam. (2020). *Influencing for Impact Guide.* https://policy-practice.oxfam.org/resources/influencing-for-impact-guide-how-to-deliver-effective-influencing-strategies-621048/
- Oxfam. (2014). *Quick Guide to Power Analysis.* https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/

handle/10546/313950/ml-quick-guide-to-power-analysis-210214-en.pdf?sequence=1

- OHCHR. *Manual on Human Rights Monitoring. Chapter 31, 'Advocacy and Intervention with the National Authorities'.* https://www.ohchr.org/sites/default/files/Documents/Publications/Chapter31-24pp.pdf
- G. Mitchelle. (2022). *Engaging decision-makers on human rights issues: A Practice Guide for Civil Society.* Centre for Asia Pacific Refugee Studies (CAPRS), University of Auckland. https://cdn.auckland.ac.nz/assets/education/about/research/CAPRS/Final%20Practice%20Guide_%20Engaging%20Decision%20Makers%20GM%20CAPRS%20May%202022.pdf?mc_cid=1158399763&mc_eid=8b4d4fbfa2
- *Theory of Change (TOC): NGO Free Press Unlimited:* https://www.freepressunlimited.org/en/who-we-are
- *TOC: Dutch MoFA*: https://www.government.nl/binaries/government/documenten/policy-notes/2019/11/28/policy-framework-strengthening-civil-society/Annex+5+%28Engels%29+-+Strengthening+Civil+Society+-+Theory+of+Change.pdf
- *TOC: Unicef webinar*: https://www.betterevaluation.org/resources/overview/UNICEF_Webinar_ToC
- *TOC: UNFPA example:* https://www.unfpa.org/sites/default/files/admin-resource/UNFPA_strategic_plan_2018-2021._Annex_2_-_Theory_of_change_-_FINAL_-_24Jul17.pdf
- WWF. http://awsassets.panda.org/downloads/Policy_and_Advocacy_Toolkit_300617.pdf
- UNICEF (pgs 40, 42 and 44): http://awsassets.panda.org/downloads/Policy_and_Advocacy_Toolkit_300617.pdf

## ሞጁል ሶስት

- ALNAP. (2005). *Protection - An ALNAP Guide for Humanitarian Agencies.* https://www.alnap.org/help-library/protection-an-alnap-guide-for-humanitarian-agencies
- ODI/HPG. (2021). *Collaborative Advocacy Between Humanitarian and Human Rights Actors.* https://cdn.odi.org/media/documents/Advocacy_IP_Collaborative_advocacy_web.pdf
- ODI/HPG. (2022). *Influencing States' Policy and Practice on the Protection of Civilians.* https://cdn.odi.org/media/documents/Influencing_states_policy.pdf
- Oxfam. *A Rights in Crisis Guide to Influencing.* https://www.oxfam.org/en/research/rights-crisis-guide-influencing
- Oxfam. (2020). *Influencing for Impact Guide.* https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/handle/10546/621048/gd-influencing-for-impact-guide-150920-en.pdf?sequence=1

## ሞጁል አራት

- ALNAP. (2014). *The Value Iceberg: Weighing the Benefits of Advocacy and Campaigning.* https://www.alnap.org/help-library/the-value-iceberg-weighing-the-benefits-of-advocacy-and-campaigning
- Center for Civilians in Conflict (CIVIC). (2022). *Protecting Together: Preventing, Mitigating, and Addressing Civilian Harm. Advocacy Guide.* https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
- Center for Evaluation Innovation. (2019). *When the Best Offense is a Good Defense: Understanding and Measuring Advocacy on the Defense.* https://www.evaluationinnovation.org/wp-content/uploads/2019/06/DEF_ADV_PAGES_LO.pdf
- CIVICUS. *Monitoring & Evaluation Toolkit.* https://www.civicus.org/monitoring-toolkits/

- INTRAC. *Advocacy: A Toolkit for Small NGOs*. https://www.intrac.org/wpcms/wp-content/uploads/2022/06/BA-Advocacy-Toolkit.pdf
- Oxfam. (2020). *Influencing for Impact Guide*. https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/handle/10546/621048/gd-influencing-for-impact-guide-150920-en.pdf?sequence=1
- Oxfam. *MEL of Influencing Toolkit*. https://melofinfluencing.org/

## ሞጁል አምስት

- *CARE Emergency Toolkit* https://www.careemergencytoolkit.org/
- Center for Civilians in Conflict (CIVIC). *Protecting Together: Preventing, Mitigating, and Addressing Civilian Harm. Advocacy Guide (Section 5: Risk Management)*. https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
- COSO. *Enterprise Risk Management: Understanding and communicating risk appetite*. https://www.coso.org/Shared%20Documents/ERM-Understanding-and-Communicating-Risk-Appetite.pdf
- EISF. (2017). *Security Risk Management: A basic guide for smaller NGOs*. https://gisf.ngo/resource/security-risk-management-a-basic-guide-for-smaller-ngos/
- EISF. (2020). *Security to go: a risk management toolkit for humanitarian aid agencies*. https://gisf.ngo/resource/security-to-go/
- Humanitarian Policy Group (HPG). (2011). *Risk in humanitarian action: towards a common approach?* https://cdn.odi.org/media/documents/6764.pdf
- InterAction/Humanitarian Outcomes. (2016). *NGOs and Risk: How international humanitarian actors manage uncertainty*. https://www.interaction.org/wp-content/uploads/2019/02/ngos_and_risk_-_february_2016.pdf
- InterAction/Humanitarian Outcomes. (2019). *NGOs & Risk:* Managing uncertainty in local-international partnerships. https://www.interaction.org/wp-content/uploads/2019/03/Risk-Global-Study.pdf
- ODI. (2019). *Risk-informed development: from crisis to resilience*. https://odi.org/en/publications/risk-informed-development-from-crisis-to-resilience/
- Oxfam. *Safe Programming:* https://www.oxfamwash.org/en/communities/safe-programming

# የተጠናቀሩ
# የሁነት ጥናቶች

## የሁነቶች ጥናት አንድ

# በሰሜን-ምዕራብ ሶሪያ የሚገኙ የሴት መምህራንን መብት ማጠናከር

*ይህ የሁነቶች ጥናት የተዘጋጀው በ ሁራስ ኔትወርክ (Huras Network) እና ኒር (NEAR) ነው።*

**የተመረጡ ጠቅለል ብለው የተገኙ ግንዛቤዎች**

➢ በሰሜን ምዕራብ ሶሪያ የሚገኙ የሴት መምህራን ቡድን ክፍያ ያለው የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብትን የሚጠይቅ እጅግ አስደናቂ የሆነ የሙግት ተነሳሽነት መርተዋል። ሴት መምህራን አጠቃላይ ካለው የሰው ሀይልን 60% ይወክላሉ። ለዓመታት እናቶች/ሴት መምህራን እና ጨቅላ ሕፃናት ከወሊድ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ሥራ በመመለሳቸው ከፍተኛ የሆነ የጥበቃ ስጋት አጋጥሟቸዋል።

➢ የጋራ የሙግት ተነሳሽነት ተጎጂዎችን ያማከለ እና ከውሳኔ ሰጭዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖራቸው በሚያበረታታ አካሄዶች የተደራጀ ነው። እንዲሁም በአገር ውስጥ አካላት የአደጋ ግምገማ፣ የባለድርሻ አካላት ትንተና፣ ትስስር እና የአቅም ግንባታ ተሳታፊ ለሆኑ አስር ሴት መምህራን ቡድን ድጋፍ አድርጓል።

➢ ከአካባቢው ባለስልጣናት እና ከለጋሾች ጋር ለወራት በተደረገ ድርድር እና በሰብአዊ ድጋፍ መሪዎች ላይ ያተኮሩ ጥረቶች ላይ ተጽእኖ ካሳደረ በኋላ የሙግት ጥረቱ አላማውን በማስፈጸም ስኬታማ ነበር። እንዲሁም የተጎዱ ሰዎችን የማስተባበር ስልቶች ውስጥ ትርጉም ያለው፣ ስርዓት-አቀፍ ተሳትፎን እንዲሁም በሰሜን-ምእራብ ሶሪያ ያለውን የሰብአዊ እርዳታ ምላሽ የህይወት ተሞክሮ እና የሙብት ባለቤቶችን በማካተት አዳዲስ አወቃቀሮችን ለመፍጠር አስተዋፅኦ አድርጓል።

## የጥበቃ ሙግት ተግዳሮት እና የተሳታፊ አካላት አቀራረብ/ስትራቴጂ ዝርዝር

በሰሜን ምዕራብ ሶሪያ በሚገኙት 1,070 ትምህርት ቤቶች ውስጥ አብዛኛው መምህራን ሴቶች ሲሆኑ 60 በመቶውን የትምህርት ዘርፍ የሰው ሃይል የሚወክሉ ናቸው። ይህ ክልል ከ2011 ጀምሮ በግጭት የተጎዳ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከአራት ሚሊዮን በላይ ተፈናቃዮችን ያስተናግዳል። ሴት መምህራንም እናቶች እንደመሆናቸው በአብዛኛው የቤተሰቦቻቸው ዋና ተንከባካቢዎች ናቸው።

ከቅርብ አመታት ወዲህ አካባቢው በሶሪያ መንግስት ቁጥጥር ስር ባልሆነበት ጊዜ ነፍሰጡር የሆኑ መምህራን ከወለዱ በኋላ ለአንድ ቀን እንኳን የወሊድ ፈቃድ አልተሰጣቸውም። ይህ ማለት በአግባቡ ለማገገም ወይም አዲስ ለተወለዱ ሕፃናት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ወይም የልጅ እንክብካቤ ድጋፍ ለማዘጋጀት ጊዜ የላቸውም ማለት ነው። እነዚህ እናቶች ልጆቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው ለአካል ጉዳት፣ ለስሜታዊ ጭንቀት፣ ለአእምሮ ጤና እና ለሥነ ልቦና ጭንቀት እንዲሁም የሕፃናት ተጋላጭነት አደጋዎችን ጨምሮ ለተለያዩ የተጋላጭነት አደጋዎች ተጋልጠዋል። ብዙ ጊዜ በድንኳን ውስጥ እየኖሩ እና እያስተማሩ፣ በየክረምቱ ከባድ ዝናብ እና የበረዶ አውሎ ነፋሶች እየተባባሱ የሚሄዱ ችግሮች እና አስጨናቂ ሁኔታዎች ያጋጥሟቸዋል። በጥር 2021 በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ወደ 120 የሚጠጉ ትምህርት ቤቶች ተጎድተዋል[51]። ይህንን ሁኔታ ለመቅረፍ በነሀሴ 2021 በሴት መምህራን እና በትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን የሚመራ ከህፃናት ጥበቃ ድርጅት ድጋፍ ጋር የHurras ኔትወርክ የሶሪያ ዘመቻ እና የሶሪያ የሴቶች አማካሪ ቦርድ, የተባበሩት መንግስታት የአመራር መዋቅር በሰሜን-ምዕራብ የሶሪያ ምላሽ የጋራ ህዝባዊ ሙግት ተነሳሽነት ተጀመረ[52]። በኋላ በ2022 የAAP ግብረ ሃይል በችግሩ ውስጥ ቁልፍ ባለድርሻ ሆኖ ተሳተፈ። ሶስት ዋና ዘዴዎች መጀመሪያ ላይ የተተገበሩ ሲሆን-የመምህራን ታሪኮች መመዝገብ እና ማቅረብ፣ የመምህራንን የሙግት ችሎታ ለማሳደግ ስልጠናዎችን ማካሄድ እና ተፅእኖ ፈጣሪዎችን መለየት በአገር ውስጥ እና በአለም አቀፍ ደረጃ (ለምሳሌ የሲቪል ትምህርት ኮሚቴ ግብረ ሃይል፣ በክልሉ የትምህርት ዳይሬክቶሬቶች እና ለትምህርት ዘርፍ የገንዘብ ድጋፍ ሰጪዎች) ላይ ተጽእኖ ማድረግ ተካቶበታል።

## በተለያዩ አካላት የተወሰዱ ልዩ የሙግት ድርሻዎች፣ ድርጊቶች እና ስልቶች

ታሪካቸው በፅሁፍ ተመዝግቦ አስደናቂና ለእይታ ሳቢ በሆነ መልኩ ታጀቦ እና የሙግት መልእክቶቻቸው ተገልፀው የመምህራን ቡድኑ ውሳኔ ሰጪዎችን እና ለጋሾችን አግኝተው በሰሜን ላሉ ሴት መምህራን በሙሉ ለሶስት ወራት ክፍያ ያለው የወሊድ ፈቃድ መብት እንዲሆን ጥሪያቸውን አቅርበዋል። በሀገር ውስጥ ያሉ ተሳታፊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ስብሰባዎችን ሲያስተባብሩ እና የቋንቋ ትርጉም ሲያስፈልግ በመተርጎም አግዘዋል።

ከዚህም በመቀጠል ሌሎች ተከታታይ ቁልፍ ግኝቶች ተከትለዋል። በአንድ ወቅት መምህራኑ የHLG ወርሃዊ ስብሰባ ላይ ተገኝተው ከተጋላጮች ጥበቃ እና የትምህርት ክላስተር አስተባባሪዎች ጋር ነፍሰ ጡር ሴት መምህራን እያጋጠሟቸው ስላለው ተግዳሮቶች እና ሌላው ከHC እና OCHA አመራር ጋር በቀጥታ የተነጋገሩበት ወቅት ነው። የሰሜን ምዕራብ ሶሪያ የAAP አማካሪዎች ቡድን ከ humanitarian Syria fund  እና ከ HC የክልል ምክትል ተወካዮች ጋር ስብሰባዎችን አስተባብሯል። በተጨማሪም በኬሞኒክ የግል ዓለም አቀፍ ልማት ድርጅት በሚመራው የማናሄል ፕሮጀክት ስር 470 ትምህርት ቤቶችን የሚደግፍ የአገር ውስጥ ተነሳሽነት - ቡድኑ የስትራቴጂክ እቅዱን ለማዘጋጀት የሚሆን ድጋፍ እና ቦታ አግኝቷል።

የሙግት ተነሳሽነት ከቃላት በላይ መሬት ላይ ወርዶ በመስራት አመርቂ ወጤት አምጥቷል። ለመምህራን መብት ለመሟገት እና ከአካባቢው ውሳኔ ሰጪዎች ጋር ለመሳተፍ የሴት መምህራን ሰራተኞች ማህበር ተመስርቷል። አዲስ የተቋቋመው ማኅበር ተወካይ በየዓመቱ ሁለት ጊዜ ከሚደረጉ የትምህርት ዳይሬክቶሬት[53] የሲቪክ ማህበራት፣ መምህራን እና የአካል ጉዳተኛ ህጻናት ወላጆች ማኅበር  መደበኛ ስብሰባዎች መካከል መገኘት ችሏል። እነዚህ የአካባቢ ደረጃ ስብሰባዎች በገጠር አሌፖ እና ኢድሊብ ክልሎች የትምህርት ፖሊሲ ስትራቴጂዎችን ለመንደፍ የታሰቡ ናቸው። የቡድኑ ተወካይ በታህሳስ 2021 ከአካባቢው የሲቪል ማህበራት ጋር በጋራ መድረኩን በመውሰድ ከትምህርት ዳይሬክቶሬቱ ጋር ለሴት መምህራን የወሊድ ፈቃድ ያለመታከት ተወያይቷል።

እነዚህ ጥረቶች መምህራን ታሪካቸውን ሲያቀርቡ ጀምሮ እስከ ድርድር እና የንግግር ችሎታን ማዳበር ስልጠና እና ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር ስብሰባ እስከማድረግ ድረስ ሙሉ አንድ አመት ፈጅቷል። የዝግጅት ጊዜ፣ ዋና ዋና መልእክቶችን ማሰናዳት፣ ስልጠናዎች እና ታሪኮችን ለማዘጋጀት ሁለት ወራት አካባቢ ፈጅቷል። የሙግት ተነሳሽነት ግብ በጥር 2022 እስኪሳካ ድረስ የሀገር አቀፍ እና አለም አቀፍ የፕሬስ ቃለመጠይቆችን ጨምሮ የተለያዩ ስልቶች፣ ለጋሽ እና ውሳኔ ሰጪዎች ማግባባት እና ከዋና ዋና ባለድርሻ አካላት ጋር በመገናኘት የጋራ የሙግት ግቦችን ለማስቀጠል እና እርምጃዎችን ለማስተባበር ጥቅም ላይ ውለዋል።

በመጨረሻ ለጋሾች እና የትምህርት ዳይሬክቶሬቶች ለመምህራን የሶስት ወር የወሊድ እረፍት ነገር ግን የአንድ ወር ክፍያ ብቻ ለመስጠት ወስነዋል። የአካባቢው የትምህርት ፕሮጀክት ፖሊሲዎች ለአንድ ወር የሚቆይ የእረፍት ጊዜን ለመሸፈን የተተኪ መምህራንን ደመወዝ ለመክፈል ተስማምተዋል። ምንም እንኳን የሙግት ጥያቄዎቹ ለሦስት ወራት የሚቆይ ፈቃድን ቢጠይቁም, ሙሉውን ጊዜ በገንዘብ እንዲሸፈን አበክረው አላሳሰቡም። ምንም እንኳን የመምህራን ታሪኮች ተፅዕኖ ለመፍጠር ጥቅም ላይ የዋሉ ቢሆንም፣ መምህራን/እናቶች እና ልጆቻቸው ያጋጠሟቸውን የተጋላጭነት ስጋቶች ለውሳኔ ሰጪዎች ለማሳወቅ እንደ መደበኛ ዘገባዎች ያሉ ጠንካራ ማስረጃዎች እጥረት ነበር።

## የአደጋ ስጋት ታሳቢዎች እና አስተዳደር

በሁራስ  ኔትዎርክ[54] እና በሶሪያ ዘመቻ የተደረገው የአደጋ ትንተና ሴት መምህራን በራሳቸው ስም ተነሳሽነትን ከጀመሩ ለትንኮሳ ሊጋለጡ የሚችሉበት እድል ከፍተኛ ነው ሲል ደምድሟል።

የአካባቢው ባለስልጣናት መምህራኑን ከስራቸው በማባረር እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዳይሰሩ በመከልከል አፀፋውን ሊመልሱ ይችላሉ። ስለዚህ የሙግት ተነሳሽነቱ ሲጀመር በመጀመሪያ የወሊድ ፈቃድ ጉዳይን ሳያካትት በሴቶች መምህራን ላይ ያተኮረ የስኬት ታሪክ ለማስተላለፍ ተዘጋጅቷል። ሴት መምህራን ከወሊድ ፈቃድ መብት ጋር በተያያዘ ጥሪያቸውን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባደረጉት ውይይት ለማቅረብ ችለዋል። እነዚህ ዝግ ስብሰባዎች አልተመዘገቡም የሚስጢራዊነት ደንቦችም ተፈጻሚ ሆነዋል (ማለትም በመገናኛ ብዙኃን ወይም በማህበራዊ አውታረ መረቦች ላይ ምንም ዓይነት ዘገባ የለም)።

በተነሳሽነቱ የተሳተፉት ሁሉም ሴት መምህራን በስጋት ምዘና ልምምዱ ላይ በመሳተፍ የተሻሉ የአደጋ መከላከያ ስልቶችን በመወሰን ረድተዋል። ሁሉም መምህራን ሊከተሏቸው የሚችሉት አደጋዎች ከተነገራቸው በኋላ እንዴት ራሳቸውን መከላከል እንደሚችሉ ትምህርት ወስደዋል።

## የጋራ ውጤቶችን በትብብር እና በትኩረት ወደ ትግበራ የማስገባት ሂደት

የሀገር ውስጥ ድርጅቶች መምህራኑ እንዲለዩ እና ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር እንዲገናኙ እድል በመፍጠር ቁልፍ ሚና የተጫወቱ ሲሆን ሴቶችን በማሰልጠን እና በማብቃት ልዩ ድጋፍ አድርገዋል። በዩናይትድ ኪንግደም መቀመጫውን ያደረገው በሶሪያ ጦርነት ለተጎዱት ድጋፍ የሚሰጠው ዘ ሲሪያ ካምፔን (The Syria Campaign) በተለይም የባለድርሻ አካላትን ትንተና በማካሄድ እና የተጋላጮች ጥበቃ የሙግት መልእክቶችን በማዘጋጀት እና ምክረ ሃሳቦች በማቅረብ አስተዋፅኦ አድርጓል።

የሀገር ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበራት የሙግት ተነሳሽነት ንድፍ በማዘጋጀት ድጋፍ ያደረጉ ሲሆን ይህም መምህራኑን የሙግት ማዕከል እና ወሳኝ አጋር አርጓቸዋል። ሁሉም ስልቶች የተስተካከሉ ሲሆን የጋራ የሙግት መልእክቶችን ከማርቀቅ ጀምሮ መምህራን እየተጋበዙ እና በስብሰባ ላይ ግንባር ቀደም ሆነው ሲገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና አስተባባሪ አካላት እንደ አስተናጋጅ እና አስተባባሪነት በሁለተኛነት ደረጃ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል።

የመብት ባለቤቶች እንደ የለውጥ ወኪሎች በዚህ የሙግት ተነሳሽነት በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ ዘልቀው በመግባታቸው እና አንዳንድ ቁልፍ እርምጃዎች ሊከናወኑ የቻሉት ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር እና ለተጎዱ ሰዎች ቁልፍ በሆኑ የሰብአዊ መድረኮች ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎን በሚደግፉ የፈጠራ ዘዴዎች ብቻ ነው። ይህ ተነሳሽነት አዳዲስ አወቃቀሮችን ለመመስረት፣ እነዚህን ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ለማስፋፋት እና ለማጠናከር አስተዋፅኦ አበርክቷል።

በተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች የሚመሩ **የAAP** ቻናሎች ተጎጂዎች በሰብአዊ ማስተባበሪያ መድረኮች ላይ እንዲካተቱ እና እንዲሳተፉ እገዛ አደርጓል። ይህም በመምህራን ቡድን እና በሚመለከታቸው ውሳኔ ሰጪዎች መካከል በሚደረጉ ስብሰባዎች ቅንጅት እንዲፈጠር ትልቅ ሚና ተጫውቷል። በተናጥል፣ ሌሎች **የAAP** ቻናሎች በሰሜን ምዕራብ ሶሪያ ውስጥ ተፈናቃዮችን ከካምፕ ማስወጣትን ለመቅረፍ መንግሥታዊ ካልሆኑ ታጣቂ ቡድኖች (NSAGs) እና ከባለሥልጣናት ጋር በሙግት ለመሳተፍ ፈቃዳቸውን አሳይተዋል። እነዚህን ስልቶችን ለማስፋፋት እና የጋራ **የAAP** መዋቅር ለመፍጠር በማለም በ2021 መገባደጃ ላይ በክልሉ ያለው **የAAP** የስራ ቡድን ከሲቪል ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ እና የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች ጋር ሰፊ የምክክር መድረክ መርቷል ይህም ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች ያሉት: የአንድ አመት የድርጊት መርሃ ግብር አዘጋጅቷል፣ እነዚህ አላማዎች የተጎዱ ሰዎችን በጥሞና ማዳመጥ; ውጤታማ ምላሽ መስጠት; እና ትኩረት በተሞላበት መንገድ መነጋገር ናቸው። በነዚህ አላማዎች መሰረት 10 ቁልፍ ተግባራትን የሚሰሩ 10 የተለያዩ የስራ ቡድኖች ፣55 ከሌሎቹ 10 የስራ ቡድኖች ጋር የተጣመሩ እያንዳንዱን ተግባር የሚቆጣጠሩ እና የሚገመግሙ ናቸው። የስራ ቡድኑ አባላት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኤጀንሲዎች፣ የሀገር ውስጥ እና አለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ Humanity & Inclusion (HI)፣ Reach፣ NORCAP's GenCap ፕሮጀክት፣ የስዊስ የልማትና ትብብር ኤጀንሲ (SDC) እና የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ፣ የኮመንዌልዝ እና ልማት ቢሮ (FCDO) ናቸው።

የ OCHA የሰብአዊ እርዳታ ማስተባበሪያ ስልቶች አካል የሆነው የሶሪያ ሴቶች አማካሪ ቦርድ HC የአካባቢ ሻምፒዮን ያደረጋቸው ሲሆን የሴት መምህራን ሰራተኞችን ጥበቃን ጨምሮ በተለያዩ የሙግት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሳትፈዋል። ቡድኑ በሶሪያ ውስጥ ከተለያዩ ሴክተሮች እና ከተለያዩ የሶሪያ የሲቪል ማህበራት የተውጣጡ ሴቶችን ያጠቃልላል። ለተጋላጭ ሴቶች እና ህጻናት በሚደረጉ የጥበቃ ጉዳዮች ላይ የሙግት ጥረቶችን የአካባቢ ሻምፒዮን እንዲሆኑ እና በይፋ እንዲመሰርቱ ድጋፍ አድርጓል። በመሬት ላይ ያሉ ባለድርሻ አካላትም የ WAB አባላት በስብሰባዎች ላይ ስለተሳተፉ፣ ውይይቶችን እና በ HLG 'ቋንቋ' ከተጎዱ ሰዎች ጥቅሶችን እና የተነሱ ጉዳዮችን ማካተት መጀመራቸውን ጠቁመዋል። ይህ የቡድኑን ተፅእኖ የሚያንፀባርቅ እና በስብሰባዎች ላይ ከቴክኒካል አቀራረብ ይልቅ ወደ የተጎዱትን ሰዎች ድምጽ ወደማዳመጥ ላይ ያተኩራል።



የ47 አመቱ ፋራጅ በአንድ ወቅት አረንጓዴ በነበረው መሬቱ ላይ ተቀምጦ *ምስል: ኢስላም ማርዲኒ*

## የሁነት ጥናት ሁለት

# በደቡብ ሱዳን ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች መፍትሄ ማስቀመጥ

*ይህ የሁነት ጥናት ከ ዳቪስ, ጀ. እና ስፔንሰር, ኤ. (2022) 'በአለምአቀፍ እና በአካባቢ የተጋላጮች ጥበቃ መካከል የተመጋጋቢነት ማሟያ: "ለእኔ ለትናገሩልኝ, እኔ ለራሴ እናገራለሁ"* ፣ *የ HPG አጭር ማስታወሻ ለንደን፡ ODI የተወሰደ*

**የተመረጡ ጠቅለል ብለው የተገኙ ግንዛቤዎች**

➤ በደቡብ ሱዳን ጾታዊ ጥቃት ላይ የሚደረጉ የሙግት ጥረቶች የተጋላጮች ጥበቃ ጉዳዮች ዓለም አቀፋዊ ትኩረትን እንዲያገኙና የሀገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት እና ተጎጂዎች በሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ ለመነጋገር እንዴት መድረኮችን መፍጠር እንደሚቻል አጉልቶ አሳይቷል።.

➤ እ.ኤ.አ. በህዳር 2018 ድንበር የለሽ ሐኪሞች (Médecins Sans Frontières (MSF)) በቤንቲዩ በሚገኘው ክሊኒካቸው ውስጥ እያከሙ ስለነበረው የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች መጨመር ሪፖርት አውጥቷል (MSF, 2018)። ይህ ከMSF ሰራተኞች መካከል የአንዱን ሰራተኛ መባረር ያስከተለ ሲሆን የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች ከአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር በመተባበር በደቡብ ሱዳን ስላለው ወሲባዊ እና ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶች (SGBV) ግንዛቤ ለማሳደግ ተንቀሳቅሰዋል። ይህ የሲቪል ማህበረሰቦችና እና ከGBV የተረፉ ሴቶች እነዚህን ጉዳዮች በማንሳት እና ለውጥን በማምጣት ላይ ያላቸው እምነት እያደገ እንዲሄድ አድርጓል።

➤ ከጥቃት የተረፉ ሰዎችን - የጤና፣ የስነ-ልቦና ወይም የህግ አገልግሎት ድጋፍ GBVን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ዘላቂ ተሳትፎ እና የገንዘብ ድጋፍ በሰዎች ህይወት ላይ ተጨባጭ ለውጦች እንዲፈጠሩ አድርጓል። ከጥቃቱ የተረፉ ሰዎች ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት እንደ ፍትህ ሚኒስቴር ካሉ ጋር ቀጥተኛ ባለደርሻዎች ጋር ውይይት አድርገዋል። በተጨማሪም ይህ ቀጣይነት ያለው የትብብር ድጋፍ በ2020 በጁባ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ፆታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን የሚፈጽሙ ወንጀለኞች እና ወጣት አጥፊዎች የሚቀጡበት ፍርድ ቤት በተሳካ ሁኔታ እንዲቋቋም አድርጓል።

## የሙግት ተግዳሮቶች እና የባለድርሻ አካላት አካሄድ/ ስትራቴጂ ዝርዝር

ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት መጠን መጨመር፣ እና የአስገድዶ መድፈር እንደ የጦር መሳሪያ ጥቅም ላይ የመዋሉ ከፍተኛ ስጋት በመፍጠሩ ለጾታዊ ጥቃቶች መከላከል እና ምላሽ ለመስጠት፣ የተጠያቂነት ዘዴዎችን ማጠናከርን ጨምሮ ህዝባዊ ጥሪዎች እንዲጨምሩ አድርጓል። በደቡብ ሱዳን የSGBV ጉዳይን ግንባር ቀደም ለማድረግ አለም አቀፍ እና አገራዊ ትኩረትን መሳብ አንዱ ቁልፍ እርምጃ ነበር። በ SGBV ጉዳዮች የህዝብ ታይታነት መኖሩ በደቡብ ሱዳን ውስጥ ላለው SGBV ደረጃ ትኩረትና ድጋፍ ለመስጠት ወሳኝ በመሆኑ በደቡብ ሱዳን መንግስት፣ በዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ፣ በተመድ የጸጥታዉ ም/ቤት እና የአፍሪካ ህብረት ጨምሮ የተለያዩ የሙግት ዘመቻዎች ተካሂደዋል። (ከዚህ በታች ይመልከቱ)

የተጋላጮች ጥበቃ ባለድርሻ አካላት ብሄራዊ እና አለም አቀፋዊ ድርጅቶች የሚወከሉበት ፆታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት (GBV) ንዑስ ክላስተር አባላትን እና የሴቶች መብት ተሟጋች አካላትን ያካትታል። የነዚህ አካላት ትብብር እና ወዳጅነት ጾታን መሰረት ላደረጉ ጥቃቶች ተጠያቂነት እንዲኖር መድረኮችን ለማዘጋጀት ቁልፍ እርምጃዎች ነበሩ።

በአለም አቀፍ እና በደቡብ ሱዳን  በግጭት ውስጥ ያለውን ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት እይታ እና መነቃቃትን በመጠቀም፤ 'ተጠያቂነት' የGBV ንኡስ ክላስተር የሙግት ጭብጥ ሆኖ ነበር። ተጠያቂነትን ወደፊት ለማስቀጠል ጠንካራ የመንግስት አጋሮች ድጋፍ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ከነዚህም ጠንካራ አጋሮች መካከል ይህ ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃትን ችግር ለመፍታት የሚደረገውን ጥረት የሚደግፈው የሥርዓተ-ፆታ፣ የሕፃናት እና ማህበራዊ ጥበቃ ሚኒስትርን እና የመከላከያ ሃይል ከፍተኛ ባለስልጣናትን ያጠቃልላል። ይሁን እንጂ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችሉ ወንድ ሻምፒዮኖች አለመኖራቸው ይህ አጀንዳ የበለጠ ወደፊት እንዳይራመድ እንቅፋት ሆነው ነበር።

በደቡብ ሱዳን የሚገኙ ሌሎች አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ትስስሮች ከጾታዊ ጥቃት ለተረፉ ድጋፍ ሰጪ ቡድኖችን በማቋቋም ከመንግስት  ውሳኔ ሰጪዎች ጋር ቀጥተኛ ውይይት ያስጀመሩ ሲሆን የአለም አቀፍ አጋሮች ደግሞ መንግስት እርምጃ እንዲወስድ ተጨማሪ ጫናዎችን ፈጥረዋል።
የዚህ ጅምር አካል በመስከረም 2021 በጁባ ውስጥ በአለም አቀፍ ደረጃ የተደገፈ የ'Survivors Speak' ኮንፈረንስ ላይ ከጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት የተረፉ ተጎጂዎች ባለስልጣናት እና የመንግስት ፖሊሲ አውጪዎችን ጨምሮ በጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት ተጽእኖ ላይ (ሙብቶች ለሰላም 2021) ተሳትፈዋል።

የሲቪል ማህበራትና እና የተጎጂ ቡድኖች በደቡብ ሱዳን ያለውን ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት ለቀጠናው እና አለምአቀፍ ባለድርሻ አካላት፤ የተባበሩት መንግስታት የፀጥታው ምክር ቤት እና ለአፍሪካ ህብረት ለማሳሰብ  ከአለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር መስራታቸውን ቀጥለዋል። እኚህ ባለድርሻ አካላት በቀጥታ ከተጎጂ ሰዎች መስማታቸው በጣም አስፈላጊ ነው።

## በተለያዩ አካላት የተወሰዱ ልዩ የሙግት ድርሻዎች፣ ድርጊቶች እና ስልቶች

በደቡብ ሱዳን   ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት የደረሰበትን የተለያዩ ደረጃዎች ለመፍታት የጋራ ዓላማ ባላቸው አካላት መካከል ድርሻዎቻቸው ተለይተው ተዘጋጅተዋል። ከአስተማማኝ አጋራት መካከል አንዱ የሆነው MSF የጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት ከፍተኛ ደረጃዎች በይፋ መናገር ለጉዳዩ ታይታነት መጨመር እንደ አስፈላጊ መሳሪያ ተደርጐ ይወሰዷል።

ደቡብ ሱዳን ጠንካራ የሲቪል ማህበራት፣ የሴቶች መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና የሴቶች ሲቪል ማህበራት ጥምረት አላት። አለም አቀፍ ድርጅቶች ብሄራዊ አካላት ብሄራዊ፣ ቀጠናዊ እና አለም አቀፋዊ መድረኮችን እና ውሳኔ ሰጪዎችን እንዲያገኙ ድጋፍ አድርገዋል። ለምሳሌ መደበኛ ያልሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቡድን ጨምሮ ፣ ክራይስስ አክሽን (Crisis Action)፣ ጀስቲስ አፍሪካ (Justice Africa)፣ ኦክስፋም (Oxfam) እና ኖርዌጂያን ፒፐልስ ኤይድ (Norwegian People's Aid (NPA))ን የሲቪል ማህበራት በሰላም ሂደቱ ውስጥ በቀጥታ እንዲሳተፉ ለመደገፍ በትብብር ሰርተዋል።

አለም አቀፍ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የደቡብ ሱዳን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶችን በጋራ እንዲሰሩ እና ተፅዕኖ በሚፈጥሩ አቀራረቦች ላይ ስትራቴጂ እንዲነድፉ፣ ለሙግት የሚሆን የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ እና ከሀገራዊ፣ ቀጠናዊ እና አለም አቀፋዊ ስልቶች ጋር እንዲሰሩ ድጋፍ አድርገዋል።

የሴቶች መብት ተሟጋቾች ጥምረት በሰላም ሂደት ዙሪያ ያለውን ተነሳሽነት በመጠቀም የሴቶችን መብት የማስከበር ትኩረት ለመሳብ ከOxfam፣ Crisis Action እና NPA ድጋፍ ጠይቋል (Oxfam፣ 2020)።

ክራይስስ አክሽን (Crisis Action)፣ የሴቶች ጥምረት ለመጀመሪያ ጊዜ በሴቶች፣ ሰላም እና ፀጥታ ጉዳዮች ላይ የኦንላይን ጉባኤ በደቡብ ሱዳን ውስጥ እንዲካሄድ ድጋፍ አድርጓል። (ሳዋ ደቡብ ሱዳን, 2018) እነዚህ እና ተዛማጅ ዘመቻዎች በሴቶች እና ልጃገረዶች ድርሻ እና መብት ላይ ያሉ አመለካከቶች እንዲቀየሩ እና በደቡብ ሱዳን ማህበረሰብ ውስጥ የአባታዊ (patriarchal) ስርአቱን ለመገዳደር አስተዋፅዖ አበርክተዋል።

ከተገኙ ስኬቶች መካከል በደቡብ ሱዳን ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት ጋር ተያይዞ የጤና፣ የስነ-ልቦና ማህበራዊ፣ የኑሮ ሁኔታ እና የህግ ድጋፍ እርዳታን ይጨምራል። ከተገኙት ስኬቶች  ዋነኛው በጁባ በ 2020 ጾታን መሰረት ያደረግ ጥቃት እና የወጣት አጥፊዎች ፍርድ ቤት መቋቋም ነበር። እንዲሁም ከላይ እንደተገለፀው ከፆታዊ ጥቃት በተረፉት እና የመንግስት  ውሳኔ ሰጪዎች መካከል ቀጥተኛ ውይይትን ማካሄድ። አንዳንድ ታላላቅ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ስኬቶች የተገኙት ከፕሮግራም ጋር የተያያዙ ገንዘቦችን ባልተቀበሉ እና መደበኛ ባልሆኑ ቡድኖች ነው።

እንደ ውድቀት ከሚቆጠረው የሚጠበቁትን ማስተዳደር እና ምላሽ ሰጪ እንቅስቃሴን መዳከምን ያካትታሉ በተለይም ከዚህ ቀደም አጋርነት በተገነባበት እና የመተማመን ደረጃ ላይ ተመስርቶ የነበረዉን። ለምሳሌ ከተከታታይ ከባድ የአስገድዶ መድፈር ጥቃቶች በኋላ የሴቶች ቡድን ተቃውሞ አነሳ። ከዚህ ቀደም አብረው ይሠሩበት ከነበረው ዓለም አቀፍ አጋር ጋር ቀርበው ነገር ግን በቢሮክራሲያዊ ችግሮች ምክንያት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ አልቻለም። ሆኖም የዓለም አቀፍ ድርጅት ተወካዮች በተቃውሞ ሰልፉ

ላይ ተገኝተው በሰነድ ዘግበውታል እንዲሁም በኋላም ይፋ አድርገዋል። የሴቶች ቡድን አባላት ዓለም አቀፉ ድርጅት ሰልፉን በገንዘብ በመደገፍ በሴቶች መካከል መከፋፈልን አስከትሏል ብለው ያስባሉ። በውጤቱም ቡድኑ ተበታተነ። ይህ ያልተጠበቁ፣ የአለምአቀፍ ተዋናዮች ድርጊት ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን እና በተለዋዋጭ የገንዘብ ድጋፍ ዙሪያ ፈተናዎችን ያስነሳል።

## የአደጋ ስጋት እሳቤዎች እና አስተዳደር

በጥቃት ሰለባዎች ወይም ተሟጋቾች ላይ የተጣሉ የበቀል አደጋዎች ለምሳሌ አንዲት የሴቶች መብት ተሟጋች  በደቡብ ሱዳን የጸጥታ ሃይሎች ብሔራዊ ደህንነትን ጨምሮ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ደርሶባት ነበር። ዓለም አቀፍ የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች በመብት ተሟጋቾች ላይ አደጋዎች ሲከሰቱ የመብት ተሟጋቾችን ለመደገፍ ብቁ አይደሉም። ይህ ሁኔታ ሲከሰት በድርጅቱና ግለሰቡ መካከል ባለው ግኑኝነት መሰረት አክቲቪስቱ አገሩን እንዲለቅ እና ወደሚደግፈው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት እንዲተላለፍ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

የሰብአዊ እርዳታ አካላት ሃገር ውስጥ ካሉ አጋሮቻቸው ጋር በቀጥታ የሙግት ስራዎች ላይ ለመስራት በሚሰማሩበት ጊዜ በሙግት ስራ ላይ የተሰማሩ አለም አቀፍ ድርጅቶች በሃገር ውስጥ ያሉ አጋሮቻቸውን እንዴት መደገፍ እንደሚችሉና ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን እንዴት መቀነስ እንደሚችሉ እንዲሁም እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ጨምሮ  የተለያዩ ጥያቄዎችን ያስነሳል።

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ባለድረሻ አካላት ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች (HRDs) ከሚያደርጉት ድጋፍ አንጻር ሲታይ  የሰባዊ እርዳታ ባለሙያዎች እነዚህን ድጋፎች በማቀድ እና በማዘጋጀት ረገድ ደካማ ናቸው። አለምአቀፍ የሰብአዊ እርዳታ አካላት በሰብአዊ መብት አቻዎቻቸው ከተዘጋጁ አካሄዶች በመማር ለሀገር አቀፍ አጋሮች ያለባቸውን የሞራል ሃላፊነትን ግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ቢያንስ ቢያንስ ለሰብአዊ መብት ተሟጋቾች (HRDs)  ቀጥተኛ ድጋፍ ለሚሰጡ ድርጅቶች የሪፈራል ስርዓትን መዘርጋት አለባቸው።

## የጋራ ውጤቶችን በትብብር እና በትኩረት የማላመድ ሂደት

የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የሙግት ጥረቶችን ለመምራት የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው ያለው ወይስ የአካባቢያዊ የሙግት መድረኮችን ድምጽ ለማጉላት ድጋፍን የማቅረብ ሚና መጫወት ወይም ብሄራዊ አካላት የሙግት ጥረቶችን እንዲመሩ ቦታ ለመክፈት  ወደኋላ አንድ እርምጃ መራመድ እንደሚሻል መረዳት አለባቸው። ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለሙግት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የተጋላጮች ጥበቃ ጉዳዮች ወይም ከተጋላጮች በተሻለ ለውጥ ላይ ተጽዕኖ የማሳደር አቅም እንዳላቸው ማሰብ የለባቸውም። ለሁሉም የሚስማማ አካሄድ ፈጽሞ ሊኖር ሰለማይችል እንደየሁኔታው ለመስራት ቀጣይነት ያለው መስተጋብር እና የጋራ ባለቤትነት እንዲኖር የሀገር ውስጥ የጥበቃ አካላትን ከግምት ውስጥ ማስገባት  ያስፈልጋል።

**ከሪፖርቱ የተሰጡ ምክረ ሃሳቦች የሚከተሉትን ያካትታሉ:**

- ብሄራዊ አካላት በተጋላጮች ጥበቃ ስራ ላይ  በቀጥታ ከውሳኔ ሰጪዎች ጋር  እንዲሳተፉ መድረኮችን ማዘጋጀት። የብሔራዊ ባላድርሻ አካላትን  አቋም እና ቅድሚያ የሚሰጧቸውን አካሄዶች በመለየት የብሔራዊ አካላትን  ተሳትፎ ማረጋገጥ። ይህም በተጋላጮች ጥበቃ ላይ የስትራቴጂ አማካሪ ቡድኖች፣ የተጋላጮች ጥበቃ ፎረም ወይም የጋራ የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት ስትራቴጂዎች በኩል ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ የሚደረጉ ጥረቶች የማስመሰል ብቻ እንዳይሆን እና የብሄራዊ ድምጾች እንዳይገለሉ  መረጋገጥ አለባቸው።

- ብሔራዊ አካላትን በሙግት ስትራቴጂዎች እና ትንተና ዝግጅት ላይ በእኩል በማሳተፍ አጋርነትን መመስረት። ይህም የሀገር ውስጥ እና የአለምአቀፍ አካላት በሙግት ተግባራት ላይ የሚኖራቸውን ድርሻ ማካተት አለበት። አለምአቀፍ አካላት የሙግት ጥረቶችን ለመምራት የተሻሉ ሲሆኑ፣ የብሄራዊ ተሟጋቾችን ድምጽ ለማጉላት መቼ ድጋፍ እንደሚሰጡ እና መቼ ወደ ኋላ መለስ ብለው ብሔራዊ አካላት የሙግት ጥረቶችን እንዲመሩ ቦታ መልቀቅ እንደሚገባቸው መረዳትና ለማዳመጥ ዝግጁ መሆን አለባቸው።
- ከአካባቢና ከሀገር ውስጥ አካላት ጋር የጋራ የአደጋ ትንተናዎችን እና ቅነሳዎችን ማረጋገጥ። ሁሉም አጋር አካላት ሊከሰቱ ስለሚችሉ አደጋዎች በበቂ ሁኔታ ማሳወቅ እና ለእነሱ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ።
- የHRD ጉዳዮችን ወደ ጥበቃ ድርጅቶች ሪፈር በማድረግ ሂደት ላይ መሳተፍ እነዚህን ምንጮችም ለማግኘት መንገዶችን መፍጠር።
- በበርካታ አመታት አጋርነት እና በብሔራዊ የሙግት አቅም ግንባታ ላይ ኢንቨስት ማድረግ። ምላሽ ሰጪ የሙግት ድጋፍን ለማነቃቃት ቋሚ ያልሆኑ የገንዘብ ድጋፎችን ወደ ሙግት ተነሳሽነቶች ማምጣት።
- የሃገር ውስጥ ባለደርሻ አካላት በሰብአዊ እርዳታ ምላሽ ውስጥ በስትራቴጂካዊ እና የውሳኔ ሰጪነት ደረጃዎች ጨምሮ ሙሉ ለሙሉ የተዋሃዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

- የሃገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት በተጋላጮች ጥበቃ ላይ በእኩልነት እንዲሳተፉ እንቅፋቶችን ለመቅረፍ ቁርጠኛ መሆን። ይህም የኃይል ሚዛን ተለዋዋጭነትን ከሚደግፉ ስርዓቶች, ሂደቶች እና የቃላት አገባቦች ጋር እውቅና መስጠትን ያካትታል።



በትምህርት ለሕይወት-ፕሮጀክት አማካኝነት መምህራን ለተማሪዎች የስነ-ልቦና-ማህበራዊ እንክብካቤን በመስጠት የሰለጠኑ ናቸው - እና አሁን በተለይ በኮሮና ምክኒያት መዘጋት በኋላ ትምህርታቸውን የማቋረጥ አደጋ ላይ ለሆኑ ልጃገረዶች ትኩረት ይሰጣሉ ።

ፎቶ፡ ሙስጠፋ ኡስማን

## የሁነት ጥናት ሶስት

# በወረራ በተያዙ የፍልስጤም ግዛቶች የሚኖሩ ሴቶችን መብት ማስጠበቅ

***ይህ የሁነት ጥናት የተዘጋጀው በፍልስጤም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ህብረትና እና ኒር (NEAR) ነው።***

**የተመረጡ ጠቅለል ብለው የተገኙ ግንዛቤዎች**

➤ ምንም እንኳን በዌስት ባንክ እና ጋዛ ጠንካራ መሰረት ያላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (CSOs) ቢኖሩም በፍልስጤም ባለስልጣናት የሚወሰደው የፈላጭ ቆራጭነት አመለካከት እና በእስራኤል ሃይሎች እየተወሰደ ያለው እስራት እና ግፍ ተጨምሮበት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሲቪል ማህበረሰብ ተሳትፎ ገድቦታል።[57]

➤ በተወረሩ የፍልስጤም ግዛት (OPT) ውስጥ ያሉ ሲቪሎች/በጦርነት ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች ለአስርተ አመታት ተደጋጋሚ ጥቃቶች እና የመብት ጥሰቶች እና ለረጅም ጊዜ የቆየ አለመረጋጋትን አስተናግደዋል።[58] በምላሹም ቁጥራቸው በርከት ያሉ የሲቪል ማህበራት የተፈጠሩ ሲሆን እነዚህም በቡድን ተሟጋችነት ላይ ልዩ እውቀትን አከማችተዋል፣ ይህም እንደ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች እና የታጠቁ ቡድኖች ጋር ድርድርን ይጨምራል።

➤ በሃይማኖት መሪዎች የወጣው የጉዞ እገዳ የሴቶችን መብትና የመዘዋወር ነፃነት ሲገድብ የፍልስጤም ሲቪል ማህበራት በፍጥነት በመንቀሳቀስ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የሰብአዊ መብት ተሟጋች ቡድኖችን በማጣመር በሴቶች እና ወጣቶች ቡድን እየተመሩ ለወራት የዘለቀ የሙግት ጥረቶችን አድርገዋል። እገዳው በፍጥነት እንዲቀለበስ ከተደረጉት ጥረቶች መካከል በፖለቲካ ፓርቲዎች እና በመገናኛ ብዙሃን ድጋፍ የማህበራዊ ሚዲያ ትስስር እና የህዝብ ግፊትን ማሰባሰብ ይገኙበታል።

➤ የጋራ ንቅናቄ ልምድ ባላቸው ባለድርሻ አካላት በአከባቢ ደረጃ የተደረገው የጋራ ቅስቀሳ ለመጀመርያ ጊዜ ከሀይማኖት አባቶች ጋር ውይይት እንዲደረግ እና በመጨረሻም እንዲሻሻል እና የጉዞ እገዳው እንዲነሳ አስችሏል።

## የሙግት ተግዳሮቶች እና የባለርሻ አካላት አካሄድ/ስትራቴጂ ዝርዝር

እ.ኤ.አ. በ2021 መጀመሪያ ላይ በጋዛ ከፍተኛው እስላማዊ ፍርድ ቤት የከፍተኛው የሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክር ቤት የወጣው ሰርኩላር የሴቶችን የመንቀሳቀስ መብታቸውን በእጅጉ የሚገድብ የጉዞ እገዳን ጥሏል።

በፍርድ ውሳኔ ላይ በተቀመጠው ድንጋጌ መሰረት፣ ያላገቡ የፍልስጤም ሴቶች 'ከወንድ ዘመዶቻቸው' (ማለትም አባት፣ ልጅ ወይም ሌላ ወንድ ዘመድ) ፈቃድ ሳያገኙ እንዲጓዙ አይፈቀድላቸውም ነበር። ሌላው ድንጋጌ ደግሞ የተፋቱ ጥንዶችን በሚመለከት ልጆቻቸው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንዲጓዙ የመፍቀድ የአባት ስልጣን ብቻ እንደሆነ ይደነግጋል።

በተሰጠው ውሳኔ ላይ የፍልስጤም የሲቪል ማህበራት አፋጣኝ ምላሽ የሠጡ ሲሆን እነዚህ ሁለቱም አንቀጾች እና ሌሎች ሶስት አንቀጾች በመብት ተሟጋቾች የ2003 የፍልስጤም መሰረታዊ ህግ እና የ OPT በአለም አቀፍ ህግ የተጣለባቸውን ግዴታዎች በተለይም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አይነት አድልዎ የማስወገድ ስምምነት (CEDAW) የጣሰ ተደርገው ተወስደዋል።

የምክር ቤቱ ፍርድ ቤት ከስልጣኑ በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሥልጣኑን አላግባብ እንደሚጠቀም የተቆጠረ ሲሆን በተለምዶ የጉዞ ደንቦች ላይ በሚወሰዱ እርምጃዎች የፍልስጤም የህግ መወሰኛ ምክር ቤት (PLC) ድምጽ ይሰጣል ወይም በከፍተኛ የዳኞች አስተዳደር ምክር ቤት ይፋ ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።[59]

## በተለያዩ አካላት የተወሰዱ ልዩ የሙግት ደርሻዎች፣ ደርጊቶች እና ስልቶች

ሰርኩላሩ ጠንካራ ተቃውሞ አስነስቷል።[60] በ OPT ውስጥ ካሉት ትላልቅ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አንዱ የሆነው የፍልስጤም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህብረት (PNGO) አባላቶቹን በፍጥነት በሁለት ዋና ዋና አንጓዎች ዙሪያ በመከፈል ከአካባቢው ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጋር በመተባበር እና ሙግቶችን በማጣመር ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ፣ በሕዝባዊ ተቃውሞዎች እና ማህበራዊ ጫናዎችን ማሰባሰብ ነበር ።አላማው የአካባቢው ባለስልጣናት ሰርኩላሩን እንዲሰርዙ ጫና ማድረግ ነበር።

የፍልስጤም መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ህብረት (PNGO) ከሚመለከታቸው የሲቪል ማህበራት ጋር በርካታ ስብሰባዎችን አድርጓል።ዘመቻውን ለመምራት፣ ሰፊ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና ጠንካራ የሙግት መልእክቶችን ለማስተላለፍ አቅም ያላቸው የሴቶች እና የወጣት ቡድኖችን ባለደርሻ አካትን ባለድርሻ አካላት አሳትፏል።

ከሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና ከ OPT ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (ICHR) ጋር በመሆን የመዘዋወር ነፃነትን እና የሴቶችን እና ህጻናትን መብቶች ለመጠበቅ የጋራ ድጋፍ እቅድ ለማውጣት እና ተግባራዊ ለማድረግ PNGO ተወካይ ኮሚቴ አቋቁሟል። የኮሚቴው መመስረትም አንኳር የክርክር ሃሳቦች በፍጥነት እንዲገለጹ እና ከፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ጋር በርካታ ስብሰባዎችን በማዘጋጀት ድጋፋቸውን እንዲያገኝ እና የፍርድ ቤቱን ምክር ቤት ሰርኩላሩውን እንዲሰርዝ ጫና ለመፍጠር አስችሎታል።

## የአደጋ ስጋት እሳቤዎች እና አስተዳደር

የሲቪል ማህበራት ተወካዮች ከሃይማኖት መሪዎች ጋር የሚደረግ ውይይት ፈታኝ እንደሚሆን ቢገነዘቡም ራሱን የቻለ አደጋን ሊያመጣ እንደሚችል አልገመቱም። የሲቪል ማህበራት ከፖለቲከኞች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በተመለከተ ስጋቶች ተንትነዋል እና ተለይተዋል። ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን በፍጥነት መለየት እና የቅድመ መከላከል እርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ እንደሆነ ታስቧል።

ከነዚህም መካከል ከለጋሾች እና ደንበኞቻቸው (ወይም ተቆርቋሪ አካላት) ጋር በተያያዘ በህብረቱና እና በሲቪል ማኅበራት ላይ ባላቸው መልካም ስም ሊደርሱ ከሚችሉ አደጋዎች፣ የመጀመሪያ እና ብቸኛው አሳሳቢ ጉዳይ ተነሳሽነቱን እንዴት እንደሚቀበሉ ግልጽ ግንኙነቶችን በመፍጠር እና የሴቶች እና ህጻናት ጥበቃ ላይ ያለውን ጉዳይ በማቅረብ ላይ የተመሰረተ ነው።

ጠንከር ያለ የህግ ትንተና ማዘጋጀት እና በሰነድ የተደገፈ የህግ ማዕቀፍ ለውሳኔ ሰጪዎችማካፈል፣ የሚወሰዱትን እርምጃዎች በአግባቡ ለማሳወቅ ብቻ ሳይሆን የተሳሳቱ መረጃዎችን ለመከላከልም አስፈላጊ ነበር።

በOPT ውስጥ የነበሩ የሲቪል ማህበር ህብረቶች ከልምዳቸው በመነሳት የሙግት ሂደትቶችን ሲያሳወቁ እንዲሁም የሙግት ስትራቴጂ እና የአደጋ ቅነሳ አካሄዶችን በተመለከተ አዲስ በተቋቋመው ኮሚቴ ውይይት ተደርጓል።

የሲቪል ማህበር ባለድርሻ አካላት በሙግት ተግባራት ከመሰማራት ውጭ ሌላ አማራጭ አላዩም። በተለይ የሴቶች እና የወጣቶች ቡድኖች ዝምታን መምረጥ ከመናገር የበለጠ አደጋ ያመጣል ብለው ያምናሉ። በመጨረሻም፣ በአጠቃላይ በሙግት ተግባራት ወስጥ ከተካተቱት በርካታ አከራካሪ ጉዳዮች እና የጸጥታ ስጋቶች አንጻር፣ OPT እና በዚያው አካባቢ ያሉ የሲቪል ማኅበራት ኃላፊነቶችን እና ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመጋራትና በትብብር ለመሥራት ወስነዋል።

ባለፉት ዓመታት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የጋራ ግንኙነቶችን የሚገነቡበት እና እንደ አጋር ሆነው የሚሰሩባቸው መንገዶች ፈጣን ለውጥ በማምጣታቸው የሙግት ተነሳሽነትን ለማደራጀት ምቹ ሆነዋል።



*በጋዛ ባህር ዳርቻ ጀንበር ስትጠልቅ ምስል በ ኪራን ዶህረቲ*

## የጋራ ውጤቶችን በትብብር እና በትኩረት የማላመድ ሂደት

በሙግት ተነሳሽነት ውስጥ በተሰማሩ አካላት መካከል ቀጣይነት ያላቸው ግንኙነቶችን ማመቻቸት የሙግት መነሳሳቶችን ለማስቀጠል ቁልፍ እርምጃ ነበር። ይህ የተገኘው በአካል በሚደረጉ ስብሰባዎች፣ በየቀኑ በሚደረጉ የስልክ ጥሪዎች፣ የቡድን ውይይቶች በፈጣን የመልእክት አገልግሎቶች (SMS ፣ ዋትስአፕ፣ ወዘተ) እና የመስመር ላይ ስብሰባዎች አማካኝነት ነው። በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች ከአንድ ወር ከባድ የሙግት ጥረቶች በኋላ የባለብዙ ባለድርሻ አካላትን ያካተቱ ስብሰባዎች፣ የተለያዩ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ የማህበራዊ ሚዲያ ጽሁፎች እና የግል ደብዳቤዎች ለሸሪዓ ፍርድ ቤት በማቅረብ የጠቅላይ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክር ቤት በሰርኩላሩ ላይ ማሻሻያ አድርጓል። ለሴቶች እና ህጻናት የጉዞ ገደቦችን በሚመለከቱ ሁለቱ በጣም ችግር ያለባቸውን አንቀጾች ለአጭር ጊዜ ተሻሽሏል።

PNGO አስቸኳይ ስብሰባ ጠርቶ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን የተሻሻለው ሰርኩላር እንዲሰረዝ በይፋ የጠየቁ ሲሆን ከአንድ ቀን በኋላ የምክር ቤቱ ፍርድ ቤት ሁሉም ሴቶች በነፃነት የመጓዝ መብታቸውን የሚያስጠብቅ ሌላ ማሻሻያ አስታውቋል። ሌሎች አከራካሪ ጽሑፎች ግን ቀርተዋል። እነዚህ የተሰረዙት በመንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተወካዮች ልዑካን ቡድን፣ በሴቶች የሚመራ የ PNGO ዘርፍ እርኒሁም የICHR ተወካዮች እና የሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክር ቤት መሪዎች በአካል ተገናኝተው ከበርካታ ሳምንታት ሙግት በኋላ ነው።

የተሟጋች ኮሚቴው አሁንም በሰርኩላሩ ውስጥ የተካተቱትን ጥሰቶች የሚገልጽ ደብዳቤ ያዘጋጀ ሲሆን ይህም ከሲቪል ማህበራት፣ ከመገናኛ ብዙሃን እና ከፖለቲካ ፓርቲዎች ቀጣይነት ያለው የጋራ ጫና ለመፍጠር ወሳኝ ነበር። ሰርኩላሩ ሙሉ በሙሉ ባይወጣም የሴቶችን የጉዞ ገደብ በሚመለከቱ አንቀጾች ላይ ግን ትልቅ ለውጦች ተደርገዋል።

በፍልስጤም የሚገኙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሙብት ጥሰቶች በሚከሰቱበት ጊዜ ከሰብአዊ ሙብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋር ተባብረው የሚሟገቱ ቢሆንም፣ PNGO ከሃይማኖት መሪዎች ጋር በሚደረገው ድርድር የፖለቲካ ፓርቲዎችን ድጋፍ እንደ ቁልፍ ስልት የማሰባሰብ ዘመቻ ያልተለመደ ነበር ። ሌላው ለጋራ የሙግት ጥረቶች ወሳኙ ነገር የኦንላይን ቅስቀሳ አካሄድ ሲሆን በተለይም የሴቶች እና የወጣቶች ቡድን በመደበኛነት በማህበራዊ ሚዲያ ፅሁፎች የዳኝነት ውሣኔዎችን በማቅረብ እና የሙብት ጥሰቶችን በማውገዝ ሰፊው ህብረተሰብ ሊሰራበት የሚችለውን ቴክኒካዊ የህግ ቃላቶች የሌሉበት ግልጽ ቋንቋ በመጠቀም ከህብረተሰቡ ጋር ማዛመድ ናቸው።

# አጋዞች እና መመሪያዎች

እ

# TOOL #1
## የተጋላጮች ጥበቃ የሙግት 'ችግሮች' እና ግቦችን መለየት

| | |
|---|---|
| **ችግሩ ምንድን ነው?**<br>*(የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ)* | አጭር ማብራሪያ (3-5 አ/ነገሮች) - ነባር ሰነዶችን፣ የጥበቃ ትንታኔዎችን ካሉ እነሱን ማጣቀስ |
| **ምን መለወጥ እንፈልጋለን?**<br>*(አላማ)* | በአንድ አ/ነገር ልናሳካው ሰለምንፈልገው ነገር |
| **ይህ ለውጥ ለምን አስፈለገ?**<br>*(እርምጃ ካልወሰድን ምን ይፈጠራል)* | ቁልፍ መልእክቶች: ከ 3-5 መገደብ (ቢበዛ እያንዳንዱ 3 አ/ነገሮች ያሉት)<br><br>1)<br><br>2)<br><br>3)<br><br>4)<br><br>5) |

*ከተጋላጮች ጥበቃ ጋር ተያይዞ (የተሰራ ትንተና ካለ)*

| | |
|---|---|
| **ከተጋላጮች ጥበቃ ጋር ተያይዞ የሚመጡ አደጋዎች ምንድን ናቸው?** *(የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ)* | ለእያንዳንዳቸው ዋና የተጋላጮች ጥበቃ ስጋቶች ከችግሩ ጋር የተያያዙ የተለዩ ነጥቦች ከተጋላጮች ጥበቃ ጋር ተያይዞ የሚመጣው አደጋ ምንድን ነው? |
| **ለውጡ የተጋላጮችን ጥበቃ ለመቀነስ እንዴት አስተዋጽኦ ያበረክታል?** *(የተጋላጮች ጥበቃ ትንታኔ)* | **ስጋቶች:** ለውጡ ዛቻዎችን ለመቀንስ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አጭር አ/ነገር (የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ካለ)<br><br>**ተጽኖዎች:** ለውጡ ዛቻዎች የሚያመጡትን ተጽእኖዎች ለመቀንስ እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት አጭር አ/ነገር (የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ካለ)<br><br>**አቅም:**ለውጡ አቅምን ለመጨመር ስለሚያበረክተው አስተዋጽኦ አጭር አ/ነገር (የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ካለ) |

# አጋዥ #2
## የተጋላጮች ጥበቃ ሙግት አላማዎች ምንነት

### ተጽእኖ የመፍጠር ስትራቴጂ ጠቅላላ ግብ/አላማ

የተፈለገው የለውጥ፣የተፅእኖ እና የዘመቻ ስትራቴጂ  አጠቃላይ አርዕስት መግለጫ አጭር፣ አሳማኝ ፣አነቃቂ እና በሰዎች ህይወት ወይም የአካባቢ መሻሻሎች ላይ ያተኮረ መሆን አለበት።

### ልዩ አላማዎች

አጠቃላይ ግቡን ለማሳካት አስተዋፅዖ የሚያበረክቱ በተለያዩ ሂደቶች የሚያልፉ ልዩ ልዩ የለውጥ ሂደቶችን ማዘጋጀት።

1)

2)

3)

# አጋዥ #3

## የባለድርሻ አካላት ልየታ

| ማን እና እንዴት? | ምን? | ለምን? | መቼ? |
| --- | --- | --- | --- |
| የትኞቹ ድርጅቶች እና ግለሰቦች? ውሳኔዎችን እንዴት እንደሚወስኑ ወይም እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳደሩ? | ግባቸውና ለመፍታት የሚፈልጉት ችግር ምንድን ነው?ውሳኔዎችን እንዴት እንደሚወስኑ ወይም እንዴት ተጽእኖ እንደሚያሳደሩ | ፍላጎታቸውና የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው? | ቁልፍ የውሳኔ ጊዜያት አሉ? |

## አጋዥ #4
## የሃይልና የባለድርሻ አካላት ትንተና ለስትራቴጂ ያለው አንድምታ

| የልየታው አቀማመጥ | የባለድርሻ አካላት መገለጫ | ምን ለማድረግ |
|---|---|---|
| **ከላይ በሚገኙት የማእዘን ጫፎቾ መካከል** | በጉዳዩ ላይ ገለልተኛ የሆኑ ትጽእኖ ፈጣሪ አካላት | ከእርሶ ጋር እንዲስማሙ ማሳመን |
| **በስእሉ መሃል ዙሪያ** | በጉዳዩ ላይ አነስተኛ ፍላጎትያላቸው አጋሮች | ጉዳዩ ጠቃሚ እንደሆነ ማሳመን |
| **Upper right quadrant** | ተጽእኖ ፈጣሪ አጋሮች | ከእነሱ ጋር ጥምረት ይፍጠሩ |
| **Bottom right quadrant** | አነስተኛ ተጽእኖ ያላቸውጠንካራ አጋሮች | ተጸኖን ለመገንባት |
| **Upper left quadrant** | ከፍተኛ ተጽእኖ ያላቸው ተቃዋሚዎች | በነሱ ላይ ትጽእኖ ለማሳደር ወይም የነሱን ትጸእኖ ለመቀነስ መንገዶችን መፈለግ |
| **Bottom left quadrant** | አነስተኛ ትጸእኖ ያላቸው ተቃዋሚዎች | Ignore and seek to isolate them |




Source: INTRAC.

# TOOL #5
## የመረጃ አሰባሰብ እቅድ ማሳያ

| የአላማዎች ተዋረድ (ተጽእኖ, የረጅም ወይም የአጭር ጊዜ ውጤት) | አመላካቾች | መነሻ መስመር (ከተቻለ) | Tools/የማረጋገጫ ዘዴ |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

| | የመረጃ ማሰባሰብ ድግግሞሽ | ሃላፊነት | እንዴት መረጃወን ማጋራት እንደሚቻል (ሪፖርት/ገለጻ) |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |

# አጋዥ #6

## ከሙግት መድረኮች በኋላ አጭር መግለጫ አዘገጃጀት መመሪያ

## የአጭር መግለጫ መመሪያ

### የመግለጫ መሰረታዊ ነገሮች

መግለጫዎች የቡድን አባላት ከባድ የስራ ጊዜያትን ወይም ትልልቅ ክስተትን የሚገመግሙበት ክፍለጊዜያት ናቸው። ከዝግጅቱ መጠናቀቅ በኋላ ትውስታዎች ሳይጠፉ ቢደረግ  በጣም የተሻለ ናቸው። ጊዜው አጠር ካለ የግማሽ ቀን  ክፍለ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ሊሆን ይችላል።

ቡድኖች አላማዎች ምን ያህል እንደተሟሉ ለመገምገም እና የወደፊት ድርጊቶችን ውጤት ለማሻሻል ትምህርቶችን ለመሳል ገለጻዎችን ያደርጋሉ። በተለይም ገለጻዎች ቡድኑ የተፈጠረውን ነገር ለመገምገም ወደ ኋላ መለስ ብሎ የሚመለከትበት አጋጣሚ ነው -"የጠበቅነውን አሳክተናል?" እና "ምን አዲስ እድሎች አሉ?" በማለት የበለጠ ውጤታማ እና የበለጠ ስኬታማ ለመሆን መንገዶችን ለመፈለግ እድል ነው።

### አጫጭር መግለጫዎችን ለማድረግ መሰረታዊ ነገሮች

- ከአላማዎች መጀመር። ያሰብነውን አሳክተናል? ያልተጠበቀ ነገር ተከስቷል? በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ግምገማዎችን ማምጣት
- በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ግምገማዎችን ማምጣት ምን ለመመርመር ነው የምንፈልገው? (ለምሳሌ የሚዲያ ሽፋን፣ የስብሰባ ውጤቶች፣ የተሰብሳቢዎች ብዛት እነማን እንደተገኙ ወዘተ).
- ስለተገኙ "ውጤቶች" እንዲሁም ስለ "ሂደቱ" ለመነጋገር ጊዜ መመደብ። ሁለቱም አፈጻጸሙን ለማሻሻል አስፈላጊ ነው።
- ግኝቶቹን፣ ማስረጃዎችን እና ምክረሃሳቦችን ጠቅለል ባለ ሪፖርት መያዝ በፓወር ፖይንት, ወይም በሚዲያ የመመዝገብና የማሰራጨ።

የሚቀጥለው ክፍል መግለጫዎች እንዴት እንደሚዘጋጁ፣ እንዴት እንደሚከናወኑ እና እንዴት ክትትል እንደሚደረግባቸው የበለጠ ዝርዝር ይሰጣል። የአክስፋም አሜሪካ የ 2010 አለም አቀፍ የሴቶች ቀን (IWD) እንቅስቃሴዎች በጠቅላላ እንደ ምሳሌነት ያገለግላሉ።

# ከማብራሪያው ክፍለ ጊዜ በፊት

የመግለጫ ክፍለ ጊዜን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ አስቀድሞ ማቀድ በጣም አስፈላጊ ነው። መግለጫው በዝግጅቱ ወይም በድርጊቶቹ አላማ በተለይም ቡድኑ ለመስራት ያሰበውን አከናውኗል የሚለውን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። በእነዚህ አላማዎች መሰረት ምን አይነት ማስረጃዎች የቡድኑን አላማዎች ለማሻሻል እንደሚረዱ መረጃዎች እንዴት መሰብሰብ እንዳለባቸው እና በማን እንደሚደረጉ መለየት። መግለጫው ከዝግጅቱ ወይም ከእንቅስቃሴው በኋላ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ መከናወን ስላለበት ከገለጻው በፊት ጠቃሚ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እና ለመተንተን አጭር የምልልስ ጊዜ ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ያለው ተግዳሮት የበለጸገ መረጃን በማግኘት እና በሰዎች መረጃን በመሰብሰብ እና በመተንተን አቅም መካከል ትክክለኛው ሚዛን ላይ መድረስ ነው።

**የማረጋገጫ ዝርዝር**

- ◻ የዝግጅቱ ወይም የእንቅስቃሴዎቹ አላማ ምንድን ነው?
- ◻ ውጤቶቹን ለመገምገም የሚያግዘው ምን አይነት መረጃና ማስረጃ ነው?
- ◻ መረጃውን እንዴት መሰብሰብ እንችላለን?
- ◻ መረጃውን የመሰብሰብ እና የመተንተን ሃላፊነት ያለበት ማነው?
- ◻ ከትክክለኛው ዝግጅት በፊት መግለጫውን ማቀድ

- ◻ በመግለጫው ውስጥ ማን መካተት እንዳለበት መለየት
- ◻ ለቡድኑ አባላት ማንኛውም ተዛማጅ ዝርዝር ያለው የማጠቃለያ ትንተና እና የቁሳቁስ ፓኬጅ ማዘጋጀት። ከተቻለ አስቀድሞ መላክ።

- ◻ ለመግለጫው የሚሆን አጀንዳ ማዘጋጀት።
- ◻ ለክፍለጊዜው የሚሆን ማስታወሻ ያዝ እና አስተባባሪ መመደብ
- ◻ በቁሳቁሱ ቅርጽ እና ስርጭት ላይ ከስምምነት መድረስ

**የመረጃ ምንጮች እነዚህን ያካትታሉ**

- የዳሰሳ ጥናቶች
- የመገናኛ ብዙሃን ውጤቶች
- የበጀት ክትትል
- የተሳታፊዎች ክትትል

- ቪድዮ/ቃለ መጠይቆች
- የውትወታ የጉብኝት ማስታወሻዎች

# በመግለጫው ክፍለጊዜ የሚሰጡ ጥቆማዎች እና ሃሳቦች

### የሚከተሉት ዋና ዋና ጥያቄዎች ናቸው

- "ምን ተፈጠረ?";
- "እና ምን?"; እና
- "በቀጣይ ምን?"

### በክፍሉ ወስጥ ማን መገኘት አለበት?

በሃሳብ ደረጃ ሁሉም በዝግጀቱ ወይም በውሳኔው ላይ የተሳተፉ የቡድን አባላት በመግለጫው ውስጥ መካተት አለባቸው።(ይህ ከሌሎች ክፍሎች የመጡ ተሳታፊዎችን ወይም በሂደቱ ውስጥ ብቻ የተሳተፉትን ያካትታል።) አንዳንድ ጊዜ ይህ የማይቻል በመሆኑ አነስተኛ ቡድን ብቻ ይሳተፋል።

### ምን ያህል ጊዜ ያስፈልገናል?

ይህ መግለጫው ባለው ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው —የክፍለ ጊዜው መጠን ከግማሽ ሰአት እስከ ሙሉ ቀን ሊደርስ ይችላል። በአጠቃላይ መግለጫው ለትልቅ ዝግጅት ወይም የረጅም ጊዜ ዘመቻ ወይም ፕሮጀክት ከሆነ ከግማሽ እስከ ሙሉ ቀን ሊያስፈልግ ይችላል።(እያንዳንዱ ቡድን እና መግለጫ የተለያየ ስለሆነ የእርሶን ግምት ይጠቀሙ።)

### አስተባባሪ ያስፈልገናል?

ይህ መግለጫው ባለው ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው። ለትልቅ ዝግጅቶች እንደ IWD እንቅስቃሴዎች የአስተባባሪዎች መኖር ቡድኑን በትክክለኛው መንገድ ለመምራት እና ሁሉም የቡድኑ አባላት በውይይቶች ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ በጣም ጠቃሚ ነው ። በሌላ በኩል መግለጫው በጣም አነስተኛ ለሆነ እንቅስቃሴ የቡድን መሪው ውይይቱን በቀላሉ ለማመቻቸት ይችላል። የማግቻቻ ሚናዎችንም ለማጋራት ይቻላል።

### በክፍሉ ውስጥ ምን መሆን አለበት?

አጀንዳ፣ ቻርቶች፣ ማርከሮች፣ አጋዥ መሳሪያዎች፣ አስፈላጊ ከሆነ ኮምፒውተር እና ፕሮጀክተሮች በክፍሉ ዉስ|ጥ ቢኖሩ።

የዝግጅቱ ወይም የእንቅስቃሴውን ውጤት ከመወያየት በተጨማሪ መግለጫው 'በሂደቱ' ዙሪያ ውይይት ማካተት አለበት። እነዚህ ሁለቱም ክፍሎች ጠቃሚ ትምህርቶችን ይሰጣሉ እንዲሁም ቡድኑ ወደፊት ጥረታቸውን እንዲያሻሽል ሊረዱት ይችላሉ።

ተፅዕኖዎችን እና ሂደቱን ለመወያየት አጠቃላይ የማጠቃለያ ክፍለ ጊዜ አጠቃላይ መግለጫ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል። ልብ ይበሉ እነዚህ ጥቆማዎች እንጂ ገለጻን ለማዋቀር ብቸኛው መንገድ አይደሉም።

### ምን ተፈጠረ?

- በዓላማዎች ተመርኩዞ የተሰበሰበ መረጃ ግምገማ
- በቡድኑ የቀረበ ግብረ መልስ እና ተጨማሪ መረጃ
- አስገራሚዎች፣ ያልተጠበቁ ውጤቶች፣ አዲስ ግንዛቤዎች
- ሊነሱ የሚችሉ ጥያቄዎች:- 'የጠበቅነውን አሳክተናል?'፣ 'ምን ጥሩ ሆነ?'፣ 'በሚቀጥለው ጊዜ የተለየ ምን እናደርጋለን?'

## እና ምን?

- የተቀመጡትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ ምን ያህል ውጤታማ ነበርን በሚለው ረገድ ምን እንማራለን?
- እነዚህን ስልቶች ከማዘጋጀት አንጻር ምን ተምረናል?
- የዚህ አይነቱን ዝግጅት፣ እንቅሳሴ ወይም ዘመቻ የመተግበር ሂደት አንጻር ምን እንማራለን?

## በቀጣይ ምን?

- እነዚህ የተወሰዱ ትምህርቶች ለወደፊቱ በተመሳሳይ ዝግጅቶች እና የዘመቻ እንቅስቃሴዎች መተግበራቸውን እንዴት ማረጋገጥ እንችላለን?
- ምን አይነት ክትትል ያስፈልጋል? ሃላፊነቱን የሚወስደው ማን ነው?
- ከመግለጫው በኋላ ዶክመንቱን እንዴት እናጠናቅራለን እና ሪፖርት እናደርጋለን? ታዳሚዎች እነማን ናቸው?(e.g. ሰራተኞች፣ የስራ ክፍሎች፣ የቡድን አባላት)። የተለያዩ የሪፖርት ማቅረቢያ ዘዴዎች መኖር በጣም አስፈላጊ ነው ።

የመግለጫ ክፍለ ጊዜ የሚሻሻለው የመረጃ ትንተናውን ማጠቃለያ በማቅረብ ነው፣ ነገር ግን ቡድኑ ለመወያየት ብዙ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል ነው - ለመረጃ ትንታኔ ምላሽ እና እንዲሁም ያልተያዙ መረጃዎችን በተመለከተ መተንተን ግን ዋጋ ያለው ነው።

እንዲሁም ሁሉንም የቀረቡትን አስተያየቶች ለመያዝ ማስታወሻ የሚይዝ መኖሩ አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም፣ የአይን ገላጭ እንቅስቃሴን ለምሳሌ ከዝግጅቱ ላይ ስላይድ ትዕይንት ማሳየት ወይም የስኬቶች ዋና ዋና ነገሮችን ማካተት አስፈላጊ ነው እንዲሁም ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

### ዝርዝር ቸክ ሊስት

- **ጊዜ ጠባቂ እና ማስታወሻ ሰጭ ይለዩ**
- **በክፍሉ ውስጥ ሁሉንም እቃዎች እና መሳሪያዎች ይኑርዎት:**

 አጀንዳ
 ፍሊፕ ቻርት
 ማርከር
 የእጅ ጽሑፎች
 ላፕቶፕ
 ፕሮጀክተር
 ድህረ-ሱ ወይም የቆሻሻ መጣያ ወረቀት

- **በአጀንዳው ውስጥ እነዚህን ያካቱ:**

 የዝግጅቱ ወይም የእንቅስቃሴው ዓላማዎች አጠቃላይ እይታ
▫ ለእያንዳንዱ ዓላማ የመከታተያ ውሂብን ይገምግሙ
▫ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ነገሮችን መተንተን
▫ ለሁሉም የቡድን አባላት ለውይይት እና አስተያየት በቂ ጊዜ መኖሩን ያረጋግጡ
▫ አስፈላጊ ከሆነ የኃይል ትንታኔን ያዘምኑ
▫ አስፈላጊ ከሆነ የጊዜ ሰሌዳውን እንደገና ይገንቡ
▫ ክትትል የሚያስፈልጋቸው ቦታዎችን መለየት እና ተጠያቂው ማን ሊሆን ይችላል።
▫ በአጠቃላይ ቡድኑ እንዴት ሪፖርት እንደሚያደርግ ይወስኑ

# ከመግለጫዉ መድረክ በኋላ

የማጠቃለያ ክፍለ-ጊዜው እንደተጠናቀቀ ቡድኑ በገለፃው ወቅት ተለይተው የሚታወቁትን ማንኛውንም እቃዎች መከታተል እና የተማሩት ትምህርቶች በትክክል መዝግበው ለሁሉም የቡድን አባላት እና ሌሎች በኤጀንሲው ውስጥ ካሉ ሌሎች የሚመለከታቸው ሰራተኞች ጋር የጋራ እንዲያደርጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

**ዝርዝር ቸክሊስት**

- **ሁሉም ክትትሎች መጠናቀቃቸዉን ያረጋግጡ**
- **የስብሰባውን ዋና ዋና ዜናዎች ሰብስቡ እንዲሁም ለሁሉም የቡድን አባላት ያቅርቡ**
- **የግንኙነት እቅድን ተግባራዊ ማድረግ - ማለትም. ሪፖርት፣ ዌቢናር፣ ፓወር ፖይንት አቀራረብ፣ ፓዳሬ መለጠፍ፣ ወዘተ**
- **የጠቃሚ ሰነዶች የመጨረሻ ቅጂዎች በግልፅ ምልክት የተደረገባቸው እና የተከማቹ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ይህ የሚያጠቃልለው፡-**

- ዝርዝር አጀንዳ
- የተሰበሰበ መረጃ ማጠቃለያ፣ ከጥሬው መረጃ ጋር በማያያዝ
- ከገለጻው ክፍለ ጊዜ የተሰባሰቡ ማስታወሻዎች
- የመጨረሻ ሪፖርት(ዎች) (ሰነድ ወይም አቀራረብ ሊሆን ይችላል)

## ምሳሌ፡ የ2010 አለም አቀፍ የሴቶች ቀን

**ከዝግጅቱ በኋላ፣ የIWD ቡድን የሚከተሉትን አድርጓል፡-**

- የመድረክ ተሳታፊዎች እና የኮንግረሱ አባላት ክትትል (የማግባባት ጉብኝቶችን ተከትሎ)
- ከገለጻው የተሰራጩ ማስታወሻዎች
- የተዘጋጀ ሪፖርት

# የወሳኝ ክንውን ማሳያ

## ይህ አጋዥ ለምን አገልግሎት ይውላል?

ይህ ማሳያ ወሳኝ የፖሊሲና ቅስቀሳ ክንዉኖችን፣ ትምህርቶችንና አበርክቶዎችን በቀላሉ ለመዘገብና ለማጋራት ያግዛል።

## እንዴትና መቼ አገልግሎት ላይ ይዉላል?

ይህ ማሳያ ጉልህ ከሆነ ፖሊሲ ወይም የዘመቻ ስኬት በኋላ በፖሊሲ እና ዘመቻዉን ባስተባበሩ ቡድኖች ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

ቡድኑ ይህንን ማሳያ በተለያዩ መንገዶች እና በተለያዩ የጥንካሬ ደረጃዎች ሊያጠናቅረው ይችላል። ቡድኑ በቡድኑ ውስጥ ባለው እውቀት እና/ወይም ተጨማሪ ማስረጃዎችን ለመሰብሰብ ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠትን ሊመርጥ ይችላል። ቡድኑ ርእሶቹን ለመወያየት የቡድን መግለጫ በማዘጋጀት ለጥያቄዎቹ መልስ ሊሰጥ ይችላል ወይም የቡድኑን አባላት ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ሊመድቡ ወይም የሁለቱንም አቀራረቦች ጥምረት መጠቀም ይችላሉ።

### መግለጫ

1. **የሚከተለዉን ማሳያ ይሙሉ (ቀጣይ ገጽ):**
2. **ጠቃሚ ዶክመንቶችን ያያይዙ (ለምሳሌ ኢሜል፣ ሪፖርቶችና የሚዲያ ቅጾች)**

   *ማስታወሻ: ቡድኑ እንዳስፈላጊነቱ ማሳያዉ ላይ ለውጥ ሊያደርግ ይችላል።*

## ወሳኝ ክንውን

**ስም:**

**ቀን:**

## ቀደምት አላማዎች

በፕሮጀክቱ መጀመሪያ ለማሳካት የታሰቡ ስራዎች?

## ቁልፍ ክንዉን

ምን ተፈጠረና ለምን ወሳኝ ሆነ?

## አስተዋጽ እና ማስረጃ

ምን አስተዋጽኦ አደረግን*? የኛ ጥረት ለለዉጡ አስተዋጽኦ እንዳደረገ በምን እናውቃለን†?

## ሌሎች ጉዳዮች: ዉጫዊ አወድና የሌሎች አበርክቶ‡

ለዉጡን ሌሎች ነገሮች እንዴት ቀረጹትና መሩት? የዉጫዊ አወዱ ተጽእኖ እንዴት ነበር? ሌሎች ቡድኖችና ሰዎች ተሳትፎ ነበራቸው?

## አማራጭ ማብራሪያዎች

ምን እንደተፈጠረ የሚያስረዱ አማራጭ ማብራሪያዎች? ለውጡ በሌላ ምክኒያት ላለመፈጠሩ ምን ማስረጃዎች አሉን?

## የገንዘብ መሰረታዊ ዋጋ

ምን አይነት ሃብቶች፣ ሁለቱም የሰራተኞች ጊዜ እና የወጣው ገንዘብ ጨምሮ ለዚህ ፕሮጀክት ጥቅም ላይ የዋለው? አላማዎችን በማሳካት ረገድ የነዚህ ግብቶአችና ስልቶች ውጤታማነት እንዴት ነበር ?

# አጋዥ #8

## ለለውጥ ያለውን አስተዋፅዖ መገምገም

# የጊዜ ሰሌዳ መልሶ የማዘጋጀት ሂደት መመሪያ

## ይህ መሳሪያ ለምን ጥቅም ላይ ይውላል?

ይህ ለውጥ እንዴት እንደተከሰተ ካርታ ለማሳየት እና ለለውጡ ያለንን አስተዋፅኦ ለመረዳት ይጠቅማል።

## እንዴት እና መቼ ጥቅም ላይ ይውላል?

ይህ ቡድኖች የቡድኑን ግቦች፣ አስተዋጽዖዎች እና የተወሰዱትን ትምህርቶች ከዳር ለማድረስ የእድገት አቅጣጫዎችን ለመለየት በየጊዜያዊ የስትራቴጂክ ግምገማ ክፍለ ጊዜዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

*ማሳሰቢያ፦ ይህ በቡድን አባላት መካከል አስተሳሰብን እና ውይይትን ለማነሳሳት የተነደፈ ሂደት ነው። ቢሆንም ግን ግምገማን አይተካም።*

## መግለጫ

### አጀማመር

- □ እንደ ማህደረ ትውስታ እገዛ የሚሆኑ ቁልፍ ቀናቶች፣ ተግባራት እና ያለፈው ሩብ (ወይም ሌላ የጊዜ ወቅት) ክንውኖችን በጊዜ መስመር የሚያሳዩ ቻርቶች።
- □ እንደ ማህደረ ትውስታ እገዛ የሚሆን የስትራቴጂው ወይም የክዋኔ ዕቅዱ ቅጂ።

### የፖሊሲና ፖሊቲካ ድሎችን መልሶ ማደራጀት *(45 ደቂቃ)*

- ባለፈው ሩብ ጊዜ የቡድኑን ቁልፍ ፖለቲካ* ወይም የፖሊሲ አሸናፊነት ስሜትን ፈልጉ። ሰዎች ሃሳባቸውን ለማስቀመጥ ተለጣፊ ማስታወሻዎችን ይጠቀማሉ። (10 ደቂቃ)
- ድምጽ ለመስጠት ተለጣፊ ነጥቦችን በመጠቀም (3 - 5) ላይ ለማተኮር አጭር ዝርዝር ይለዩ። (10 ደቂቃ)
- በሶስት ወይም በአራት ቡድን በቡድን በመስራት ለውጤቱ ያበቃውን 'የምክንያት መንገዶችን' እንደገና መስራት። እንደ የክስተቶች ሰንሰለት ወይም የማስረጃ ሰንሰለት እንደገና መገንባት። ያ ካለቀ በኋላ ማድመቅ እና ለድል እንዴት እንዳበረከተ መግለጽ (ለምሳሌ፡ የውትወታ ስራ፣ የተበረከተ የህግ ረቂቅ ጽሑፍ፣ የህብረት መድረክን መቅረጽ፣ ወዘተ)። (25 ደቂቃ)

### ለቀጣይ ስትራቴጂ የተወሰዱ ትምህርቶችን መሳል (45 ደቂቃዎች)

- *ጋለሪ መራመድ፡-* ከእያንዳንዱ ቡድን አንድ ሰው በመልሶ ግንባታው ይቆያል፣ ሌሎች ደግሞ በእንደገና ግንባታው ውስጥ ይሰራጫሉ። ‹አስተናጋጁ› ስለ መልሶ ግንባታው ባጭሩ ያብራራል። (15 ደቂቃ)
- በድሎች ውስጥ ምን አይነት ትምህርቶች መሳል እንደሚችሉ ለማየት ቡድኑ በሙሉ ወደ ስራዉ መጀመሪያ ይመለሳል። የሚያመሳስሉ ነገሮች አሉ? ያልተጠበቁ ነገሮች? ያመለጡ እድሎች? የበለጠ ማድረግ ያለብን ነገሮች? ያነሰ? ለተለያዩ ጾታዎች ወይም ቡድኖች (ወንድ እና ሴት፣ አዛውንት እና ወጣት ተሳታፊዎች፣ ወዘተ) የለውጥ ሂደት እና የውጤት(ቶች) ልዩነት የተሞከሮ ልምዶች ነበሩ? (30 ደቂቃ)

### ወጤቶች

- ላለፉት ሩብ ዓመታት የተመዘገቡ የፖሊሲ እና ፖለቲካ ድል ዝርዝር
- በጣም ጉልህ ለሆኑ ድሎች ያበረከቱት አስተዋፅኦ ወይም የቡድንዎ አስተዋፅዖ ሰነድ

- በቀሪው የስትራቴጂ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ለመመገብ ውጤታማ ዘዴዎች ስልታዊ ትንተና
- የግምገማ ዶክመንቶች (በግልጽ ውይይቶች ወቅት የድምጽ መቅጃ በመጠቀም እና ውይይቱን እና ትንታኔዎችን ለመያዝ እና ተለጣፊ ማስታወሻዎችን እራሳቸው በመጠቀም የምክንያት መንገዶችን ለድል አድራጊነት ለመመዝገብ)።

*** የፖሊሲ ድሎች**

➤ በአገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ከተሳትፎ ጋር በትክክል ልናገኛቸው የምንችላቸው በፖሊሲ ወይም በተግባር ላይ ያሉ ለውጦች (የህዝብ ወይም የግሉ ዘርፍ)።

➤ ሁለቱንም አወንታዊ ለውጦች እና አሉታዊ ለውጦችን ያካትታል። በፖሊሲ ላይ ትክክለኛ ለውጦችን፣ እንደ ሕግ ማስተዋወቅ ያሉ መካከለኛ ደረጃዎችን፣ እና በፖሊሲ ውስጥ ሊለካ የሚችል ማሻሻያዎችን ያካትታል።

**†የፖሊቲካ ድሎች**

➤ አሁን እና ወደፊት ድሎችን የማሳካት አቅማችንን የሚያሻሽል የፖለቲካ ሃይል፣ ተደራሽነት፣ ተጽእኖ እና ተገቢነት መጨመር።

➤ የሚያጠቃልለው፡ የፖሊሲ አውጪዎችን ተደራሽነት፣ የምርት ስርጭትን፣ በክርክር ረገድ ለውጦችን፣ የሚዲያ ጣልቃገብነትን እና የመስመር ላይ አግባብነትን ነው። የህዝብ መግለጫዎች እና እርምጃዎች በውሳኔ ሰጭዎች እና ተፅእኖ ፈጣሪዎች ፣ አዲስ ወይም የተጠናከሩ ግንኙነቶች ፣ ሻምፒዮናዎች ፣ ስብሰባዎች ፣ ዝግጅቶች ፣ የሪፖርት ጅምር ፣ ምስክርነት ፣ አጭር መግለጫዎች ፣ ወዘተ።

# የፔስትል አጋዥ መሳሪያ

## ፔስትልን እንዴት መጠቀም እንችላለን?

1. ለእያንዳንዳቸው ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ምድቦች በቀጥታ ችግር የሚፈጥሩ ወይም የችግሮቹን መዘዝ የሚነኩ ውጫዊ ሁኔታዎችን ይዘርዝሩ

- ፖለቲካ
- ኢኮኖሚክስ
- ማህበራዊ
- ቴክኖሎጂ
- ህጋዊ
- አካባቢ

2. ከእነዚህ ውስጥ የትኛው በጣም ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ይለዩ - እንደ እድሎች ወይም ስጋቶች። በእድሜ፣ በፆታ እና በልዩነት በሰዎች ላይ እንዴት እንደሚነኩ አስቡ።
3. ለጉዳዩ በጣም አስፈላጊ በሆኑት በአምስቱ ቁልፍ አዝማሚያዎች ላይ ይስማሙ።

### ፖለቲካ

**ርዕሰ ጉዳዮች**

- የመንግስት መረጋጋት
- የሙስና ደረጃዎች
- ሳንሱር
- የፖለቲካ አንጃዎች እና ጥምረቶች
- ህዝባዊ አመጽ ወይም ሰልፎች
- ክልላዊ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶች

**መ መመሪያ**

- መንግስት፣ ህግ አውጪ፣ የፍትህ አካላት ክትትል/ የቁጥጥር ማነስ፣እንዲሁም ሌሎች የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እና ግፊት ቡድኖችን ጨምሮ አግባብነት ያላቸው ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና አዝማሚያዎች ምን ምን ናቸው? እንዲሁም ለአለም አቀፍ ደረጃዎች (ለምሳሌ የስምምነት ቃል ኪዳኖች ወይም የክልል አካላት አባልነት) ምላሽ እንዴት እንደሚሰጡ አስቡበት።
- ሚኒስትሮች እና ጠቅላይ ሚኒስትሮች/ፕሬዝዳንቶች የሚሉትን ይመርምሩ። የቅርብ ጊዜ ንግግራቸውን ይገምግሙ እና በምርጫ ማኒፌስቶዎች ወይም በመንግስት እቅዶች ውስጥ ተገቢ ቃል መግባታቸውን እና እነዚህን ቃላቶች ላይ ማድረጋቸውን ይቆጣጠሩ። አግባብነት ያላቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እንደ የፖሊሲ ወረቀቶች ያሉ ኢላማዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ ከጥብቅና አጀንዳው ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን እና እየተሟሉ መሆናቸውን ለማየት መፈተሽ ተገቢ ነው።
- የፓርቲ ፖለቲካ በውሳኔ አሰጣጥ ላይም ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል፡ ለመንግስት አቋም ስምምነት መኖሩን ለማየት በፓርላማ ውስጥ ተገቢ ክርክሮችን መከለስ አስፈላጊ ነው. እንዲሁም የትኞቹ የፖለቲካ ተዋናዮች የሙግት ጥምረት ያቀደውን አጀንዳ ሊቃወሙ እንደሚችሉ መለየት እና ምላሹን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

## ኢኮኖሚክስ

### TOPICS

- የኢኮኖሚ እድገት
- የዋጋ ግሽበት እና የመሠረታዊ ዕቃዎች ተደራሽነት
- የንግድ ገደቦች
- የስራ አጥነት መጠን
- የድህነት ደረጃዎች

### *መመሪያ*

በሀገሪቱ ያሉ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች እና አዝማሚያዎች (መንግስት ገንዘቡን የሚያገኝበት፣ ዋና የግሉ ዘርፍ አሰሪዎች፣ የገቢ ክፍፍል እና የድህነት ደረጃዎችን ጨምሮ) ምን ምን ናቸው? ሃብቶች ብዙ ጊዜ አከራካሪ በመሆናቸው ለመንግስት ወይም ለዘርፉ የበጀት አዝማሚያዎችን ለመቅረጽ የታለመውን ዋና ምንጮች እና የገቢ ደረጃዎችን እና በመጨረሻም ፣ኢኮኖሚ ምን ሊሆን እንደሚችል መተንተን አስፈላጊ ነው። ለሲቪል ሰርቪስ አገልግሎት ሰጪዎች የመንግስት ሰራተኞች የአቅም ውስንነቶችን ማጤን ተገቢ ነው። ምክንያቱም የታቀዱትን ለውጦች ተግባራዊ ማድረግ ያለባቸው እነሱ ናቸው። በህብረት የታቀደ አጀንዳ እና ምላሹን ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው።

## ማህበራዊ

### ርዕሰ ጉዳዮች

- የህዝብ ቁጥር መጨመር
- የእድሜ ስርጭት
- የጤና ንቃተ ህሊና
- ባህላዊ ባህሪያት እና ወጎች
- የብሔር ወይም የሃይማኖት ስብጥር

### *መመሪያ*

በሀገሪቱ ውስጥ አግባብነት ያላቸው ማህበራዊ ሁኔታዎች እና አዝማሚያዎች (የስነ-ሕዝብ መረጃ፣ የትምህርት እና የጤና ስታቲስቲክስ፣ የሥራ ስምሪት መጠን፣ የመሬት ባለቤትነት፣ የሚዲያ ነፃነት፣ የሃይማኖት ትስስር፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ጨምሮ) ምን ምን ናቸው? ለድህነት እና ለሥርዓተ-ፆታ አለመመጣጠን አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ቁልፍ ጉዳዮችን አስቡባቸው።

## ቴክኖሎጂ

### ርዕሰ ጉዳዮች

- የፈጠራ እና አውቶሜሽን ደረጃዎች
- የበይነ መረብ ተደራሽነት እና ማህበራዊ ሚዲያ ባህል
- የቴክኖሎጂ ለውጥ
- የሳይበር ደህንነት ሁኔታ

### *መመሪያ*

በሀገሪቱ ያለው የቴክኖሎጂ ሁኔታዎች እና አዝማሚያዎች (ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ መሠረተ ልማት፣ የቴሌኮሙኒኬሽን እና የብሮድካስት ሚዲያ ተደራሽነት፣ ወዘተ) ምን ምን ናቸው?

## ህጋዊ

**ርእሰ ጉዳዮች**

- የ ኢ-መገለል ህጎች (ብሄር፣ ጾታና ሃይማኖትን በተመለከተ)
- የስራ እድል ህጎች
- የንብረትና ተጠቃሚነት ህጎች
- የጤናና ደህንነት ህጎች

***መመሪያ***

ከጥብቅና ስራ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ህጋዊ ምክንያቶች እና ገደቦች ምን ምን ናቸው? የታቀደው አጀንዳ አንዳንድ የሕግ አውጭ ቅድመ ሁኔታዎች ሊኖሩት ስለሚችል በሕገ መንግሥቱ፣ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና ዕቅዶች ውስጥ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አንቀጾች መከለስ አስፈላጊ ነው። ተሐድሶዎች ቀደም ብለው ተሞክረው ሊሆን ይችላል፣ ስለዚህ የእነዚህን ማሻሻያዎች ታሪክ መተንተን እና አሁን ያሉ ማነቆዎችን መለየት ተገቢ ነው። እንደ የሰብአዊ መብት ኮሚሽኖች ወይም እንባ ጠባቂዎች ያሉ ተቆጣጣሪ አካላት ርምጃ እንዲወስዱ ተሰጥቷቸው ስለመሆኑ እና ከጉዳዩ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ እየወሰዱ እንደሆነ መለየትም አስፈላጊ ነው።

## አካባቢያዊ

**ርዕሰ ጉዳዮች**

- የአየር ሁኔታ
- የአካባቢ ሁኔታ ፖሊሲዎች
- የተፈጥሮ አደጋዎች
- አስፈላጊ ሀብቶች (ውሃ ፣ ሰብሎች ፣ ወዘተ) ሁኔታ

***መመሪያ***

በአገሪቱ ዋና ዋና የአካባቢ ሁኔታዎች (የደን መጨፍጨፍ፣ ብክለት፣ ድርቅ/ጎርፍ፣ ግብርና ወዘተ) ምን ምን ናቸው? የአየር ንብረት ለውጥ የድርጅቶች ጥምረት ለመምከር ባሰበበት ጉዳይ ላይ ምን ያህል ይነካል? ምክንያት ከሆነ የትብብሩ ምላሽ እንዴት ግምት ውስጥ ያስገባል?

# አጋዥ #10

## ፈጣን እና ቀላል የአደጋ ስጋት ማትሪክስ*

| የታቀደ ተግባር | ለህብረተሰቡ የሚጠበቁ ጥቅሞች<br>(አማራጭ: ለአጋሮች) | በማህበረሰቡ፣ አጋሮች እና/ወይም ደጋፊዎች ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ ወይም ተጨባጭ አደጋዎች | እነዚህን አደጋዎች እንዴት መከላከል፣ መቀነስ ወይም ማስተዳደር ይቻላል? | በአስተዳደር ስምምነት የተደረሰባቸው ድርጊቶች/ማስተካከያዎች<br>(አማራጭ:- በማንና መቼ) |
|---|---|---|---|---|
| | | | | |

** ከኦክስፋም የአደጋ ማትሪክስ የተወሰደ*

**እድል:**

ሰለባ የሆኑ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት:

በውሳኔዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የሚችሉ ዋና ባለድርሻ አካላት፡-

**የስጋት ሁኔታ (ምን ሊሆን ይችላል/የአደጋ አይነት)፡**

የመሆን እድል፡ ከፍተኛ/መካከለኛ/ ዝቅተኛ

ተጽዕኖ፡ ከፍተኛ/መካከለኛ/ ዝቅተኛ

ክብደት፡- ጥቅማጥቅሞች ሊፈጠሩ ከሚችሉ አደጋዎች የበለጠ ክብደት አላቸው ተብሎ ይታሰባል? **አዎ**/ **አይ**

ሁኔታ: ▫ አረንጓዴ / ▫ አምበር / ▫ ቀይ

Actions:

አደጋን ለመከታተል ማትሪክስ በመደበኛነት መዘመን አለበት እና ስለሚከናወኑ ተግባራት በመረጃ ላይ የተመሠረተ ውሳኔ ሊሰጡ የሚችሉ ወሳኔ ሰጪዎችን ተሳትፎ ይጠይቃል።

# TOOL #11
## የትራፊክ መብራት ሲስተም ምሳሌ

### የሚገኘው ጥቅም ሊከሰቱ ከሚችሉ አደጋዎች የበለጡ ናቸው

ሊከሰቱ የሚችሉ አደጋዎችን ለመገምገም ‘የትራፊክ መብራት’ ስርአትን መጠቀም ይቻላል።

| አረንጓዴ | አምቢ | ቀይ |
| --- | --- | --- |
| ዕድሎች ከአደጋዎች በላይ ናቸው። እንደ ጉልህ የማይታዩ ሊሆኑ ይችላሉ አደጋውን ለማስኬድ ይቀጥሉ ግን ይቆጣጠሩ። | ሁኔታው በእድሎች እና በአደጋዎች መካከል ይበልጥ እኩል ነው። በመሆኑም በጥንቃቄ ይቀጥሉ። የበለጠ ጥብቅ የቅነሳ እና ክትትል ስራ ያስፈልጋል። | አደጋዎች ከሚፈጠሩ እድሎች በእጅጉ ይበልጣሉ። እንቅስቃሴዎችን ባለማስመቀጠል አደጋን ያስወግዱ። |

## አጋዥ #12

## የአደጋ ስጋት አጠቃላይ እይታ

| | ስጋት | የአደጋ ዒላማ | የመሆን እድል | ተጽዕኖ | የአደጋ ደረጃ | የቅነሳ እርምጃዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | |
| 2 | | | | | | |
| 3 | | | | | | |
| 4 | | | | | | |
| 5 | | | | | | |
| 6 | | | | | | |
| 7 | | | | | | |
| 8 | | | | | | |
| 9 | | | | | | |
| 10 | | | | | | |

## TOOL #13

## የአደጋ ስጋት ማትሪክስ (matrix) - መለኪያዎች: ዕድል / ተጽዕኖ

| | | ተጽእኖ<br>*(ለምሳሌዎች ቀጣዩን ገጽ ይመልከቱ)* | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ኢምንት | አነስተኛ | መጠነኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
| **የመሆን እድል** | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| **በጣም ከፍተኛ**<br>*ከምላ ጎደል እርግጠኛ፣ በጣም ሊሆን ይችላል።*<br>*> 90% ሊሆን ይችላል።* | 5 | 5 | 10 | 15 | 20 | 25 |
| **ከፍተኛ**<br>*በጣም ሊሆን ይችላል፣ ምናልባት ሊከሰት ይችላል።*<br>*60-90% የመሆን እድል* | 4 | 4 | 8 | 12 | 16 | 20 |
| **መካከለኛ**<br>*ሊከሰት ይችላል።*<br>*40-59% የመሆን እድል* | 3 | 3 | 6 | 9 | 12 | 15 |
| **ዝቅተኛ**<br>*10-39%ይቻላል ነገር ግን የማይታሰብ*<br>*10-39% ዕድል* | 2 | 2 | 4 | 6 | 8 | 10 |
| **በጣም ዝቅተኛ**<br>ሊታሰብ የሚችል ነገር ግን በጣም የማይመስል ነገር<br><10% የመሆን እድሉ | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |

# የተጽዕኖ ምሳሌዎች

| ኢምንት | አነስተኛ | መጠነኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|
| **ሰላምና ደህንነት** | | | | |
| በሰላምና ደህንነት ዙሪያ ምንም አይነት ለዉጥ የለም። | ጥቃቅን እንድምታዎች<br>ለሰራተኞች እና ለመሠረተ ልማት; ኤጀንሲዎች በሚገኙበት ጊዜ በካምፖች ውስጥ ውጥረት ይጨምራል። | ጠበኛ<br>በኤጀንሲው ሰራተኞች ላይ የተቃጣ ቁጣ። | አነስተኛ<br>አናሳ ኤጀንሲዎችን በመቃወም ሰልፍ፣ በባልደረባዎች ላይ ማስፈራሪያዎች፣ በሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ላይ የሚወረወሩ ድንጋዮች። | ሀይል የቀላቀለ<br>ቢሮዎች እንዲዘጉ/እንዲተኙ የሚያደርጉ የኃይል ሰልፎች; በሠራተኞች ላይ የሚደርሱ አካላዊ ጥቃቶች። |
| **አፐሬሽኖች፣ ፕሮግራማዊ እና ስልታዊ** | | | | |
| በኦፐሬሽኖች እና በፕሮግራሞች ላይ ጉልህ ያልሆነ ተፅእኖ። | ካምፖች አልተዘጉም እና ተደራሽነታቸው ተጠብቀዋል፣ ነገር ግን የጉዞ ፍቃድ እና ቪዛ እንቅፋቶችን ጨምሯል። ከግጭት አካባቢዎች ውጭ ባሉ ፕሮግራሞች ላይ ምንም ተጽእኖ የለም። | በግጭት አካባቢዎች ዙሪያ ወደሚገኙ ሁሉም ካምፖች እንዳይገቡ መከልከል። | በሀገሪቱ ግጭት በሚፈጠርባቸው አካባቢዎች መስራት ባለመቻሉ የመስክ ቢሮዎችን እንዲዘጉ መመሪያ ተሰጥቷል። | |
| **ታዋቂ እና ድርጅታዊ ባህል/እሴቶች** | | | | |
| አነስተኛ ተጽዕኖ ለምሳሌ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ አልፎ አልፎ የሚነገሩ ወሬዎች ወይም አሉባልታዎች። | ስለ ኤጀንሲዎች ባህሪ አጭር የሚዲያ ሽፋን ሲሰጥ፣ ከለጋሾች እና ሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ አካላት የተነሱ ጥያቄዎች ግን ወዲያውኑ ምንም ተጽእኖ የሌላቸው። | ረዘም ላለ ጊዜ ወሳኝ የፕሬስ ሽፋን፣ በአንድ ሀገር ውስጥ መዋቅሮችን በማስተባበር ላይ እምነት ማጣት፣ በመተማመን ጉድለት ምክንያት የገንዘብ ድጋፍ እድሎችን ሊያጡ ይችላሉ። | ቁልፍ ባለድርሻ<br>አካላት ከኤጀንሲዎች<br>ጋር ያላቸውን ግንኙነት<br>እና ድጋፍ እንደሚያነሱ<br>ያስፈራራሉ።<br>በአገር ውስጥ<br>የገንዘብ ድጋፍ ማጣት። | |

**የመጀመሪያ ደረጃ ባለድርሻ አካላት ጤንነት**

| | | | |
|---|---|---|---|
| በአጠቃላይ ጤንነታቸው ላይ ምንም ለውጥ የለም። | በጣም ጎጂ ባልሆኑ የጤና ጉዳዮች ላይ አነስተኛ ጭማሪ። | ሊቀለበስ የሚችል የጤና ተጽእኖ; ገዳይ ያልሆኑ ትናንሽ በሽታዎች መከሰት። | ቋሚ የጤና ጉዳት፣ የሞትና ዋና ዋና በሽታዎች መጨመር። |

# ማስታወሻዎች

# ማስታወሻዎች


1. https://reliefweb.int/report/world/2023-global-humanitarian-overview-presentation-global-humanitarian-overview-under-secretary-general-humanitarian-affairs-and-emergency-relief-coordinator-martin-griffiths-geneva-1-december-2022
2. ስለ ጥበቃ ስጋት ትንተና ለውሳኔ አሰጣጥ ማዕቀፍ እና ስለአደጋ ስጋት ማሰላሰል በተመለከተ በገጽ 9 ላይ በDG ECHO ጭብጥ ፖሊሲ ሰነድ ቁጥር 8 የሰብአዊ ጥበቃ (2016) እዚህ ማግኘት ይቻላልhttps://ec.europa.eu/echo/files/policies/sectoral/policy_guidelines_humanitarian_protection_en.pdf
3. በሰብአዊ ድርጊት ውስጥ የIASC ጥበቃ ፖሊሲ እዚህ ይገኛል: https://interagencystandingcommittee.org/iasc-protection-priority-global-protection-cluster/ iasc-policy-protection-humanitarian-action-2016
4. ስለ ሴትነት ተጽእኖ፣ እባክዎን የኦክስፋም የሴቶች ተጽዕኖ መመሪያን እዚህ ይመልከቱ:- https://oi-files-d8-prod.s3.eu-west-2.amazonaws.com/s3fs-public/file_attachments/oxfams_guide_to_feminist_influencing_english.pdf
5. ICRC(2018) ከICRC ፕሮፌሽናል ደረጃዎች የጥበቃ ሥራ እትም ገጽ 21 እዚህ ሊገኝ ይችላል:- https://www.icrc.org/en/publication/4342-professional- standards-protection-work-2018-abridged-edition
6. በጋራ ትንተና ተለይተው የሚታወቁ የጥበቃ ስጋቶች ማስረጃን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ለበለጠ መረጃ፣የአለምአቀፍ ጥበቃ ክላስተር ጥበቃ የትንታኔ ማዕቀፍ (PAF) እዚህ ይመልከቱ:- https://globalprotectioncluster.org/field-support/Protection-Analytical-Framework
7. አግባብነት ያለው አለምአቀፍ ህግ ለምሳሌ፡ አለም አቀፍ የሰብአዊ ህግጋት፡ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግ እና የአለም አቀፍ የስደተኞች ህግን በመጥቀስ
8. ከሲቪክ መሣሪያ ስብስብ፡ በግጭት ውስጥ ያሉ የሲቪሎችን ጥበቃን ማሳደግ እዚህ ሊገኝ ይችላል፣ https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
9. ከኦክስፋም ተፅዕኖ መመሪያ የተወሰደ ምስል: https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/handle/10546/621048/gd-influencing-for-impact-guide-150920-en.pdf?sequence=1)
10. የለውጥ ጽንሰ ሃሳብ በክፍል 2 የበለጠ ተብራርቷል።
11. ምስሉ የተወሰደው https://www.heatproject.eu/articles/stakeholder-mapping-for-advocacy-campaigns/
12. እንዲሁም የኦክስፋምን የኃይል ሚዛን ትንታኔ መመሪያ እዚህ መመልከት ይችላሉ: https://oxfamilibrary.openrepository.com/bitstream/handle/10546/313950/ml-quick-guide-to-power-analysis-210214-en.pdf?sequence=1
13. ከሀገር አቀፍ ባለስልጣናት ጋር ስለመገናኘት ለበለጠ መመሪያ እባኮትን ከOHCHR የመጡ የመመሪያ ሰነዶችን ይመልከቱ https://www.ohchr.org/sites/default/files/Documents/Publications/ Chapter31-24pp.pdf ወይም የኤዢያ ፓስፊክ የጥገኝነት ጥናት ማእከል https://cdn.auckland.ac.nz/assets/education/about/research/CAPRS/Final%20Practice%20Guide_%20Engaging%20Decision%20Makers%20GM%20CAPRS%20May%202022.pdf
14. የፖሊሲ ሰነዱን እዚህ ማግኘት ይችላሉ: https://odi.org/en/publications/protection-of-civilians-learning-from-icrcs-roots-of-restraint-in-war-study/
15. ሰነዶችን እዚህ ማግኘት ይቻላል: https://www.genevacall.org/documents/
16. የፀረ-ሽብርተኝነት ስጋቶችን ስለመቆጣጠር ተጨማሪ እዚህ ያንብቡ:- https://www.nrc.no/toolkit/principled-humanitarian-action-managing-counterterrorism-risks/

17. እባክዎን የHPG አጭር ማስታወሻ ይመልከቱ፡- በአለምአቀፍ እና በአካባቢ ጥበቃ ጥብቅና መካከል ማሟያ አቀራረቦች እዚህ፡- https://cdn.odi.org/media/documents/Advocacy_IP_National-international_collaboration_web_mhVpyZK.pdf
18. ለምሳሌ ይህንን ያንብቡ: https://odi.org/en/publications/advocating-together-to-strengthen-protection-collective-efforts-of-international-and-national-organisations/
19. https://www.un.org/peacebuilding/sites/www.un.org.peacebuilding/files/documents/2020_sg_call_to_action_for_hr_the_highest_aspiration.pdf
20. https://www.ipinst.org/wp-content/uploads/2022/03/UN-Agenda-for-Protection-PDF.pdf
21. https://interagencystandingcommittee.org/iasc-protection-priority-global-protection-cluster/iasc-policy-protection-humanitarian-action-2016
22. ለምሳሌ የWWF ፖሊሲ እና የሙግት መመሪያ በገጽ 29-31 ላይ ይመልከቱ፡- https://awsassets.panda.org/downloads/Policy_and_Advocacy_Toolkit_300617.pdf
23. HPG (2022) በሲቪሎች ጥበቃ ላይ የአገራት ፖሊሲ እና አሠራር ላይ ተጽዕኖ ማሳደር። ሰነዱ እዚህ ሊገኝ ይችላል: https://cdn.odi.org/media/documents/Influencing_states_policy.pdf
24. HPG (2021) በሰብአዊ መብት ተዋናዮች መካከል የትብብር ድጋፍ እዚህ ይገኛል፡- https://cdn.odi.org/media/documents/Advocacy_IP_Collaborative_advocacy_web.pdf
25. ለምሳሌ፣ የ IASC ማጣቀሻ ሞጁሉን ለክላስተር ማስተባበሪያ እዚህ ይመልከቱ፡- https://interagencystandingcommittee.org/iasc-transformative-agenda/iasc-reference-module-cluster-coordination-country-level-revised-july-2015
26. ICRC (2001) የባለሙያ ጥበቃ ስራዎች ደረጃ፣ እዚህ ይገኛል፡https://www.icrc.org/en/doc/assets/files/other/icrc_002_0999.pdf
27. HPG (2022) በሲቪሎች ጥበቃ ላይ የአገራት ፖሊሲ እና አሠራር ላይ ተጽዕኖ ማሳደር። ሰነዱ እዚህ ሊገኝ ይችላል: https://cdn.odi.org/media/documents/Influencing_states_policy.pdf
28. ምስሉ የተወሰደው: https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
29. እባኮትን የኦክስፋም ተጽእኖ ማሳደር መመሪያ፡ እንዴት ውጤታማ የተፅእኖ ስልቶችን ማቅረብ እንደሚቻል ይመልከቱ። https://policy-practice.oxfam.org/resources/influencing-for-impact-guide-how-to-deliver- effective-influencing-strategies-621048/
30. እባክዎትን ይህን ይመልከቱ: https://www.globalprotectioncluster.org/emergencies/protection-analysis-updates
31. እባክዎትን ይህን ይመልከቱ: https://odi.org/en/about/our-work/advocating-for-humanity-opportunities-for-improving-protection-outcomes-in-conflict/
32. ሪፖርቱ እዚህ ሊገኝ ይችላል: https://cdn.odi.org/media/documents/Influencing_states_policy.pdf
33. የሲቪክ ሙግት መመሪያ እዚህ ሊገኝ ይችላል። https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
34. ከሲቪክ ሙግት መመሪያ
35. ለአነስተኛ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች INTRAC Toolkit እዚህ ማግኘት ይቻላል፡- https://www.intrac.org/wpcms/wp-content/uploads/2022/06/BA-Advocacy-Toolkit.pdf
36. እባኮትን የኦክስፋምን ክትትል፣ ግምገማና መማር ኢጋዥ መመሪያ እዚህ ይመልከቱ: https://melofinfluencing.org/
37. የሲቪክ ሙግት መመሪያ እዚህ ሊገኝ ይችላል: https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf
38. ለምሳሌ የኦክስፋምን ክትትል፣ ግምገማና መማር ኢጋዥ መመሪያ እዚህ ይገኛል: https://melofinfluencing.org/
39. ይህንን ይጎብኙ https://www.civicus.org/monitoring-toolkits/toolkit/outcome-harvesting/
40. በተጨማሪም የአልናፕን የእሴት አይስበርግ፣ የመግት እና የዘመቻ ጥቅሞችን ማመዛዘን ይመልከቱ https://www.alnap.org/help-library/the-value-iceberg-weighing-the-benefits-of-advocacy-and-campaigning

41. ከ: https://www.intrac.org/wpcms/wp-content/uploads/2022/06/BA-Advocacy-Toolkit.pdf የተወሰደ

42. ከሲቪክ ሙግት መመሪያ የተወሰደ https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf

43. እባክዎትን ይህን ያገናዝቡ: https://www.iso.org/news/ref2263.html

44. ERM መነሻው በግሉ ዘርፍ ነው ነገር ግን በተባበሩት መንግስታት ስርዓት ውስጥ ያሉ አካላትን ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች ዋጋ አለው። እ.ኤ.አ. በ 2006 በፀደቀው 61/245 የውሳኔ ሃሳብ ጠቅላላ ጉባኤው አስተዳደርን እና ቁጥጥርን ለማጎልበት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስርዓት ውስጥ ERM እንዲፀድቅ አድርጓል።

45. ይህንን ይመልከቱ https://www.globalprotectioncluster.org/themes/protection_mainstreaming

46. ስለ አስተማማኝ እቅድ አሰራር ተጨማሪ፣ ይህንን ይመልከቱ https://www.oxfamwash.org/en/communities/safe-programming

47. ለምሳሌ፣ ይህንን ተመልከቱ: https://cdacollaborative.org/what-we-do/conflict-sensitivity/

48. የGISF ደህንነት ዝርዝር፡ ለሰብአዊ ርዳታ ኤጀንሲዎች የአደጋ አስተዳደር አጋዥ መሣሪያ ስብስብ እዚህ ሊገኝ ይችላል: https://gisf.ngo/resource/security-to-go/

49. ከሲቪክ ሙግት መመሪያ የተወሰደ https://civiliansinconflict.org/wp-content/uploads/2022/08/CIVIC_Advocacy_Guide-English.pdf

50. እባክዎን ስለ ማበረታቻ እና የአደጋ ስጋት ግንዛቤዎች እዚህ ካለው የODI ሪፖርት ያንብቡ፡ https://odi.org/en/publications/protection-advocacy-by-ingos-in-armed-conflict-situations-breaking-the-barriers/

51. https://reliefweb.int/report/syrian-arab-republic/nearly-120-schools-damaged-northwest-syria-floods-thousands-children

52. የሶሪያ ሴቶች አማካሪ ቦርድ የሰብአዊ ግንኙነት ቡድን (HLG) አካል ነው። ከሰብአዊ ሀገር ቡድን (ኤች.ቲ.ቲ.) ጋር እኩል ነው። እንዲሁም በቀጥታ የሰብአዊ አስተባባሪን ያማክራል። HLG በአካባቢው የሰብአዊ ማህበረሰብ ለሰሜን-ምዕራብ የሶሪያ ምላሽ ከፍተኛው የውሳኔ ሰጪ ቦታ ተደርጎ ይቆጠራል።

53. የትምህርት ዳይሬክቶሬቶች በሶሪያ ሰሜናዊ ክፍል በ ኢድሊብ፣ ላታኪያ፣ ሃማ እና አሌፖ አውራጃዎች ለትምህርት ፖሊሲዎች፣ ማስተባበር እና አስተዳደር ኃላፊነት ያላቸው የአካባቢ ደረጃ አካላት ናቸው። በአገር ውስጥ መሪዎች፣ ባለሥልጣኖች እና በገለልተኛ ቡድኖች የሚመራ ቢሆንም በመካከላቸው ያለው ቅንጅት አነስተኛ ነው።

54. https://hrs.ngo

55. 10ቱ እርምጃዎች፡ በሁሉም ስብሰባዎች እና ሰነዶች ውስጥ የአካባቢ ቋንቋዎችን በአግባቡ መጠቀም; የገንዘብ ድጋፍ ዘዴዎች አማካሪ ቦርዶች ላይ የተጎዱ ሰዎች ተሳትፎ; የሰብአዊ ፍላጎቶች አጠቃላይ እይታ (HNO) እና የሰብአዊ ምላሽ እቅድ (HRP) በተጠቁ ሰዎች ተወካዮች ማረጋገጥ; የተለያዩ ድምፆችን ማካተት ማመቻቸት እና ለሴቶች, ህጻናት, ወጣቶች, አረጋውያን እና የአካል ጉዳተኞች ፍላጎቶች ልዩ ትኩረት መስጠት; የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት ቅድሚያ መስጠት፣ በሁሉም የሰብአዊነት ቅንጅት ዘዴዎች; በሰብአዊ ማስተባበሪያ ስብሰባዎች የተጎዱትን ተሳትፎ ማረጋገጥ; በክላስተር አስተባባሪዎች ቀጥተኛ ተሳትፎን ማረጋገጥ፣ ከተጎዱ ማህበረሰቦች ጋር; በተጎዱ ሰዎች እና በሰብአዊነት መሪዎች እና ውሳኔ ሰጪዎች መካከል የሁለትዮሽ ግንኙነትን ማመቻቸት; የሶሪያ ሲቪል ማህበረሰብን ማጠናከር እና የሶሪያ ግብረሰናይ ድርጅቶች ከተጎዱት ጋር ለመነጋገር በሚደረጉ ጥረቶች ሁሉ ማዕከላዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ; እና የግብረመልስ ዘዴዎችን ማጠናከር ናቸው። ለተጨማሪ ይህንን ይመልከቱ: https://phap.org/PHAP/Events/ OEV2022/OEV220503.aspx እና https://www.humanitarianresponse.info/en/operations/stima/ document/action-plan-change

56. የኢንተር-ኤጀንሲ ቋሚ ኮሚቴ (IASC). (2010) IASC አገር ውስጥ ለተፈናቀሉ ሰዎች ዘላቂ መፍትሄዎች ማእቀፍ። https://interagencystandingcommittee.org/other/iasc-framework-durable- solutions-internally-displaced-persons እና ዘላቂ መፍትሔዎች አመላካች ቤተ-መጽሐፍት። https://inform-durablesolutions-idp.org/indicators-2/

57. የአውሮፓ የውጭ ግንኙነት ምክር ቤት (ECFR). (ኤን.ዲ.) የፍልስጤም ፖለቲካን ማቀድ። መግቢያ፡ ሲቪል ማህበረሰብ https://ecfr.eu/special/mapping_palestinian_politics/introduction_civil_society/

**58.** የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር (OHCHR) ቢሮ. (2022) በሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ውሳኔዎች S-9/1 እና S-12/1 መሰረት በተያዘው የፍልስጤም ግዛት ውስጥ ስላለው የሰብአዊ መብት ሁኔታ (A/HRC/49/83) አስራ አራተኛ ጊዜያዊ ሪፖርት። ከህዳር 1 ቀን 2020 እስከ ኦክቶበር 31 2021 ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። https://www.ohchr.org/en/statements/2022/03/occupied-palestinian-territory

**59.** ስለOPT የፍትህ ስርዓት ለበለጠ፣ ECFRን ይመልከቱ። የፍልስጤም ፖለቲካ ካርታ፡ የፍትህ ስርዓት። https://ecfr.eu/special/mapping_palestinian_politics/justice_system/

**60.** ይህንን ይመልከቱ https://images.alwatanvoice.com/news/images/3911129616.jpg; https://www.alwatanvoice. com/arabic/news/2021/02/14/1398515.html

**61.** የከፍተኛ ሸሪዓ ፍርድ ቤት ምክር ቤት የካቲት 21 ቀን 2007 ዓ.ም የፍትህ ስርአተ ደንብ ቁ. (02/2021) የመጀመሪያውን ሰርኩላር ቁ. (01/2021)